# መመሪያ ቁጥር ፱፻፸፯/፪ሺ፲፯

# አማራጭ የህፃናት ድጋፍና ክብካቤ መመሪያ

**መግቢያ** ....................................................................................1
**ክፍል አንድ** ....................................................................................2
**ጠቅላላ** ....................................................................................2
1. አጭር ርዕስ ....................................................................................2
2. ትርጉም ....................................................................................2
3. የመመሪያው የተፈጻሚነት ወሰን ....................................................................................5
4. የአማራጭ ክብካቤ አገልግሎቶች አሰጣጥ መሰረታዊ መርሆዎች ....................................................................................5
**ክፍል ሁለት** ....................................................................................6
**ጥቃት ለደረሰባቸውና ቸል ለተባሉ ሕፃናት ምላሽ ስለመስጠት** ....................................................................................6
**5. ምላሽ አሰጣጥ** ....................................................................................6
6. ለዚህ ክፍል አፈጻጸም ተግባራዊ የሚደረጉ አሰራሮች ....................................................................................7
7. የሕፃናት ጥቃትና ቸል መባልን ስለመጠቆም ....................................................................................7
8. የሕፃን የዳሰሳ ጥናት ....................................................................................8
9. ሕፃናት ከክብካቤ ሊወጡ ስለሚችሉበት ሁኔታ ....................................................................................9
10. ክብካቤን ለማቋረጥ ስለሚቀርብ ማመልከቻ ....................................................................................9
**ክፍል ሶስት** ....................................................................................10
**ቅንጅታዊ አሰራር** ....................................................................................10
11. ብሔራዊ ግብረ ኃይል ....................................................................................10
12. የአማራጭ ክብካቤ የቴክኒክ ቡድን ....................................................................................10
**ክፍል አራት** ....................................................................................10
**የአማራጭ የሕፃናት ክብካቤ የሚሰጡ አካላት ኃላፊነት** ....................................................................................10
13. የመንግሥት ተቋማት ኃላፊነት ....................................................................................10
14. አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ....................................................................................12
15. ቀጥተኛ ያልሆነ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ....................................................................................14
**ክፍል አምስት** ....................................................................................15
**ስለበጎፈቃደኞች እና ጎብኝዎች** ....................................................................................15
16. በበጎ ፈቃደኞች የሚሰጥ አገልግሎት ....................................................................................15
**ክፍል ስድስት** ....................................................................................16
**የክብካቤ ዘዴዎች አተገባበር ቅደም ተከተል** ....................................................................................16

17. የክብካቤ ቅደም ተከተል ደረጃዎች ....16
**ክፍል ሰባት** ....17
**ቤተሰብ ተኮር ክብካቤ** ....17
18. የቤተሰብ ተኮር ክብካቤ አገልግሎት አይነቶች ....17
ንኡስ ክፍል አንድ ....17
የቤተሰብ ጥበቃና አቅም ማጎልበት ....17
**19. የቤተሰብ ጥበቃና አቅም ማጎልበት አገልግሎት ዓላማና ግብ** ....17
20. የቤተሰብ ጥበቃና አቅም ማጎልበት አገልግሎት ተጠቃሚዎች ....18
21. የቤተሰብ ጥበቃና አቅም ማጎልበት አገልግሎት አሰጣጥ ዝቅተኛ መስፈርት ....19
ንኡስ ክፍል ሁለት ....20
መልሶ ማቀላቀል እና ማዋሀድ ....20
22. መልሶ ማቀላቀል እና ማዋሀድ ....20
23. የመልሶ ማቀላቀልና ማዋሃድ ቅድመ ሁኔታዎች ....21
24. የመልሶ ማቀላቀልና ማዋሃድ አገልግሎት የሚከተላቸው ሂደቶች ....21
25. የመልሶ ማቀላቀልና ማዋሃድ አገልግሎት ከመከናወኑ በፊት መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች ....21
26. ክትትልና ድጋፍ ....22
ንኡስ ክፍል ሶስት ....23
የተቋጥሮ ዝምድና ክብካቤ ....23
27. የተቋጥሮ ዝምድና ክብካቤ አገልግሎት አሰጣጥ ....23
28. የተቋጥሮ ዝምድና ክብካቤ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች ....23
ንኡስ ክፍል አራት ....25
የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ....25
29. የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አገልግሎት አሰጣጥ ....25
30. የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አፈጻጸም የሚከተላቸው መሰረታዊ መርሆዎች ....25
31. የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ዓይነቶች ....26
36. የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ሕጋዊ ውጤቶች ....28
37. የተገቢነት ደረጃዎች ....28
38. ሕፃናትን በአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ለመመደብ የተገቢነት መስፈርቶች ....28
39. ዕጩ የአደራ ቤተሰቦች ብቁነት መስፈርቶች ....29

40. ለአደራ ቤተሰብ ምዝገባ የሚቀርብ ማመልከቻ ....................30
41. የአደራ ቤተሰብ ሥልጠና....................31
42. የአደራ ቤተሰብ ምዝገባ....................31
43. የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አገልግሎት አሰጣጥ ዝቅተኛ መስፈርቶች....................31
ንኡስ ክፍል አምስት ....................36
ጉዲፈቻ ....................36
44. የጉዲፈቻ አገልግሎት አሰጣጥ መሰረታዊ መርሆዎች እና ዓላማዎች....................36
45. በጉዲፈቻ ተጠቃሚ ስለሚሆኑ ሕፃናት....................38
46. የጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰብ ብቁነት....................39
47. የጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና ማኅበራዊ ሠራተኞች ዝቅተኛ መስፈርቶች ....................40
**ክፍል ስምንት**....................46
**ማኅበረሰብ አቀፍ ክብካቤ** ....................46
49. ከድጋፍ ጋር ራስን ችሎ መኖር....................46
50. ለአገልግሎቱ የብቁነት መስፈርት....................46
51. የሚሰጡ አገልግሎቶች ....................47
52. ልየታ ....................48
53. መካሪዎች (ሜንቶር) ....................49
54. የድጋፍ እና የቅብብሎሽ አገልግሎት ....................51
55. የአገልግሎት ዕቅድ እና ስምምነት ....................52
56. የአገልግሎት መጠናቀቅ....................52
**ክፍል ዘጠኝ**....................53
**ተቋማዊ ክብካቤ አገልግሎት**....................53
57. ተቋማዊ ክብካቤ....................53
58. የተቋማዊ ክብካቤ ዓይነቶች....................53
59. የተቋማዊ ክብካቤ ዝርዝር ዓላማዎች ....................54
60. የተቋማዊ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ምዝገባ እና ሪፖርት....................55
61. መደበኛ ተቋማዊ፣ የተቀናጀ ማኅበረሰብ አቀፍ እና ልዩ ፍላጎት ላላቸው ሕፃናት የክብካቤ ተቋም ምስረታ ማመልከቻ....................55
62. የተገቢነት የዳሰሳ ጥናት እና የቅበላ ሂደት....................56

63. የቅበላ ቅጽ ....................................................................................................... 56
64. ከተቋም ውጪ ያሉ አማራጮች መታየታችውን ማረጋገጥ ....................................................... 58
65. የተቀናጀ ማኅበረሰብ አቀፍ የሕፃናት ክብካቤ አገልግሎት ዝቅተኛ መስፈርቶች ............................ 59
66. ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሕፃናት ልዩ ተቋማዊ ክብካቤ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ዝቅተኛ መስፈርቶች 62
67. መደበኛ ተቋማዊ የሕፃናት ክብካቤ ............................................................................ 65
68. መደበኛ ተቋማዊ የሕፃናት ክብካቤ አገልግሎት ዝቅተኛ መስፈርቶች ........................................ 66
**ክፍል አሥር** ........................................................................................................ 73
**በአስቸኳይ ጊዜ የሚሰጥ ክብካቤ** .................................................................................... 73
69. መነሻ ................................................................................................................ 73
70. በአስቸኳይ ጊዜ የሚሰጥ ክብካቤ መርሆዎች .................................................................... 73
71. የአስቸኳይ ጊዜ የባለድርሻ አካላት ሚና እና ኃላፊነት ......................................................... 74
72. የመለያየት ሥጋትን መቀነስ .................................................................................... 74
73. በአስቸኳይ ጊዜ የሚሰጡ አማራጭ የሕፃናት ክብካቤ ......................................................... 74
**ክፍል አሥራ አንድ** ................................................................................................. 75
**የጉዳይ አያያዝ የአሰራር ሥርዓት** ................................................................................... 75
74. የጉዳይ አያያዝ ...................................................................................................... 75
**ክፍል አሥራ ሁለት** ................................................................................................ 77
**የመረጃ አያያዝ፣ ክትትል እና ግምገማ** ............................................................................. 77
75. የመረጃ አያያዝ ...................................................................................................... 77
76. የሕፃን ማኅደር መክፈት ........................................................................................... 77
77. የመረጃ ክምችት፣ ዝውውር እና ደህንነት ...................................................................... 78
78. ሪፖርት ................................................................................................................ 79
79. ክትትል እና ግምገማ .............................................................................................. 80
**ክፍል አሥራ ሶስት** ................................................................................................. 82
**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች** ............................................................................................... 82
80. ተጠያቂነት ........................................................................................................... 82
81. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች ........................................................................................ 82
82. መስፈርቶችን ስለማውጣትና አሰራሮችን ስለመዘርጋት ....................................................... 82

83. የተሻሩ ህጎች .... 82
84. ተፈፃሚነት የሌላቸዉ መመሪያዎችና አሰራሮች .... 82
85. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ .... 82

## መግቢያ

በኢትዮጵያ በተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ በሆኑ ምክንያቶች ለችግር የተጋለጡና በተለያዩ አማራጭ የሕፃናት ድጋፍና ክብካቤ የሚያስፈልጋቸው ሕፃናት ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ ለእነዚህ ሕፃናት ደረጃውን የጠበቀና ሁሉን አቀፍ የሕፃናት ድጋፍና ክብካቤ ዘዴዎች ማመቻቸት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

አሁን በስራ ላይ የሚገኙ አማራጭ የድጋፍና ክብካቤ ዘዴዎች በተለያዩ ሰነዶች ውስጥ ተካተው የሚገኙ በመሆናቸው ለአስፈጻሚ አካላት ለአፈጻጸም አስቸጋሪ ከመሆናቸውም በላይ የህግ አስገዳጅነት የሌላቸው በመሆናቸው አንድ ወጥ የሆነና አስገዳጅነት ያለው የህግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ለፌዴራል የመንግሥት አስፈጻሚ አካላት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 19 (4) እንዲሁም አንቀጽ 36 (አ) እና (ኸ) በተሰጠው ህግ የማመንጨትና የማስፈጸም ስልጣን መሰረት ደረጃውን የጠበቀ አማራጭ የሕፃናት ድጋፍና ክብካቤ አገልግሎት አሰጣጥ እንዲኖር ይህን መመሪያ አውጥቷል።

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

## 1. አጭር ርዕስ

*ይህ መመሪያ* **“አማራጭ የሕፃናት ድጋፍና ክብካቤ *መመሪያ* ቁ**ጥር ፱፻፸፯/፪ሺ፲፯” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ትርጉም

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣ በዚህ *መመሪያ* ውስጥ፤

1) **“ሚኒስቴር”** ማለት የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ነው፡፡
2) **“ጥቃት”** ማለት በሕፃናት ላይ የሚፈጸም የአካል፣ የወሲብ፣ የሥነ-ልቦና፣ የማኅበራዊ ወይም የአዕምሮ ጉዳት የሚያስከትል ማንኛውም ድርጊት ሲሆን፣ የአካላዊ ጥቃትን፣ ቸል ማለትን፣ ወሲባዊ ትንኮሳንና የውስጥ ስሜት እንግልትን እና ከእነዚህ የጥቃት አይነቶች ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን ድርጊቶች የሚያካትት ነው።
3) **“ጉዲፈቻ”** ማለት ለችግር የተጋለጠና በተፈጥሮአዊ ወላጆቹ ሊያድግ ባልቻለ ሕፃንና የሕፃኑ ተፈጥሮአዊ ባልሆኑ ወላጆች መካከል በህግ መሰረት ቋሚ የወላጅነት እና የልጅነት ግንኙነትን የሚፈጥር ነው፡፡
4) **“አማራጭ ጊዜያዊ ክብካቤ”** ማለት በዚህ *መመሪያ* መሠረት አንድ ሕፃን በፍርድ ቤት ወይም በአስተዳደራዊ ወይም አግባብ ባለው አካል ውሳኔ ወይም በሕፃኑ ወይም በወላጆቹ ወይም በቀዳሚ አሳዳጊዎቹ ጥያቄ፣ ወይም ወላጆቹ በማይኖሩበት ጊዜ በክብካቤ ሰጪው ድንገተኛ ውሳኔ ቢያንስ ለአንድ አዳር ከወላጆች ቤት ውጭ ጥበቃ የሚደረግበት የክብካቤ አሰጣጥ ሲሆን፣ ሕፃኑ ከጓደኞቹ ወይም ከቤተሰቡ ጋር በጉብኝት ወይም በበዓል ምክንያት አዳሩን የሚቆይበትን ሁኔታ አያካትትም።
5) **“ክብካቤ”** ማለት የአንድን ሕፃን ሁለንተናዊ ደህንነት ለማስጠበቅ የሚተገበር ሂደት ሲሆን፣ ይህም ሁለንተናዊ ጥቅማችው ተጠብቆ ጥሩ አመጋገብ፣ ደህንነት፣ የጤና ክትትል፣ ተገቢ ምክር እና ምሪት እንዲያገኙ በማስቻል ለአካላዊ፣ አዕምሮአዊ፣ መንፈሳዊ፣ ሥነ ምግባራዊ እና ማህበራዊ ዕድገታቸው አስተዋጽዖ ማድረግ ነው።
6) **“የዳሰሳ ጥናት”** ማለት የአንድን ሕፃንና የቤተሰቡን ችግሮች፣ ፍላጎቶችና መብቶች ከማኅበረሰቡ አውድ አኳያ የመገንዘብና የማየት ሂደት ነው።
7) **“ቅርርብና ትሥሥር”** ማለት በሕጻናት እና በወላጆቻቸው ወይም ቀዳሚ አሳዳጊዎቻቸው መካከል የሚፈጠር አስተማማኝ፣ የእርስ በእርስ እና ዘለቄታዊ የሆነ የስሜት እና የስነ ልቦዊ የጋራ ቁርኝት ነው።
8) “**የሕፃኑ ጥቅምና ደህንነት”** ማለት ህግ አውጪው፣ ህግ ተርጓሚው፣ ህግ አስፈጻሚና መንግሥታዊ ያልሆኑ ናድርጅቶች ሕፃኑን በሚመለከቱ እርምጃዎችና ውሳኔዎች ውስጥ የሕፃኑን ፍላጎት መካተቱን ለማረጋገጥ ሕፃኑን፣ ሞግዚቱን ወይም የሚመለከተውን የመንግሥት አካል በማማከር የሚያከናውኑት ተግባር ነው፡፡
9) **“የሕፃኑ ጥቅም እና ደህንነት ዳሰሳ”** ማለት በአንድ በሚመለከተው ሕፃን ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር እርምጃ ከመወሰዱ በፊት የሚካሄድ ዳሰሳ ሲሆን፣ ይህም የሕፃኑ ጥቅም እና ደህንነት በአጠቃላይ ሂደቱ

የሕፃኑን ተገቢነት ያለው ተሳትፎ የሚያረጋግጥ የጉዳይ አያያዝ ቁልፍ አካል ሆኖ በሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀፅ 3 መሠረት በአንድ ሕፃን ስም ከሚሰጥ ውሳኔ ወይም ከሚወሰድ እርምጃ አኳያ የሕፃናት ጥበቃ ተዋናዮችን የመደገፍ እሳቤን የያዘ ነው።

10) **"የሕፃኑ ጥቅም እና ደህንነት ውሳኔ"** ማለት ለአንድ ሕፃን ወይም በቡድን ላሉ ሕፃናት መብቶቻቸውን በተሻለ የሚጠብቅ ሁለንተናዊ ውሳኔ መስጠት ይቻል ዘንድ አንድ ውሳኔ ሰጪ በአንድ ጉዳይ ላይ ተገቢነት ያላቸውን ሁሉንም ምክንያቶች የሚገመግምበትና የሚያመዛዝንበት፣ የተለዩ የአካሄድ ጥበቃዎችንና የሰነድ መስፈርቶችንም የሚያካትት የውሳኔ አሰጣጥ መደበኛ ሂደት ነው። ሂደቱም ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው የተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መብቶች ስምምነት፣ የአፍሪካ የሕፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር፣ እንዲሁም የአካል ጉዳተኞች መብት ስምምነት ውስጥ ለሰፈሩት መብቶችና ግዴታዎች ተገቢውን ትኩረት የሚሰጥ ነው፡፡

11) **"ተንከባካቢ"** ማለት የአንድ ሕፃንን ደህንነት ለመጠበቅ ኀላፊነት የተጣለበት ሰው ነው።

12) **"የክብካቤ ዕቅድ"** ማለት የሕፃኑን የዕድገት ፍላጎቶች በማን፣ እንዴትና መቼ ይሟላል የሚሉትን ለማከናወን ባለሙያው ያስቀመጣቸውን የግል ግቦች ለማሳካት የሚስፈልጉ ድጋፎች ክንውኖች እና ሀብቶችን በአጭሩ የሚዘረዝር የተጻፈ ሰነድ ነው። ሰነዱ ሲዘጋጅ ከሕፃናቱ ጥቅም አንጻር የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ ፣ ሕፃን ተኮርና ቤተሰብ አቀፍ የመረጃ አሰባሰብ፣ የፍላጎቶች ልየታ፣ የግብ መጣልና የዕቅድ ዝግጅት ሂደትን በመጠቀም ውሳኔዎችንና የተደረጉ ስምምነቶችን በአግባቡ በማሰናሰል የሚዘጋጅም ሰነድ ነው።

13) **"ጉዳይ መዝጊያ"** ማለት ከሕፃኑና ከተንከባካቢው ወይም ከቤተሰቡ ጋር የሚደረግ፣ ተከታታይ ምክክሮችንና ውይይቶችን የሚያጠቃልል ሆኖ የጉዳይ ዕቅድና በጉዳይ ማኅደሩ የውስጥ ሰነዶች ላይም የመጨረሻ ክለሳ የሚደረግበት ሂደት ነው። ይህም ልጁና ተንከባካቢው ወይም ቤተሰቡ የጉዳይ አመራር ግቦችንና ዓላማዎችን አሳክተው እንደሆነ ለመወሰን የሚያስችል፣ የጉዳይ ዕቅዱ የተሳካና አብሮ መኖሩ አስተማማኝና ዘላቂነት ያለው መሆኑ የታመነበት ከሆነ ወይም ጉዳዩ ሕጋዊ አግባብ ወዳላቸው ባለስልጣናት ወይም ወደ ሌላ አገልግሎት ሰጪ ለቀጣይ ክትትል ተላልፎ ከሆነ በዝርዝር በማካተት የሚዘጋጅ ነው፡፡

14) **"የጉዳይ ሥራ አስኪያጅ"** ማለት ከሕፃኑ ጥቅም እና ደህንነት ጋር በተያያዘ የሚሰጡ ውሳኔዎች በተሻለ መንገድ መሰጠታቸውንና ጉዳዩም ዕውቅና በተሰጣቸው አካሄዶች መሠረት መያዙን የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት፣ የጉዳይ ሠራተኞች ላይ ክትትል የሚያደርግ እና የሁሉንም ተሳታፊ ተዋናዮች ግብአቶችና የመረጃ ፍሰትን የማቀናጀት ኀላፊነት ያለበት ሰው ነው።

15) **"የጉዳይ አያያዝ"** ማለት የአንድ ህፃን ክብካቤ፣ ጥበቃና የድጋፍ ፍላጎቶች መሟላታቸውን የሚያረጋግጥ የትብብር ሂደት ነው።

16) **"የጉዳይ ሠራተኛ"** ማለት ጉዳይን ከመለየት ጀምሮ እስከ ማጠናቀቂያ ድረስ ለሕፃኑ ክብካቤ ኃላፊነት የሚወስድ ቁልፍ ሠራተኛ ሆኖ፣ በመንግሥት መስሪያ ቤት፣ ለትርፍ ባልተቋቋመ የበጎ አድራጎት ድርጅት፣ ወይም በዚህ መመሪያ አግባብ አማራጭ ክብካቤ ለመስጠት ፈቃድ ባለው ሌላ አካል የተቀጠረ ማኅበራዊ ሠራተኛ ወይም ተባባሪ ማኅበራዊ ሠራተኛ ነው።

17) **"ሕፃን"** ማለት ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው ነው።

18) **"የሕፃናት ጥበቃ"** ማለት ሕፃናት ከሁሉም የጉዳት ዓይነቶች መጠበቃቸውን የሚያረጋግጥ በአደረጃጀትና በተግባር እርምጃ የታገዘ ሂደት ሲሆን፣ አስፈላጊ ሥነ-ሥርዓት ተከትሎ በሕፃናት ላይ የሚፈጸምን ቸል መባልን፣ ብዝበዛንና ጥቃትን አስፈላጊውን ሥነ-ሥርዓት ተከትሎ የመከላከልንና ምላሽ የመስጠት ተግባር የሚያካትት ነው፡፡

19) **"የህጻን ጥበቃ ባለሙያ"** ማለት ህጻናትን ከማንኛውም ዓይነት ጥቃት፣ ብዝበዛ እና ጉዳት ለመጠበቅ የሚሰራ አግባብ ባለው ሙያ የሰለጠነ ባለሙያ ነው።

20) **"የማኅበረሰብ ክብካቤ ቅንጅት"** ማለት በህፃናት ደህንነት ጥበቃ ላይ ጉልህ ሚና ያላቸው፣ በቀበሌ ደረጃ የሚገኙ የሕፃናትን መብቶች በማስተዋወቅና ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ሕፃናትን በመለየት በተቀናጀ መልኩ አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያደርጉ ዘርፈ ብዙ ባለድርሻ አካላት ወይም በጎ ፈቃደኛ የማህበረሰብ አደረጃጀቶች ናቸው፡፡

21) **"ቤተሰብ"** ማለት ከህጻኑ ጋር የቅርብ ዝምድና ያላቸው የተፈጥሮ ወይም የጉዲፈቻ እናት፣ አባት፣ የእንጀራ እናት ፣የእንጀራ አባት፣ ፣ወንድም፣ እህት፣ አያት ወይም የተቋጥሮ ዝምድና ያላቸው አክስት፣ አጎት፣ የአጎትና የአክስት ልጆችን ይጨምራል ።

22) **"ሞግዚት"** ማለት ሕፃኑ አስራ ስምንት አመት እስኪሞላው ድረስ ለሕፃኑ የሚያስፈልገውን ስሜታዊ፣ ማኅበራዊ፣ አዕምሯዊ፣ ባሕላዊ፣ ሕጋዊና መንፈሳዊ አገልግሎት ምቹ በሆነ መኖሪያ ቦታ ለመስጠት ሃላፊነት የተሰጠው ሰው ነው፡፡

23) **"በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ስምምነት"** ማለት አገልግሎቱን ለማግኘት ስምምነታቸውን ለመግለጽ እድሜያቸው የማይፈቅድላቸው ህጻናት፣ ስለአገልግሎቱ በቂ ግንዛቤ ያላቸው ከሆነ ፈቃደኝነታቸውን በግልጽ በተነገረ ወይም በተገለጸ አኳኋን ሲሰጡ ነው፡፡

24) **"መካሪ"** ማለት አንድ ሕፃን ከማኅበረሰቡ ጋር ተቀላቅሎ እንዲኖር እና ራሱን እንዲችል ለማድረግ ስሜታዊና ማኅበራዊድጋፎችን ለማድረግ ተለይቶ የሚመደብ ባለሙያ ነው።

25) **"አካል ጉዳተኛ"** ማለት ማንኛውም ከሌሎች ጋር በእኩል በማህበረሰቡ ዉስጥ የተሟላ እና ውጤታማ ተሣትፎ እንዳያደርግ ሊከለክለው ወይም ሊገድበው የሚችል ዘላቂ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የአካል፤የስሜት ሕዋሳት፤የአእምሮ ወይም የግንዛቤ ውስንነት ያለበት ሰዉ ነዉ፡፡

26) **"ሥነ-ልቦናዊና-ማኅበራዊ ድጋፍ"** ማለት በተንከባካቢዎች፣ በቤተሰብ አባላት፣ በጓደኛ ፣ በጎረቤት፣ በመምህራን፣ በጤና ባለሙያዎችና በማህበረሰቡ አባላት የሚሰጥ በግልና በማህበራዊ አካባቢ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር ድጋፍና እንክብካቤ ሲሆን፣ ይህ ድጋፍ ልዩ ስልጠና ባላቸው አካላት የሚሰጥ ድጋፍን የሚጨምር ነው፡፡

27) **"ተመጣጣኝ ማመቻቸት"** ማለት አካል ጉዳተኞች በተናጠል ጉዳዮች ተፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሌሎች ጋር በእኩል ደረጃ የሰብዓዊ መብቶችና መሰረታዊ ነፃነቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ እርምጃው ያልተመጣጠነ ጫና የሚያስከትል እስካልሆነ ድረስ አስፈላጊና አግባብ ያላቸው ማሻሻያዎችና ማስተካከያዎችን ለማሟላት የሚፈፀም ክንውን ነው፡፡

28) **"ቅብብሎሽ"** ማለት በተቋማት መካከል የሚደረግ የአሰራር ሥርዐት ሲሆን ለሕፃናት ወይም ለቤተሰቦቻቸው ከሌሎች ድርጅቶች አስፈላጊ የሆኑ የገንዘብ ወይም የጤና ወይም ሌሎች ድጋፎችን እንዲያገኙ በመደበኛ አሰራር ወይም በተዘጋጀው ቅጽ መሰረት የሚከናወን ተግባር ነው፡፡

29) **"አግባብነት ያለው ቢሮ"** ማለት እንደ አግባቡ በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች ስር የሚገኙ የሴቶችን፣ ህጻናትን እና ማህበራዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ቢሮዎች ወይም ጽህፈት ቤቶች ናቸው።

30) **"ሥጋት"** ማለት ከግለሰባዊ ተጋላጭነት ጋር ተያያዠነት ያላቸው ድህነት፣ የአካል ጉዳት ወይም መገለልን የሚመለከት ሲሆን የአደጋ መከሰት፣ የአደጋው ከፍተኛነትና የሚያስከትላቸው ጉዳቶች፣ በውጫዊና ውስጣዊ ችግር የሚፈጠሩ ፣ በጦር መሳሪያ የሚፈጸም ጥቃት፣ የተፈጥሮ አደጋዎች፣ጾታን መሰረት በማድረግ የሚፈፀም ጥቃትን የሚጨም ነው ፡፡

31) **"የሥጋት ዳሰሳ ጥናት"** ማለት የማኅበረሰቡን ችግር የመቋቋም ወይም ከተፅዕኖ የማገገም ችሎታን በተለይ ሕፃናትንና ቤተሰባቸውን ሊጎዱ የሚችሉ ታሳቢ አደጋዎችንና አሁን ያሉ የተጋላጭነት ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት የሥጋትን ተፈጥሮና መጠን የመወሰን ሥነ ዘዴ ነው።

32) **"የሥጋት መነሻ ምክንያቶች"** ማለት በበሽታ የመጠቃት ዕድልን፣ በአካል ላይ ወይም በደህንነት ላይ ጉዳት የመከሰት ስጋትን የሚጨምሩ የአንድ ግለሰብ ወይም ሕፃን ልዩ ባሕርያት ወይም ተጋላጭነት ናቸው።

33) **"ፍለጋ"** ማለት ከወላጆቹ ወይም ከአጠቃላይ ቤተሰቡ የተነጠለ ሕፃንን ከወላጆች ወይም የተቋጠሮ ዝምድና ካላቸው ቤተሰቡ ጋር ለማገናኘት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የመሰብሰብና መገኛ ቦታቸውን የመለየት ዓላማ ያለው በሚመለከተው የመንግሥት ባለስልጣን፣ በማኅበረሰቡ አባላት፣ በዘመዶች ወይም በሌሎች ወኪል ድርጅቶች የሚከናወን ተግባር ነው።

34)**"ተጋላጭ ሕፃን"** ማለት በተለያዩ ምክንያቶች ደህንነቱ፣ ሕልውናውና ዕድገቱ ሥጋት ላይ የወደቀበት ሕፃን ሲሆን በተለይም ህጻኑ የስሜት መጎዳት፣ ከትምህርት ገበታ የመለየት፣ በበሽታ፣ በተመጣጠነ ምግብ እጦትና በመሳሰሉት ሁኔታዎች ከአቻዎቹ በባሰ ሁኔታ አሉታዊ ጉዳቶች ያጋጠው ሕፃን ነው።

35) **"ተጋላጭነት"** ማለት የአንድን ማኅበረሰብ ወይም ግለሰብ ለችግር እና ለአደጋ የመጋለጥ ዕድልን ከፍ የሚያደርጉ፣ ብሎም በማጣት፣ በጉዳት፣ በአለመረጋጋት እንዲሁም በሞት ሳቢያ አደጋ ውስጥ የሚከቷቸው አካላዊ፣ ማኅበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ምክንያቶች ናቸው።

36)**"ታዳጊ ሕፃናት"** ማለት እድሜአቸው ከ15 እስከ 18 ዓመት ያሉ ህጻናት ናቸው፡፡

37)በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## 3. የመመሪያው የተፈጻሚነት ወሰን

1) ይህ መመሪያ አግባብነት ባላቸው በሁሉም የፌደራልና የከተማ አስተዳደሮች የመንግሥት ተቋማት፣ በጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና በፌደራል መንግሥት የሕፃናት ክብካቤ አገልግሎት ለመስጠት ፍቃድ በተሰጣቸው አገልግሎት አቅራቢዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

2) ክልሎች ይህን መመሪያ እንደመነሻ በመውሰድና የአካባቢያቸውን ነባራዊ ሁኔታ ወይም ዐውድ በማገናዘብ የራሳቸውን መመሪያ ማዘጋጀት ይችላሉ።

3) ይህ መመሪያ የወጣት ጥፋተኞችን በሚያቆዩ ተቋማት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

## 4. የአማራጭ ክብካቤ አገልግሎቶች አሰጣጥ መሰረታዊ መርሆዎች

1) በዚህ መመሪያ ስር የሚከናወኑ ሁሉም መስተጋብሮች፣ ዕቅዶች፣ ውሳኔዎች እና ተግባራት የተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መብቶች ስምምነት ባስቀመጣቸውና ከዚህ በታች በተገለጹ አራት አጠቃላይ መርሆዎች መሰረት የሚመሩ ይሆናል፣

ሀ) **አድልዎ የሌለበት አገልገሎት፡-** በአማራጭ ክብካቤ ላይ የሚሰጡ ማንኛውም ውሳኔዎች የሕፃናቱን ሥርዓተ-ጾታ፣ የዘር ማንነት፣ ሃይማኖት፣ ትውልድ፣ የወላጆች ሁኔታ፣ የአካል ጉዳት፣ የቋንቋና የፖለቲካ ወይም ሌላ አመለካከትን መሰረት ያላደረገ አድልዎ የሌለበት አገልግሎት የማግኘት መብታቸውን ያከበሩ መሆን አለባቸው። አገልግሎቶች ያለ አድሎና ለሕፃኑ ልዩ ፍላጎቶች ትኩረት በመስጠት የሚቀርቡ ይሆናል። ሁሉም ሕፃናት ዜግነታቸው፣ ብሔራቸው፣ ጾታቸው፣ ዕድሜያቸው፣ ችሎታቸው ወይም ያሉበት ሁኔታ ከመጠበቅና ለሕይወታቸውና ለዕድገታቸው የሚያስፈልጓቸውን መሠረታዊ አገልግሎቶች ከማግኘት ሊያግዷቸው አይገባም።

ለ) **የሕፃኑ ጥቅምና ደህንነት ፡-** በዚህ መመሪያ ሥር የሚሰጡ ማንኛውም ውሳኔዎችና የሚወሰዱ እርምጃዎች የሕፃኑ ጥቅምና ደህንነትን በዋናነት ግምት ዉስጥ ያስገቡ መሆን አለባቸው።

ሐ) **የሕፃኑ ህልዉናና ዕድገት**፦ በዚህ መመሪያ የሚሰጡ ማንኛውም ውሳኔዎችና የሚወሰዱ እርምጃዎች የሕፃኑን ህልዉናና ዕድገት በከፍተኛ ደረጃ የማረጋገጥ ዓላማ ሊኖራቸው ይገባል።

መ) **ተሳትፎ፦** በዚህ መመሪያ የሚሰጡ ማንኛውም ውሳኔዎችና የሚወሰዱ እርምጃዎች የሕፃኑን ሐሳብ የመግለጽ፣ ከግምት ውስጥ የማስገባት ብሎም ተገቢውን ክብደት የማግኘት መብቶች ሙሉ በሙሉ ሊያከብሩ ይገባል። ይህም ሕፃናት ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚያስችል መረጃ ማግኘትን ያካትታል።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተቀመጡት አጠቃላይ የተባባሩት መንግሥታት የሕፃናት መብት ስምምነት መርሆዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ መመሪያ ስር የሚከናወኑ ሁሉም መስተጋብሮች፣ ዕቅዶች፣ ውሳኔዎችና እርምጃዎች ሁሉ የሚከተሉትን መርሆዎች መከተል ይኖርባቸዋል፣

ሀ) **መነጣጠልን መከላከል፦** ሁሉም የአገልግሎት አይነት ሲሰጥ ቤተሰቦችን ሳይበተኑ እንዲቆዩ ለማገዝ እና ተለያይተው የነበሩ ቤተሰቦችን መልሶ ለማቀላቀል የሕፃኑን ጥቅምና ደህንነት መሠረት ያደረጉ ምክንያታዊ እርምጃዎች ሁሉ መወሰድ አለባቸው።

ለ) **ጉዳት አለማድረስ፦** ሕፃናትን በሚመለከት የሚወሰዱ ማንኛውም እርምጃዎችና ውሳኔዎች ሕፃኑን ለመደገፍ እና ተጨማሪ ጉዳትን ለማስወገድ ወይም ጥቃትን እና መገለልን ለመከላከል፣ በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ስምምነትን እና ምሥጢር መጠበቅን ለማረጋገጥ ዓላማ ያደረጉ መሆን አለባቸው።

ሐ) **በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ስምምነት፦** በማንኛውም ሁኔታ አገልግሎቶችን ከመስጠት በፊት ሕፃናትና ቤተሰቦቻቸው ወይም ተንከባካቢዎቻቸው ስምምነት ሊጠየቁ ይገባል።

መ) **ለመኖሪያ ቦታ ያለው ቅርበት፦** በአማራጭ ክብካቤ ውስጥ የሚሰጡ ማንኛውም ውሳኔዎች ሕፃናት ከቤተሰቦቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነትን ለማስቀጠል፣ መልሶ የማቀላቀል ዕድልን ለማመቻቸት እንዲሁም የትምህርት፣ የባህልና ማኅበራዊ ሕይወት እንዳይቋረጥ ሕፃናትን ከተለመደው የመኖሪያ ቦታቸው በቅርብ ርቀት የማቆየትን አስፈላጊነት ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው።

ሠ) **ዘላቂነት**፦ በኢ-መደበኛ ክብካቤ ያሉ ሕፃናትን ጨምሮ በአማራጭ ክብካቤ ውስጥ ያሉ ሕፃናትን የሚመለከት ማንኛውም ውሳኔ ዘላቂነትን ግብ በማድረግ ሕፃናት በተረጋጋና መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸው በሚሟላበት ቤት ውስጥ ደስተኛ ሆነው መኖራቸውን እና ከተንከባካቢዎቻቸው ጋር የሚኖራቸውን ትስስር ቀጣይነት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊነትን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት።

## ክፍል ሁለት

## ጥቃት ለደረሰባቸውና ቸል ለተባሉ ሕፃናት ምላሽ ስለመስጠት

### 5. ምላሽ አሰጣጥ

1) ሕፃናት በሁሉም የክብካቤ አማራጭ ተጠቃሚ በሚሆኑ ጊዜ ከጥቃት፣ ቸል ከመባል እና ከሁሉም አይነት ብዝበዛ መጠበቅ አለባቸው።

2) በሕፃኑ ላይ ሊፈጸም የሚችል አካላዊ፣ ወሲባዊ፣ ስሜታዊ፣ ወይም ሥነ-ልቦናዊና ማኅበራዊ አሳሳቢ የደህንነት ስጋት ካለ ሕፃኑ ወደ ፖሊስ ወይም አግባብነት ወደ አላቸው ቢሮዎች ወይም የተቀናጀ የፍትህና እንክብካቤ ማእከላት እንዲመራ መደረግ አለበት።

3) በሕፃኑ ላይ የወሲብ ትንኮሳ ወይም የተለያዩ አካላዊ ጥቃቶች መፈጸሙ ከተጠረጠረ ወይም ከተረጋገጠ ሕፃኑ ተገቢ የሕክምና እንክብካቤ ማግኘት አለበት።

## 6. ለዚህ ክፍል አፈጻጸም ተግባራዊ የሚደረጉ አሰራሮች

1) የሕፃናት ጥቃት እና ቸል መባልን መከላከል እንዲሁም የቤተሰብ ጥበቃ ለሚቀርቡ ጥቆማዎች ምላሽ መስጠት ቀዳሚ ዓላማ መሆን ይገባዋል።

2) ሕፃናትን ከቤተሰባዊ አኗኗር ሁኔታ ማለያየት ወይም ማራራቅን በተመለከተ የሚደረግ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት ለሕፃኑ ደህንነትና ሕልውና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ የሚፈጸም ነው።

3) ሕፃናትን ካሉበት የቤተሰብ ወይም የአማራጭ ክብካቤ እንዲወጡ ማድረግ እንደ መጨረሻ አማራጭ መታየት ያለበት ሲሆን ውሳኔው ጊዜያዊ እና ጥንቃቄ የተሞላው ክትትልና መደበኛ ግምገማ የሚደረግበት መሆን አለበት።

4) ከቤተሰብ ወይም ከአማራጭ ክብካቤ እንዲወጡ የተደረጉትን ሕፃናት ወደ ተቋማዊ ክብካቤ ማስገባት እንደ መጨረሻ አማራጭ ሊወሰድ ይገባል፣ ቅድሚያ ለተቋጥሮ ዝምድናና ለአደራ ቤተሰብ መሰጠት አለበት።

5) በዚህ ክፍል ሥር ለሚሰጥ ማንኛውም ውሳኔ የሕፃኑ ደህንነትና ጥቅም መሰረታዊ መርህ ሆኖ ያገለግላል።

6) ለሕፃናቱ ደህንነትና ጥቅም ሲባል ካልሆነ በስተቀር ወንድማማቾች ወይም እህትማማቾች መነጣጠል የለባቸውም።

## 7. የሕፃናት ጥቃትና ቸል መባልን ስለመጠቆም

1) የሕፃናትን ደህንነት፣ ጥቃት እና ቸል መባልን በተመለከተ አሳሳቢ ሁኔታ መፈጠሩን የሚያውቅ ወይም የሚጠረጥር ማንኛዉም ሰዉ ወይም ሕፃን  በወረዳ ወይም በቀበሌ ደረጃ ለሚገኙ  አግባብነት ያላቸው ቢሮዎች  ወይም የተቀናጀ የፍትህና እንክብካቤ ማእከል ወይም ለፖሊስ ወይም ለሕፃናት ጥበቃ ባለሙያ ጥቆማ  ማድረግ ይኖርበታል።  ሕፃናት ራሳቸው ሊጠቁሙ ይችላሉ።

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ አንድ ላይ በተመለከተው መሰረት የሚቀርብ ያልተረጋገጠ ጥቆማ በቅን ልቦና ላይ ተመስርቶ የቀረበ ከሆነ ጥቆማ አቅራቢውን የሃሰት ማስረጃ በማቅረብ በሚል ተጠያቂ  አይሆንም፡፡

3) ጥቃት ወይም ቸል መባል መፈጸሙ ጥቆማ የቀረበለት የሚመለከተው አካል ድርጊቱ የተከሰተበትን ጊዜ፣ ቦታና አድራሻ እንዲሁም  የሕፃኑን እድሜ እና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች ላይ አትኩሮት በመስጠት አስፈላጊውን መረጃ መያዝ አለበት።

4) ጥቆማው ስለ ተከሰተው የጥቃትና የብዝበዛ አይነት፣ ቸል መባል፣ በሕፃኑ ላይ የደረሰን የአካል፣ የሥነ-ልቦና ወይም የወሲብ ጥቃት  እንዲሁም በአስቸኳይ የተሰጠ ሕክምና በተጨማሪም ከጥቃት ፈጻሚዉ ጋር በተያያዘ ማንኛውንም የመለያ ዝርዝሮች፣ ጥቃቱ የተፈጸመበት ቀንና ጊዜ፣ እና ሌሎች መረጃዎችን ማካተት አለበት።

5) ጥቆማው የቀረበለት ኃላፊም ይህን መረጃ ለመመዝገብ በተዘጋጀ ቅፅ ላይ በአግባቡ መመዝገብ አለበት።

## 8. የሕፃን የዳሰሳ ጥናት

1) በማህበረሰብ አቀፍ ጥምረት ውስጥ የሚገኝ የጉዳይ ሠራተኛ ወይም የሕፃን ጥበቃ ባለሙያ የስጋት ዳሰሳን ያካተተ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ ይኖርበታል፡፡

2) የዳሰሳ ጥናቱ ሕፃኑ ሊከሰት በሚችል አደጋ ውስጥ መሆኑ ወይም የተባለው ወንጀል ሰለባ መሆኑን ካሳየ የጉዳይ ሠራተኛው ወይም የማህበረሰብ አቀፍ ጥምረቱ ለሕፃን ጥበቃ ባለሙያው ወይም ለሴቶች፣ አግባብነት ላላቸው ቢሮዎች ወዲያውኑ የማሳወቅ፤ የሕፃኑን ደህንነት ለማስከበርም አፋጣኝ እርምጃዎችን የመውሰድና ሕፃኑ ላይ አካላዊ ጥቃት፣ ብዝበዛ ወይም ወሲባዊ ጥቃት ተፈጽሞበት ከሆነ ሕፃኑ ከጥቃት ፈጻሚዉ ጋር ግንኙነት እንዳይኖረው የማድረግ ሃላፊነት አለበት፡፡

3) የዳሰሳ ጥናት ውጤቱ ሕፃኑ በተንከባካቢው ስር ሆኖ መቆየት እንደሌለበት አመላካች ሆኖ ከተገኘ የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያው ወይም አግባብነት ያለው ቢሮ ሕፃኑ ወደ ሌላ የአማራጭ ክብካቤ እንዲዛወር ለፍርድ ቤት አቤቱታውን ማቅረብ አለበት፡፡

4) የዳሰሳ ጥናቱ ብሄራዊ የሕፃናት ጥበቃ ጉዳይ አያያዝ ማዕቀፍ ውስጥ በተቀመጡት የጉዳይ አያያዝ ሂደቶች መሠረት መካሄድ አለበት። የጉዳይ ሠራተኞች የዳሰሳ ጥናቱን በሚያካሂዱበት ጊዜ የሚከተሉትን ጉዳዮች በተጨማሪ ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል።

   ሀ) በሕፃኑ አካል፣ ሥነ-ልቦና ወይም በስሜቱ ላይ ጉዳትን ሊያደርስ የሚያስችል የተፈጠረ ክስተትን፣

   ለ) ሕፃኑ በዳሰሳ ጥናቱ ወቅት አደጋ ላይ ባይሆንም በሕፃኑ ላይ ጉዳት ሊደርስ እንደሚችል የሚያመላክቱ የስጋት ምክንያቶች መኖራቸውን፣

   ሐ) በሕፃኑ ላይ ቀደም ብሎ የተከሰተ ጉዳት ስለመኖሩ፣

   መ) ሕፃኑ ከቤተሰብ ሳይለይ ለቤተሰቡ ጥበቃና አቅም ማጎልበት አገልገሎቶችን ወይም ከሌሎች አገልገሎት ሰጪ ተቋማት ጋር በማገናኘት የምክር፣ የማስማማት እንዲሁም ቤተሰቡን ከመበተን የሚታደጉ የቅድመ መከላከል አገልግሎቶች ፣ የቤተሰብ መልሶ ግንባታ እና የችግር አፈታት አገልግሎቶችን እንዲያገኝ ስለመደረጉ፣

   ሠ) ሕፃኑ በጊዜያዊ አማራጭ ክብካቤ ወይም በአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ በማቆየት ለቤተሰቡ የጥበቃና የማብቃት አገልገሎቶችን ማመቻቸት የሕፃኑን ጉዳት ላይ የመውደቅ ስጋትን ስለመቀነሱ፣

   ረ) ሕፃኑ በአማራጭ ክብካቤ ውስጥ የሚመደብ ከሆነ ከላይ ታሳቢ እንደተደረገው ሕፃኑን በቤተሰብ ተኮር የአማራጭ ክብካቤ ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ ለመመደብ ሁሉም ጥረቶች ስለመደረጉ፣ አግባብነት ያለው ቢሮ ወይም የሕፃን ጥበቃ ባለሙያው ሕፃኑን በዚህ ዓይነት አገልግሎት ውስጥ ሲመድብ ከ6 ወር ላልበለጠ ጊዜ መሆን እንዳለበት ታሳቢ በማድረግ ስለመመቻቸቱ፣

   ሰ) የዳሰሳ ጥናቱ ግኝቶችና ውሳኔዎች መነሻ ምክንያቶች በአግባቡ ስለመመዝገባቸው እና ሰነዶቹ ስለመደራጀታቸው፡፡

5) ጉዳዩን በመጀመሪያ የሚይዘው አካል ህጻኑን ለፖሊስ፣ ለጤና ተቋም እና ለሚመለከተው የመንግስት አካል ሲያቀርብ የህጻናት ጉዳይ አያያዝ ማእቀፍን መሰረት በማድረግ መፈጸም ይኖርበታል፡፡

6) የጥቃት ሰለባ የሆኑ ሕፃናት ሕክምናና ሌሎች ተገቢ እንክብካቤዎችን በፍጥነት ማግኘት ይኖርባቸዋል። በተለይ ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሕፃናት በ24 ሰዓት ጊዜ ውስጥ እርዳታውን ማግኘት ይኖርባቸዋል።

## 9. ሕፃናት ከክብካቤ ሊወጡ ስለሚችሉበት ሁኔታ

1) አንድ ህጻን ባለበት ክብካቤ ውስጥ አስቸኳይ የጥበቃ አገልግሎት የሚያስፈልገው ሆኖ ሲገኝ እና ሕፃኑን ካለበት ክብካቤ አዉጥቶ ወደ ጊዜያዊ ክብካቤ ለመመደብ የፍርድ ቤት ትእዛዝ ማውጣት ጊዜ የሚፈጅ ሲሆን ለተጨማሪ አደጋ እንዳይጋለጥና የህጻኑን ጥቅምና ደህነት ለማስጠበቅ ሲባል አግባብነት ያለው ቢሮ ከፖሊስ ጋር በመሆን ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ሕፃኑን ካለበት ክብካቤ በአስቸኳይ ማስወጣት ይችላሉ።

2) አግባብነት ያለው ቢሮ ህጻናት ጥቃትና ቸል መባል የተፈጸመባቸዉን ስለመሆኑ ጥቆማ ሲደርሰው ከፖሊስ ጋር በተባበር ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ሕፃኑ ወደሚገኝበት ቦታ በመግባት ሕፃናኑ ካሉበት ክብካቤ የማዉጣት ተግባር መፈጸም ይችላሉ።

3) ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ጥቃት ወይም ቸል የመባል ጥቆማ እንደተደረገ የሕፃኑን ደህንነት ለመወሰን በክፍል አሥራ አንድ በተጠቀሰው የጉዳይ አያያዝ ሂደትና መሠረት አግባብነት ያለው ቢሮ የቅበላ ማጣሪያ በማካሄድ በሕፃኑ ላይ አፋጣኝ ምላሽ የሚፈልግ ስጋት ካገኘ የሥጋት ዳሰሳ ጥናት መካሄድ የሕፃኑን ደህንነት ለማስጠበቅ የቤተሰብ አቀፍ ክብካቤን ቀዳሚ ምርጫ በማድረግ ወደ ሌላ አማራጭ ክብካቤ ለመመደብ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት። ሕፃናት በማንኛውም የአማራጭ ክብካቤ ውስጥ ሲመደቡ በዚህ መመሪያ ክፍል ሰባት ስር ከተጠቀሱት የአማራጭ ክብካቤ አይነቶች የጊዜ ገደብ በላይ በክብካቤው ውስጥ መቆየት የለባቸውም።

4) የመነሻ ዳሰሳ ጥናቱ የወንጀል ነክ ጉዳይና በሕፃኑ ላይ አፋጣኝ ምላሽ የሚፈልግ ስጋት አለመሆኑን ነገር ግን ሕፃኑ ተጋላጭና አገልግሎቶች የሚያስፈልገው መሆኑ ከተረጋገጠ አግባብነት ያለው ቢሮ ወይም የህጻናት ጥበቃ ባለሙያ ክትትል አያደረጉበት ችግሩ በማህረሰብ አቀፍ ጥምረት በኩል እንዲፈታ ይረጋል፡፡ ክብካቤን ለማቋረጥ ስለሚቀርብ ማመልከቻ።

## 10. ክብካቤን ለማቋረጥ ስለሚቀርብ ማመልከቻ

1) ሕፃናት ሊከሰትባቸው በሚችል የጉዳት ሥጋት ምክንያት በአስቸኳይ ወደ ሌላ አማራጭ ክብካቤ መዛወር ሲኖርባቸው ዝውውሩን የሚያካሂደው አካል ለሕፃኑ ቤተሰቦች ወይም ተንከባካቢዎች በ24 ሰዓት ውስጥ ማሳወቅ ይኖርበታል።

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ህጻኑን ወደ ሌላ አማራጭ የማዘዋወሩ ሂደት የሕፃኑ ጥቅምንና ደህንነትን የሚጎዳ ሆኖ ሲገኝ ሕፃኑ ያለበት ስፍራ መገለጽ የለበትም።

3) የሕፃናት በአስቸኳይ ወደ ሌላ አማራጭ ክብካቤ መዘዋወር በተፈጸመ በ48 ሰዓታት ውስጥ አግባብነት ያለው ቢሮ ዝርዝር ማስረጃዎችን በማቅረብ በፍርድ ቤት እንዲረጋገጥ ያደርጋል፡፡

4) ዝዉውሩ በፍርድ ቤት የታዘዘ ሲሆን፣ ጉዳዩን እንዲይዝ የተመደበዉ የጉዳይ ሠራተኛ በዚህ መመሪያ መሰረት የመጨረሻ ግቡ ሕፃኑን ከቤተሰቡ ጋር መልሶ ማቀላቀል ወይም በሌላ አማራጭ የቤተሰብ ተኮር ወይም ማህበረሰብ አቀፍ ክብካቤ ውስጥ መመደብ እንዲችል የሚያደርግ የጉዳይ አያያዝ ሂደትን ማከናወን ይኖርበታል።

5) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7(1) መሠረት ጥቃት ወይም ብዝበዛ ስለመፈጸሙ ጥቆማ የመቀበል ሃላፊነት የተሰጣቸው አካላት፣ በጥቆማው መሰረት እርምጃ ባለመውሰዳቸው በህጻናቱ ላይ ለሚደርስ ጥቃት አግባብነት ባላቸው ሌሎች ህጎች በወንጀል ወይም በአስተዳደር ተጠያቂ ይሆናሉ።

## ክፍል ሶስት

## ቅንጅታዊ አሰራር

### 11. ብሔራዊ ግብረ ኃይል

1) የሕፃናትን ጉዳይ በሚመለከት በቅንጅት የሚሰራ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (3) የተመለከቱትን ተቋማት በአባልነት የያዘ ብሔራዊ ግብረ ኀይል በዚህ መመሪያ ተቋቁማል ።
2) ግብረ ኃይሉ በዕቅድ፣ በፋይናንስ እና ቅንጅታዊ አሰራር ላይ ክትትል የማድረግ፣ የሕፃናት መብትን የተመለከቱ ክንውኖችን የማቀናጀት እንዲሁም ከሕፃናት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን አስመልክቶ ሚኒስቴሩን የማማከር ኀላፊነት ይኖረዋል።
3) ብሔራዊ ግብረ ኃይሉ በሚኒስቴሩ የሚመራ ሲሆን በሚዘጋጀው የአሰራር ሥነ-ሥርዐት መሰረት አግባብነት ያላቸውን የመንግሥት ተቋማትን፣ ብሔራዊ የሕፃናት ፓርላማ፣ የሲቪል ማኀበራት ድርጅቶችን እና እንደ አስፈላጊነቱ ቴክኒካዊ ሥልጠናን የሚሰጡ የትምህርት ተቋማት በብሔራዊ ግብረ ኃይሉ በአባልነት ሊካተቱ ይችላሉ።
4) ብሔራዊ ግብረ ኃይሉ የአማራጭ ክብካቤ ተግባራዊ መሆኑን የሚከታተል የቴክኒክ ሥራ ቡድን በተለያየ የሙያ ዘርፍ ሊያቋቁም ይችላል።

### 12. የአማራጭ ክብካቤ የቴክኒክ ቡድን

1) በሚኒስቴሩ ስር የሚመራ ዘርፈ ብዙ አማራጭ የሕፃናት ክብካቤ ቅንጅቶችን የሚያስተባብር እና የሚቆጣጠር የአማራጭ ክብካቤ የቴክኒክ ቡድን ይቋቋማል።

2) የቴክኒክ ቡድኑ በፌደራል ደረጃ ያሉ የሚመለከታቸውን የመንግሥት አካላትንና የሲቪል ማኀበራትን በአባልነት የሚያካተት ይሆናል፡፡

3) የቴክኒክ ቡድኑ ተግባርና ኃላፊነት በሚዘጋጀው የአሰራር ሥነ-ሥርዐት የሚወሰን ይሆናል።

## ክፍል አራት

## የአማራጭ የሕፃናት ክብካቤ የሚሰጡ አካላት ኃላፊነት

### 13. የመንግሥት ተቋማት ኃላፊነት

1) የሚኒስቴሩ ሃላፊነት፣

ሀ) የዚህን መመሪያ አፈጻጸም የመከታተልና የመቆጣጠር፣

ለ) ብሔራዊ ግብረ ኃይሉንና የቴክኒክ ሥራ ቡድንን የማስተባበርና የመምራት፣

ሐ) ቅንጅታዊ አሰራርን ለማጠናከር በህግ የሕፃናት ጥበቃ ለማድረግ ሥልጣን ከተሰጣቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ጋር በትብብር የመስራት፣

መ) አገልግሎት ሰጪ ተቋማት፣ በሕፃናት ጥበቃ፣ ጉዳይ አያያዝ፣ እንዲሁም በዚህ የአማራጭ ክብካቤ መመሪያ ላይ ያላቸውን የተሳትፎ፣ የትብብር፣ የክትትልና የቁጥጥር ድርሻና ሃላፊነት፣ እንዲሁም የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓትን የሚያሳዩ ግልጽና ደረጃዉን የጠበቀ የአሰራር ሂደት (ኤስ.ኦ.ፒ) የማዘጋጀት፣

ሠ) የፖሊሲ ውሳኔዎችን ለሚመለከታቸው አግባብነት ላላቸው ቢሮዎች የማስተዋወቅ ስራ የመስራት፣

ረ) ለአማራጭ የሕፃናት ክብካቤና ድጋፍ አገልግሎት የተመደቡ ሀብቶችንና በጀት አጠቃቀም የመከታተልና የመቆጣጠር፣

ሰ) የአማራጭ የሕፃናት ክብካቤ እና የጉዳይ አያያዝና ጉዳዮችን አፈጻጸም በኃላፊነት የመከታተል፣

ሸ) የአማራጭ የሕፃናት ክብካቤ አገልግሎት የሚሰጡ አካላት በሰው ኃይል እንዲጠናከሩና ትኩረት እንዲሰጣቸው የማድረግ፣

ቀ) የአማራጭ ሕፃናት ክብካቤ መመሪያ አፈጻጸም እና የቅንጅት ክፍተቶችን የመለየት እና መፍትሄ የመስጠት፣

በ) በሕፃናት ጥበቃና አማራጭ የሕፃናት ክብካቤ ላይ የመረጃ አያያዝ ሥርዓትን በመዘረጋት ከሕፃናት ጥበቃ፣ ከአማራጭ ክብካቤና የጉዳይ አያያዝ ጋር የተያያዘ መረጃን ለመከታተል እና ለመተንተን ከሌሎች ዘርፎች ጋር በቅንጅት የመስራት፣

ተ) የሕፃናት ጥበቃ እና አማራጭ የሕፃናት ክብካቤ ሥርዓትን ለማጠናከር የሚስችል ተከታታይነት ያለው እቅድ በማውጣት አገልግሎቶቹ በተገቢው መንገድና በተቀናጀ ሁኔታ እንዲፈጸሙ የማድረግ፣

ቸ) ወላጆቻቸው በወንጀል ተጠርጥረው ወይም በፍርድ በማረምያ ቤት እዲቆዩ የተደረጉ ሕፃናትን በተመለከተ ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤት የሕፃናቱን ጥቅም መሰረት በማድረግ በዚህ መመሪያ ከተቀመጡት አማራጭ የሕፃናት ክብካቤ ዘዴዎች በአንዱ ተጠቃሚ እንዲያደርጉ ትእዛዝ ከሰጠ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያላቸው ቢሮዎች ትእዛዙን ተፈጻሚ የማድረግ።

2) የሕፃናት ጥበቃ እና የአማራጭ ክብካቤ ተጨማሪ አገልግሎቶችን የሚሰጡ ሌሎች የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ አካላት ፖሊስ፣ ጤና፣ ትምህርት፣ ትራንስፖርት እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ተቋማት በሚዘጋጁት የአሰራር ሥርዓት (ኤስ.ኦ.ፒ) ወይም የመግባቢያ የስምምነት ውሎች ውስጥ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማካተት አለባቸው፡-

ሀ) ተጋላጭ የሆኑ ወይም ክብካቤና ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው ሕፃናትን መለየት እና ማሳወቅ፣

ለ) የሕፃናት ጥበቃ ጉዳዮችን እንዲሁም የቤተሰብ ተኮር ክብካቤን በተመለከተ በማኅበረሰብ ደረጃ ግንዛቤን ማስጨበጥ እና ሃላፊነት ወስዶ የማስተዋወቅ፣

ሐ) ከማኅበረሰቡ ሐብቶችን በማሰባሰብ ተጋላጭ የሆኑ ሕፃናትን እና ቤተሰቦችን የመደገፍ፣

መ) የሕፃናት ጥበቃ ጉዳዮችንና እና የተለየ ትኩረት የሚሹ ሕፃናት ፍላጎቶችን በተመለከተ አግባብነት ካላቸው ቢሮ ወይም ከሕፃናት ጥበቃ ባለሙያ ጋር በቅርበት የመስራት፣

ረ) የተለያዩ ችግሮችን ለመከላከል የግንዛቤን ማስጨበጥ እንዲሁም አጠቃላይ መፍትሄ ለሚሹ ችግሮች ማህበረሰባዊ መፍትሄ እንዲሰጣቸው የመስራት፣

ሰ) የማኅበረሰብ አቀፍ የክብካቤ አማራጮችን የማስገንዘብ፣

ሸ) ሕፃናትን እና ቤተሰብን በማኅበረሰብ ዉስጥ በሚካሄዱ ኩነቶች ውስጥ የማሳተፍ፣

ቀ) ሕፃናትን ወደ ቤተሰብ እና ማኅበረሰብ የመቀላቀል እና የማዋሃድ ተግባራትን የማከናወን፡፡

## 14. አገልግሎት ሰጪ ተቋማት

1) አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚባሉት፡-

ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ ተገቢው ፈቃድ እና እውቅና የተሰጣቸው እንዲሁም በሚዘጋጁ የሕፃናት የአማራጭ ክብካቤ አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያዎች መሠረት አንድ ወይም ከዚያ በላይ አገልግሎቶችን የሚሰጡ ድርጅቶች፣ ወይም

ለ) ማኅበራዊና ባሕላዊ ተቋማት፣ ወይም

ሐ) በአንድ ወይም ከአንድ በላይ የዚህ መመሪያ ክፍሎች ተግባራዊ የሚሆንባቸው የመንግሥት ተቋማት ወይም ሌሎች ህጋዊ አገልግሎት ሰጪዎች ናቸው።

2) የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት በዚህ መመሪያና ሌሎች አግባብነት ባላቸው የኢትዮጵያ ሕጎች መሠረት ሕጋዊ ምዝገባ ማካሄድና ዕውቅና ማግኘት አባቸው።

3) የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለሕፃናትና ለቤተሰቦች አገልግሎት እንዲሰጡ ሥልጣን የተሰጣቸው የመንግሥት ድርጅቶች ወይም የስራ ክፍሎች ሊሆኑ ይችላሉ።

4) የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሕፃናትን ፍላጎት በብቃት የማሟላት አቅም እና ግብአት ሊኖራቸው የሚገባ ሲሆን ሠራተኞቻቸው ተገቢ የሆነ ስልጠና ማግኘታቸውን እና የብቃት መስፈርቶችን ማሟላታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

5) አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሕፃናት ደህንነት እና ዕድገት መጠበቁን ለማረጋገጥ የሕፃናት ክብካቤን እና ጥበቃ ወይም አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚያስችሉ መስፈርቶችንና የአሰራሮች ስነ-ስርዓቶችን የተሟሉ መሆኑንና ብቃት ያላቸውና ከህጻናቱ ቁጥር ጋር የተመጣጠነ ሠራተኞች ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው።

6) አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በመዋቅራዊና ከዚያም ባሻገር ራሳቸዉን ችለዉ መስራት መቻላቸዉን ማረጋገጥ፣ የሠራተኞች ስምሪትን፣ የሚሰጡ አገልግሎቶች እና በየጊዜው የሰራተኞችን የስልጠና ፍላጎቶች እያጠኑ ሊያሟሉ የሚችሉበት የስራ ዕቅድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

7) አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አገልግሎት በሚሰጡበት ጊዜ የሚከተሉትን የሥነ-ምግባር መርሆዎች መከተል ይኖርባቸዋል፤

ሀ) **በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ስምምነት፡-** በህግ ስምምነታቸውን ለመስጠት የተፈቀደላቸው ሕፃናት ወይም ታዳጊዎች በማንኛውም የድጋፍ ፕሮግራሞች ውስጥ ስለሚኖራቸው ተሳትፎ፣ በሚደረግላቸው ድጋፍ ሊኖሩ ስለሚችሉ ለውጦች ሙሉ እውቀት ኖሯቸው ስምምነታቸውን መስጠት አለባቸው።

ለ) በሕግ ስምምነት መስጠት የማይችሉ ሕፃናት ስምምነታቸውን በቤተሰባቸው ወይም በተንከባካቢዎቻቸው መስጠት እና የሕፃኑ አስተያየትና ፍላጎቶች ማንጸባረቅ ይኖርበታል።

ሐ) **ምሥጢርን መጠበቅ**፡- አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ማናቸውንም አገልግሎት ሲሰጡ የሕፃኑን ምሥጢር የመጠበቅ፣ በሕፃናትና በቤተሰቦቻቸው የተሰጡ መረጃዎችን ያለ ሕፃኑ ወይም ቤተሰቡ እውቅናና ስምምነት ለማይመለከታቸው ሰዎች መስጠት የለባቸውም።

መ) **ተጠያቂነት**፡- ሁሉም አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የጉዳይ አያያዝ ሂደቶችን በሚገባ የመከተል እና የተሰሩ ስራዎችን በቅርበት የመከታተልና የመገምገም ኀላፊነት አለባቸው።

ሠ) **ጥንካሬ ላይ የተመሰረተ አገልግሎት፡-** የሚሰጡ አገልግሎቶች ሕፃናት በተፈጥሮ ያላቸውን ችግርን የመቋቋም ችሎታቸውን እንዲሁም በቤተሰብ እና በማህበረሰብ ውስጥ ያላቸውን የድጋፍ ዘዴዎችን የመገንባት፣ ሊከሰት የሚችል ሥጋትንና የመከላከል አቅማቸውን የመዳሰስ፣ የተጋላጭነት ተጽዕኖን መቀነስ እንዲሁም አዎንታዊ ዕድገታቸውን የሚያጎለብቱ ተጨማሪ ተሞክሮዎችን መስጠትን ግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ፣ በተጨማሪ ለህፃናትና ታዳጊዎች የሚሰጡ የሥነ-ልቦና እና የማኅበራዊ አገልግሎቶች አቅማቸውን እንዲያዳብሩ እና ሙሉ በሙሉ መጠቀም እንዲችሉ የማድረግ ሃላፊነት አለባቸው።

ሠ) **የተሟላ ፍላጎቶች**፡- አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚሰጧቸው አገልግሎቶቻቸው ሕፃን ተኮር፣ ዕድሜያቸውን ያማከሉ እና ከሕፃናቱ ሁለንተናዊ ፍላጎቶች አንጻር የተዘጋጁ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

ረ) **በማስረጃ ላይ የተመሰረተ አገልግሎት፡** አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የክብካቤ እና የጥበቃ ፍላጎቶች የላቸውን ሕፃናት ለመድረስ ያለሙ አገልግሎቶቻቸው በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ መሆናቸውን የማረጋገጥ፣ የፕሮግራም እንቅስቃሴዎችን እና አገልግሎቶችን በተገኙ መረጃዎች ላይ መሰረት በማድረግ ማዘጋጀት እንዲሁም በክትትል እና በመረጃ መሰብሰብ ላይ ትኩረት በማድረግ የሚገኙ መረጃዎችን አገልግሎት አሰጣጥ ዘዴዎችን ለማሻሻል ጥቅም ላይ ማዋል አለባቸው።

8) አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚከተሉትን ተግባሮች ማከናወን ይኖርባቸዋል፣

ሀ) ከመንግሥትና ከማህበረሰቡ አጋሮች ጋር በመሆን የሚሰጡትን አገልግሎት የማቀናጀት፣

ለ) ተጨማሪ ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው ሕፃናትን በመለየት ወደ የሚመለከተው ባለድርሻ አካል የማስተላለፍ፣

ሐ) የምክር፣ የሥነ-ልቦናና የማህበራዊ አገልግሎቶች፣ በፍላጎታቸው ወይም ያለፍላጎታቸው በመዛወር ላይ የሚገኙ ሕፃናትን መልሶ የማቀላቀል፣ የሕፃናትን ጥቅምና ደህንንትን የመወሰን፣ የጤና አገልግሎቶችን ለመስጠት፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመቀነስ፣ ከቤተሰብ ክብካቤው ውጪ ለሚኖሩ ሕፃናት የድጋፍ አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚያስችሉ ዘርፈ ብዙ የሆኑ ልዩ አገልግሎቶችን የመስጠት፣

መ) ማረፊያ ለሚፈልጉ ሕፃናት ደህንነቱ የተጠበቀ ጊዜያዊ መጠለያ የማዘጋጀት፣

ሠ) በሕፃናት መብት ጥበቃ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎችን በበቂ ሁኔታ የማቅረብ፣

ረ) በየደረጃው የሚገኙ የሕፃናት ድጋፍ የሚሰጡ የመንግሥት አደረጃጀቶችን አቅም መገንባት፣

ሰ) በሕፃናት ጥበቃ ጉዳዮች ላይ ቅስቀሳ ማድረግና ግንዛቤን የማሳደግ፣

ሸ) አማራጭ የሕጻናት ድጋፍና ክብካቤን ለመደገፍ ሃብት ማሰባሰብ፣

ቀ) በድንገተኛ ሁኔታዎች ውስጥ ላሉ ሕፃናት የድጋፍ አገልግሎቶችን የመስጠት።

9) የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚቀጥሯቸው የማህበራዊ ሠራተኞች እና የጉዳይ ሥራ አስኪያጆች የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡-

ሀ) በማኅበራዊ ሳይንስ የትምህርት መስክ በሶሻል ወርክ፣ በሶሺዮሎጂ፣ በሳይኮሎጂ ወይም በሕግ የመጀመሪያ የዩኒቨርሲቲ ዲግሪ ያላቸው እና በሕፃናት ጥበቃ የሥራ ልምድ ወይም እውቅና ካለው ተቋም ሥልጠና የወሰደ መሆኑን፣

ለ) መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ባልሆነ ድርጅት ውስጥ በሕፃናት ጥበቃ ፕሮግራም ላይ ቢያንስ ከ 2 እስከ 5 ዓመት የሥራ ልምድ ያላቸው እንዲሁም ለሌሎች ስልጠና የመስጠት፣ የመረጃ አያያዝ፣ ክትትል እና ግምገማ የማካሄድ ክህሎትን ያዳበሩ መሆኑን፣

ሐ) በሕፃናት ጥበቃ እና የአማራጭ ክብካቤ ዙርያ መደበኛ ሥልጠና መውሰዳቸውን፣

መ) ጥሩ የተግባቦት ክህሎት ያላቸው መሆኑን፣

ሠ) የሕፃናትን እና የቤተሰቦቻቸውን ተፈጥሯዊ ክብር እና ሊሰጣቸዉ የሚገባውን ቦታ ወይም ዋጋ የማክበር እንዲሁም ያላቸውን ግለሰባዊ እና የባህል ልዩነቶች የማጤን ችሎታ እንዳላቸው፣ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

## 15. ቀጥተኛ ያልሆነ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት

1) በቀጥታ ለህጻናት አገልግሎት የማይሰጡ ተቋማት ከአማራጭ ክብካቤ አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ተግባራት ሊያከናውኑ ይችላሉ፣

ሀ) በተወሰኑ ዘርፎች ውስጥ ለሚደረግ የፖሊሲ ቀረጻ ሙያዊ አስተዋፅኦ የማድረግ፣

ለ) ለቅስቀሳ ስራዎች አስተዋጾ የማድረግ፣

ሐ) ሃብት የማሰባሰብ እና ለአገልግሎት አቅራቢዎች የገንዘብ ድጋፍ የማድረግ፣

መ) በፅንሰ-ሀሳብ እና በመተግበር ረገድ ቴክኒካዊ ድጋፍ የመስጠት፣

ሠ) በተለያዩ ምክንያቶች ወላጆቻቸውና ተንከባካቢያቸውን ያጡ የስደተኛ ሕፃናትን ጉዳይ ለብሔራዊ የቅብብሎሽ ሥርዓት የመምራት ተግባራትን ሊያከናውኑ ይችላሉ፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለበጎፈቃደኞች እና ጎብኚዎች

### 16. በበጎ ፈቃደኞች የሚሰጥ አገልግሎት

1) በጎ ፈቃደኛ ማለት በዚህ መመሪያ ውስጥ በተገለጹ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ወይም የተቋማዊ አገልግሎት ሰጪ ድረጅቶች ውስጥ ያለክፍያ ጊዜውን፣ ክህሎቱን እና ሐብቱን የሚሰጥ ሰው ነው።

2) ማንኛውም አገልግሎት ሰጪ ተቋም ወይም ተቋማዊ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለመስጠት የመጡ በጎ ፈቃደኞችን ወይም ጎብኚዎችን ስም፣ አድራሻ እና የጉብኝታቸውን ዓላማ በጎብኚዎች መዝገብ ላይ መመዝገብ አለበት።

3) በጎ ፈቃደኞች ለአገልግሎት ሰጪ ወይም ለተቋማዊ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መስጠት የሚችሉት አግባብነት ካለው ቢሮ ወይም የመንግሥት መስሪያ ቤት በጽሑፍ የተሰጠ ፈቃድ ሲኖራቸው ብቻ ነው። ይህም ፈቃድ የሚከተሉት ማስረጃዎች ተሟልተው ሲቀርቡ ብቻ የሚሰጥ ይሆናል፡-

ሀ) የትምህርት ማስረጃ፣ የሥራ ልምድ ዝርዝር እና ማመልከቻ፣

ለ) ከአመልካቹ ጋር ዝምድና የሌላቸው የበጎ ሥነ ምግባር ምስክርነት ሊሰጡ የሚችሉ የሁለት ምስክሮች ስም እና አድራሻ፣

ሐ) ከሕፃናት ክብካቤ፣ ድጋፍ፣ ክህሎት ማዳበር እና ትምህርት ጋር ተያያዥነት ያለው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ፣

መ) ለኢትዮጵያ ዜጎችና ነዋሪዎች ከወንጀል ነጻ መሆናቸውን የሚረጋግጥ ማስረጃ፡፡

4) ከላይ ከተጠቀሱት ማስረጃዎች በተጨማሪ በጎ ፈቃደኞች ወይም ጎብኝዎች የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው ሲሆኑ የሚከተሉትን ማስረጃዎች የማቅረብ ሃፊነት አለባቸው፡-

ሀ) አመልካቹ ዜግነት ካገኘበት ሀገር ወይም ላለፉት 10 አመታት በመደበኛነት ከሚኖርበት ሀገር ወይም በበጎ ፈቃደኝነት ካገለገለበት ሀገር ከወንጀል ነጻ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፣

ለ) የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን ለመስጠት ወደ ኢትዮጵያ በሕጋዊ መንገድ ስለመምጣቱ ከሚመለከተው ባለሥልጣን የተሰጠ ማረጋገጫ፣

ሐ) የሕክምና መድን ሽፋን ማረጋገጫ፡፡

5) አንድ በጎ ፈቃደኛ በተቋማዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ውስጥ ለማንኛውም ሕፃን ቀዳሚ ተንከባካቢ መሆን ወይም በተቋሙ ውስጥ ካለ አንድ ሕፃን ጋር ብቻ የጠበቀ ቁርኝነት ሊኖረው አይገባም።

6) አንድ በጎ ፈቃደኛ በተቋማዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰራተኞችን ከማገዝ ያለፈ ለሕፃናት በቀጥታ ኃላፊነት መውሰድ አይችልም።

7) የተቋማዊ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ለሕፃናት ክብካቤ ከመስጠት ተግባራትን ከማከናወን በተጨማሪ በጎ ፈቃደኞች ያላቸውን ሚና እና ኃላፊነቶች የማሳወቅ ኃላፊነት አለባቸው።

8) በጎ ፈቃደኞች በበጎ ፈቃደኝነት የማገልገል ዕድልን ለማግኘት ማመልከት እና በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት በሚያዘጋጁት የበጎ ፈቃደኞች ተግባራት በግልጽ በሚዘረዝረው የበጎ ፈቃደኛ የአገልግሎት ውል መፈረም አለባቸው።

9) በጎ ፈቃደኞች የሥነ-ምግባር ደንብን እና የተቋማዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋሙን አገልግሎት፣ ብሄራዊ የሕፃናት ፖሊሲን እንዲያውቁ ከተደረገ በኋላ የስምምነት ሰነድ እንዲፈርሙ መደረግ አለበት።

## ክፍል ስድስት

## የክብካቤ ዘዴዎች አተገባበር ቅደም ተከተል

### 17. የክብካቤ ቅደም ተከተል ደረጃዎች

1) ይህ መመሪያ የሚከተሉትን የቤተሰብ፣ የማኅበረሰብ እና ተቋማዊ የክብካቤ ዘዴዎች ቅደም ተከተል እውቅና ይሰጣል፦

ሀ) የቤተሰብ ተኮር ክብካቤ

1) የቤተሰብ ጥበቃና አቅም ማጎልበት፣
2) መልሶ ማቀላቀል እና ማዋሃድ፣
3) የተቋጥሮ ዝምድና ክብካቤ፣
4) የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ፣
5) ጉዲፈቻ፣

ለ) የማኅበረሰብ አቀፍ ክብካቤ

1) ከድጋፍ ጋር ራስን ችሎ የመኖር

ሐ) የተቋማዊ ክብካቤ

## ክፍል ሰባት

## ቤተሰብ ተኮር ክብካቤ

### 18. የቤተሰብ ተኮር ክብካቤ አገልግሎት አይነቶች

1) ቤተሰብ ተኮር ክብካቤ ሕፃናት ምቹ በሆነ ሁኔታ ወጥነት ባለው እንክብካቤ በሚያገኙበት ቤተሰብ እና በሚደገፉበት ማህበረሰብ ውስጥ ለአጭር ወይም ለረዥም ጊዜ የሚመደቡበት የክብካቤ አይነት ሲሆን በዚህ ንኡስ ክፍል የቤተሰብ ጥበቃና አቅም ማጎልበት አገልግሎት፣ የመልሶ ማቀላቀል እና ማዋሃድ፣ የተቋጥሮ ዝምድና ክብካቤ፣ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ እና የጉዲፈቻ አገልግሎት አይነቶች እንዲካተቱ ተደርጓል።

## ንኡስ ክፍል አንድ
## የቤተሰብ ጥበቃና አቅም ማጎልበት

### 19. የቤተሰብ ጥበቃና አቅም ማጎልበት አገልግሎት ዓላማና ግብ

1) የቤተሰብ ጥበቃና አቅም ማጎልበት ወላጅን/ጆችን ወይም ሕጋዊ ሞግዚቶችን ወይም የተቋጥሮ ዝምድና ያላቸውን የቤተሰብ አባላትን ለሕፃናት ውጤታማ በሆነ መንገድ የተሻለ ክብካቤ መስጠት እንዲችሉ አቅማቸውን ማጎልበት የሚያስችል፣ የቤተሰብ መለያየት እንዳይከሰት እንዲሁም ህጻናትን በአማራጭ ክብካቤ የመመደብ ሥጋትን ለማስወገድ ያለመ የአገልግሎት አይነት ነው።

2) የቤተሰብ ጥበቃና አቅም ማጎልበት አገልግሎት ቤተሰብን ከመበተን፣ ሕፃናትን ከመጣል እና ቸል ከመባል ወይም ከቤተሰብ የመለየት አደጋ የሚታደጉ ዘርፈ ብዙ የድጋፍ አገልግሎቶችንና ስልቶችን የሚያካትት ነው፡ ፡

3) አገልግሎቱ የቤተሰብን ሕልውና የሚጠብቁ ድጋፎች መስጠትን፣ አቅም በማጎልበትንና ተጨማሪ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ማመቻቸትን እና ቤተሰቦችን በማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች በማቀፍ ሕፃናት ከቤተሰብ በመነጠል ወደ ሌሎች የአማራጭ ክብካቤ አገልግሎቶች እንዳይሄዱ ማገዝ፣ እንዲሁም ሕፃናት በከፍተኛ የደህንንነት ስጋት ውስጥ ሲገኙ የሕፃናቱን ጥቅምና ፈላጎት ቅድሚያ በመስጠት ሌሎች አስፈላጊ እና ተስማሚ አማራጭ ክብካቤዎችን እንዲያገኙ ያደርጋል።

4) የቤተሰብ ጥበቃና አቅም ማጎልበት አገልግሎት ለቤተሰብ ሁለንተናዊ ድጋፍ በመስጠትና ልዩ ልዩ ፍላጎቶቻቸውን በማሟላት ራሳቸውን እንዲችሉ ማድረግና ተግዳሮትን የመቋቋም አቅማቸውን ማጎልበት ይኖርበታል።

5) ወላጆቻቸውን በሞት ያጡ እና ለችግር የተጋለጡ ሕፃናት የአገልግሎት መስጫ መስፈረት እና የድጋፍ አገልግሎቶች በቤተሰብ ጥበቃና አቅም ማጎልበት አገልግሎት አሰጣጥ ውስጥ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

6) የቤተሰብ ጥበቃና አቅም ማጎልበት አገልግሎት ሕፃናት በቤተሰባቸው ውስጥ ደህንነታቸው ተጠብቆ ማደግ እንዲችሉ የሚያግዝ ዘዴ ሲሆን የቤተሰቡ አባላት ከሚኖሩበት ማህበረሰብ እና በበጎ ፈቃደኞች ድጋፍ አገልግሎቶች በሚሰጡ አካላት ሊደገፍ ይችላል።

7) በቤተሰብ ጥበቃና ማብቃት አገልግሎት የመስጠት ሂደት ውስጥ የቤተሰቡ እንዲሁም የሕፃኑ አመለካከት፣ ስጋት፣ ቀጣይ ተግባራት እና የህጻኑ የግንዛቤ ደረጃ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

## 20. የቤተሰብ ጥበቃና አቅም ማጎልበት አገልግሎት ተጠቃሚዎች

1) የቤተሰብ ጥበቃና አቅም ማጎልበት አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው መገኘት አለባቸው፡-

ሀ) በዜግነት ኢትዮጵያዊ የሆኑ፣

ለ) ለዚህ ድጋፍ አላማ ሕፃናትን የሚንከባከቡ ለችግር ተገላጭ የሆኑ ቤተሰቦች፣ የተቋጥሮ ዝምድና ያላቸው ቀዳሚ ተንከባካቢዎች ወይም ህጋዊ ሞግዚቶች ናቸው፡፡

2) ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ቤተሰቦች የሚባሉት፣

ሀ) አነስተኛ ወይም ምንም የገቢ ምንጭ የሌላቸው፣

ለ) የቤተሰቡን መሠረታዊ ፍላጎት ማሟላት የማይችሉ፣

ሐ) ቀዳሚ ተንከባካቢው የአካል ጉዳት ወይም በማይድን በሽታ የተያዙ፣

መ) የአካል ጉዳተኛ ወይም በማይድን በሽታ የተያዘ ሕፃንን የሚንከባከብ ቤተሰብ፣

ሠ) ለጥቃት እና ብዝበዛ ተጋላጭ የሆነ ቤተሰብ፡፡

3) የቤተሰብ ጥበቃ እና አቅም ማጎልበት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ወላጆቻቸውን ያጡ እና ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ሕፃናት የአገልግሎት አሰጣጥ መስፈርት ውስጥ የተጠቀሱትን እና ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የአገልግሎት አይነቶችን በቅንጅት መስጠት አለባቸው።

ሀ) የተመጣጠነ የምግብ አቅርቦት

ለ) መጠለያ

ሐ) የሕግ ከለላ

መ) የጤና እንክብካቤ

ሠ) ሥነ-ልቦናዊ እና ማኅበራዊ ድጋፍ

ረ) ትምህርት

ሰ) የገቢ ምንጭን ማሳደግ

4) የቤተሰብ ጥበቃና አቅም ማጎልበት አገልግሎት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን እና ሌሎች ተጨማሪ አገልግሎቶችን ሊያካትት ይችላል፡-

ሀ) የአካል ጉዳት ወይም ሥር የሰደደ የማይድን በሽታ ላለባቸው ሕፃናት የሚያስፈልግ ልዩ የድጋፍ አገልግሎት፣

ለ) አዎንታዊ የሕፃናት አስተዳደግ/ክብካቤ ድጋፍ አገልግሎት፣

ሐ) የሕፃናት ማቆያ ክብካቤ አገልግሎት፣

መ) ቤተሰቦችን ለድጋፍ እና እገዛ ከማኅበረሰብ መዋቅሮች ጋር ማገናኘት፡፡

## 21. የቤተሰብ ጥበቃና አቅም ማጎልበት አገልግሎት አሰጣጥ ዝቅተኛ መስፈርት

1) የቤተሰብ ጥበቃና አቅም ማጎልበት አገልገሎት ወላጆቻቸውን ያጡ እና ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ሕፃናት እና አገልግሎቶች አሰጣጥ መስፈርት መሰረት በማድረግ ተፈጻሚ ይሆናል።

2) አገልግሎቱ የሚያስፈልጋቸው ተጋላጭ ቤተሰቦች በአካባቢያቸው ለሚገኝ የመንግሥት አካል በማሳወቅ ወይም በጉዳይ ሠራተኛ ወይም በህጻናት ጥበቃ ባለሙያ ሊለዩና ወደ አገልግሎት ሰጪው ሊመሩ ይችላሉ።

3) በአንድ ቤት ውስጥ የሚገኙ ቤተሰቦች እንዲሁም ሕፃናት ልዩ ፍላጎቶቻቸውን እና ለአገልግሎቱ ብቁ መሆናቸውን ለመለየት የዳሰሳ ጥናት መደረግ ያለበት ሲሆን፣ የዳሰሳ ጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ የጉዳይ አያያዝ ቅጾችን በመጠቀም ሁሉንም የቤተሰብ አባላትን እንዲሁም ሕፃናትን ማካተት አለበት።

4) የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ከተለያዩ ተቋማት አገልግሎት በሚያገኙበት ወቅት የአገልግሎት ድግግሞሽን ለማስወገድ እንዲቻል የሚሰጡት አገልግሎቶች አግባብነት ባለው ቢሮ ወይም በሕፃን ጥበቃ ባለሙያው በሚሰየም የጉዳይ ሥራ አስኪያጅ በቅንጅት መመራት አለባቸው።

5) ለቤተሰቦች የሚሰጡ አገልግሎቶች ሁሉን አቀፍ ማለትም ማኅበራዊ፣ ሥነ-ልቦናዊ፣ የምክር አገልግሎት፣ የልጅ አስተዳደግ ክህሎት፣ ጥቃትና ሱስን የመከላከል፣ የተመጣጠነ አመጋገብ፣ የጤና ድጋፍ፣ መጠለያ፣ የገቢ ምንጭ ማጠናከርያ፣ የንግድ ሥራና የሙያ ክህሎት ሥልጠና እና ቅድመ መከላከል ላይ ያተኮሩና ምላሽ ሰጪ መሆን አለባቸው።

6) የጉዳይ ሰራተኞች የተለዩትን ልዩ ልዩ የቤተሰቡን ፍላጎቶች ለማሟላት የቅድመ ዳሰሳ ጥናቱን መሰረት በማድረግ የአገልግሎት አሰጣጥ እቅድ አገልግሎቱ የሚሰጣቸውን ቤተሰቦችና ሕፃናትን በማሳተፍ ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል።

7) የጉዳይ ሠራተኞች በሚያከናውኑት ወቅታዊ የቤት ለቤት ክትትል የሕፃናቱን አጠቃላይ ደህንነት እና ዕድገት መከታተል፣ በአገልግሎቱ ምክንያት የታዩ መሻሻሎችን መሰነድ እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ የአገልግሎት አቅርቦቱ ላይ ማሻሻያ ማድረግ አለባቸው።

8) የጉዳይ ሠራተኞች በቤተሰቡ ውስጥ በክትትል ወቅት የታዩ ለውጦች እና ሁኔታዎችን በክብካቤ ዕቅድ ውስጥ አካተው ማሳየት አለባቸው።

9) የጉዳይ ሠራተኞች ክትትል በሚያደርጉበት ጊዜ በሚኒስቴሩ የተዘጋጀውን የክትትል ቅጽ መጠቀም አለባቸው፡፡

10) የጉዳይ ሠራተኞች ከአገልግሎት ተጠቃሚዎች ጋር ድጋፍንና ማብቃትን መሰረት ያደረገ ግንኙነት መፍጠርና ማስቀጠል አለባቸው።

11) ሚኒስቴሩ፣ አግባብነት ያለው ቢሮ፣ የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያዎች እንዲሁም ሥልጣን የተሰጣቸው አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለቤተሰቦች የሚሰጥ ድጋፍን ማደራጀት እና ማመቻቸት አለባቸው።

12) በአገልግሎት አሰጣጥ ወቅት የሕፃናቱ እና የቤተሰቦቹ እሴቶች፣ አስተሳሰቦች እና እምነቶች ሊከበሩ ይገባል።

13) የጉዳይ ሠራተኞች የቤተሰቦችን አቅም ለማጎልበት እና ራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግ የጉዳይ አያያዝ ሂደቱ የቤተሰቡን ጥንካሬ እና ተግዳሮትን የመቋቋም ችሎታ ያማከለ መሆን አለበት።

14) ቤተሰቦች ተግዳሮትን የመቋቋም እና ክብካቤ የመስጠት ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ተገቢ የሆነ የልጅ አስተዳደግ እንዲሁም ሌሎች የሕይወት ክህሎት ሥልጠናዎችን ማግኘት አለባቸው።

15) የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ፍሎጎቶቻቸውን ለማሟላት በሚደረጉ በማንኛውም ውሳኔዎች እንዲሁም ደህንነታቸውን በጠበቀ ሁኔታ የአገልግሎት አሰጣጥ እቅድ ዝግጅትን ጨምሮ በሚኖራቸው አቅም ሁሉ እንዲሳተፉ መደረግ አለበት፡፡

16) አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎችን ተሳትፎ ለማበረታታት በሚመርጡት ቋንቋ የማስተርጎም፣ የልዩ ፍላጎት አገልግሎቶችን እንዲያገኙ የማድረግ እንዲሁም ባህላቸውን ያገናዘበና አክብሮትን የተላበሰ አገልግሎት የመስጠት ሀላፊነት አለባቸው።

17) የተፈጥሮ ወላጆች ወይም የተቋጥሮ ዝምድና ያላቸው ቤተሰቦች የሚንከባከቧቸው ሕፃናት ሊያጋጥሟቸው የሚችሉትን የክብካቤ እንዲሁም የደህንነት ጉዳዮችን በንቃት እንዲከታተሉ እና ምላሽ የመስጠት ሚና እንዲጫወቱ መበረታታት አለባቸው።

18) አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ የሆኑ ሕፃናት ወይም ቤተሰቦች የምግብ፣ መጠለያ፣ አልባሳት፣ ትምህርት፣ ጤና፣ ማኅበራዊ እገዛ፣ የሕግ ድጋፍ አገልግሎቶችን እና ኢኮኖሚያቸውን የማጎልበት ዕድሎችን እንደአስፈላጊነቱ ተደራሽ መሆናቸውን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለባቸው።

19) ሚኒስቴሩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ለቤተሰብ ጥበቃና ማብቃት አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃቸውን የጠበቁ የአፈጻጸም መተግበሪያ መስፈርቶችን ማዘጋጀት አለበት።

20) አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚሰጧቸው አገልግሎቶች ውጤታማነት የሚለካ፣ በጊዜ የተገደበ እና አገልግሎቱ በተሰጠበት የጊዜ ገደብ ውስጥ ቤተሰቦች ራሳቸውን ለመቻል መብቃታቸውን እንዲሁም የአገልግሎቱ ጥገኛ አለመሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

21) ማኅበረሰቡ በውስጡ የሚገኙትን ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ሕፃናት እና ቤተሰቦችን በመደገፍ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ሁኔታዎች ሊመቻቹላቸው ይገባል፡፡

## ንኡስ ክፍል ሁለት
## መልሶ ማቀላቀል እና ማዋሀድ

## 22. መልሶ ማቀላቀል እና ማዋሀድ

1) መልሶ ማቀላቀል አንድን ሕፃን ከቤተሰቡ ወይም ከቀድሞ ተንከባካቢው ጋር እንደገና በአካል ማገናኘት ሲሆን፣ ይህም በቋሚነት አብሮ መኖርን ኢላማ ያደረገ ነው።

2) የማዋሀድ አገልግሎት ማለት አንድን ከቤተሰብ ተለይቶ የቆየን ሕፃን ጥበቃና ክብካቤ ለማግኘት እና በሁሉም የሕይወት ዘርፍ የእኔነት ስሜት እንዲላበስ ወደ ቅርብ ወይም የተቋጥሮ ዝምድና ወዳላቸው ቤተሰብ እና ማኅበረሰብ የሚመለስበትና በቋሚነት አብሮ መኖርን ኢላማ የሚደረግ የሽግግር ሂደት ነው።

3) የማዋሀድ አገልግሎት ዓላማ የሕፃኑን ወይም ታዳጊውን አሁን ካለበት የክብካቤ ዓይነት ወደ ቤተሰብ ክብካቤ የሚደረግ ስኬታማ ሽግግርን ማረጋገጥ ነው።

4) አንድ የጉዳይ ሠራተኛ የመልሶ ማቀላቀል እና የማዋሃድ ተግባር ሲያከናውን ግልጽ ዓላማ እና ጥንቃቄ የተሞላበት የዳሰሳ ጥናት ምዘና እና በሕፃኑ ግላዊ ክብካቤ ዕቅድ የሚመራ ሂደት ማከናወን ያለበት ሲሆን፣ ይህም የሕፃኑን ዕድሜ፣ ፍላጎቶች፣ እያደጉ ያሉ ብቃቶች፣ ከቤተሰቡ የተለየበትን ምክንያቶችንና የወቅቱን አማራጭ ክብካቤ ምደባን ግምት ውስጥ በሚያስገቡ የክትትልና የድጋፍ ሥርዓቶች ታግዞ የሚካሄድ ይሆናል።

## 23. የመልሶ ማቀላቀልና ማዋሃድ ቅድመ ሁኔታዎች

1) ሕፃኑ እና ቤተሰቡ በተገቢው መንገድ መደገፍና ቀድመው ለሽግግር መዘጋጀት አለባቸው። ቅድመ ዝግጅቱም በጉዳይ ዕቅድ ዝርዝር ላይ መመስረት አለበት፡፡

2) ሕጻኑን መልሶ ለማቀላቀል ከሽግግሩ ምን መጠበቅ እንዳለበት ማስገንዘብን እና ለሂደቱም በቂ ጊዜ መመደብ አለበት፡፡

3) ቅድመ ዝግጅቱ በሕፃኑ እና በቤተሰቡ መካከል የቤት ወይም የቁርኝት ጉብኝቶችን ማካተት ያለበት ሲሆን፣ እነዚህ ጉብኝቶች በጉዳይ ሠራተኛው የሚታቀዱና ሕፃኑ ወደ ቤት ከመመለሱ በፊት የሚፈለገውን ድጋፍ ለመለየት የሚጠቅሙ እና የጉብኝቶቹ ድግግሞሽና ቆይታም እንደየጉዳዩ መወሰን አለበት፡፡

4) የጉዳይ ሠራተኞች ሕፃኑን ለመቀበል የሚደረገውን የቤተሰብና ሌሎች ከቤተሰቡ ጋራ የሚኖሩ አባላትን ዝግጅት ማገዝ አለባቸው።

5) በመልሶ ማቀላቀል ዝግጅት ወቅት ለቤተሰብ ዕይታዎች፣ ፍላጎቶች፣ ስጋቶች እና አመለካከቶች ተገቢው ክብደት መሰጠት አለበት፡፡

6) ሕፃናት እና ቤተሰቦች ፍላጎቶቻቸውን እና ችግር የመቋቋም ችሎታቸውን ሊያጠናክሩ በሚችሉ በተለያዩ አገልግሎቶች መደገፍ አለባቸው።

7) መልሶ የማቀላቀል አገልግሎት ከመሰጠቱ በፊት የቤተሰቡ አስቸኳይ ፍላጎቶች የሆኑትን አዎንታዊ የሕፃን አስተዳደግ፣ የቤት ንጽህና አጠባበቅ፣ ጤና፣ በሥነ-ልቦና ጉዳት ዙሪያ እና በመሳሰሉ ርዕሶች ላይ ስልጠናን መስጠትን ጨምሮ የምክር እና ተጨማሪ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ መደረግ አለበት፡፡

## 24. የመልሶ ማቀላቀልና ማዋሃድ አገልግሎት የሚከተላቸው ሂደቶች

1) መልሶ ማቀላቀልና ማዋሃድ የሚከተላቸው ሂደቶች በጉዳይ አያያዝ የአሰራር ስርዓት ማዕቀፍ እና ይህን መመሪያ ተከትሎ በሚወጣው የአሰራር ስነ-ስርዓት የሚያስቀመጣቸውን ዝርዝር አሰራሮች ተከትሎ መፈጸም አለበት፡፡

2) ሕፃኑ ወደ ቤተሰቡ ለመመለስ ፈቃደኛ ካልሆነ፣ ምክንያቶቹን በተጨባጭ በመገምገም የሕፃኑን ጥቅም እና ደህንነት ያማከለ ውሳኔ መሰጠት አለበት።

## 25. የመልሶ ማቀላቀልና ማዋሃድ አገልግሎት ከመከናወኑ በፊት መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

1) ማንኛውን ሕፃን መልሶ ከመቀላቀሉ በፊት የሚከተሉት ሁኔታዎች በቅድሚያ መረጋገጥ አለባቸው፡፡

ሀ) የሕፃኑ ቤተሰብ ተፈልጎ ከተገኘና ከተረጋገጠ፣

ለ) ሕፃኑ ከበተሰቡ የተለየበት ምክንያት ከታወቀ፣ መፍትሄ ከተሰጠባቸውና ችግሮቹ ስለመፈታታቸው ክትትል ከተደረገ በኋላ፣

ሐ) የሕፃኑ ቤተሰብ ሕፃኑን መልሰው ለመውሰድ ፈቃደኛ ከሆኑ፣ እንዲሁም ክብካቤ ለማድረግ በአዕምሮ እና በአካል ብቁ ከሆኑ፣

መ) ሕፃኑ ከቤተሰቦቹ ወይም የተቋጥሮ ዝምድና ካላቸው የቤተሰብ አባላት ጋር መልሶ ለመቀላቀል ፈቃደኛ ከሆነ፣

ሠ) ሕፃኑ ወደ ቤተሰብ መልሶ ለመቀላቀል ፈቃደኛ በማይሆንበት ጊዜ የሕፃኑ ምክንያቶች በተጨባጭ ተገምግመው የሕፃኑን ጥቅም እና ደህንነት ያማከሉ ውሳኔዎች ከተወሰኑ፣

ረ) የጉዳይ ሠራተኞች በብሔራዊ ጉዳይ አያያዝ የአሰራር ማዕቀፍ መሠረት ተገቢውን የመልሶ ማቀላቀል ቅጽ የመጠቀም፣

ሰ) ቤተሰብ፤ አግባብነት ያለው ቢሮ፣ የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያ፣ የአገልግሎት ሰጪ ተቋም እና የአማራጭ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪዎች ተቀዳሚ ኃላፊነቶቻቸው በጽሑፍ መቀመጥ እና የሚመለከታቸው ሁሉ ሲስማሙበት፣

## 26. ክትትልና ድጋፍ

1) መልሶ ማቀላቀሉ በተደረገ በሁለት ሳምንት ውስጥ የድህረ መቀላቀል ወይም ምደባ ክትትል መካሄድ አለበት።

2) የሕፃኑን ጥቅም እና ደህንነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ ተደጋጋሚ ክትትልን የሚጠይቁ ፍላጎቶች ካልተከሰቱ በስተቀር ለመጀመሪያዎቹ ሁለት ወራት ወርሃዊ መደበኛ የድህረ ምደባ ክትትል መካሄድ አለበት።

3) የጉዳይ ሠራተኛው መልሶ የተቀላቀለውን ሕፃን ለመጀመሪያ አንድ ዓመት በየሶስት ወሩ፣ ከአንድ አመት በኋላ ሕፃኑ እና ቤተሰቡ በሚገባ መላመዳቸው እስኪረጋገጥ ድረስ በዓመት አንዴ ክትትል ማድረግ አለበት።

4) የጉዳይ ሠራተኛው በክትትል ጉብኝቱ ግኝቶች ላይ በመመሥረት ሕፃኑን ከቤተሰቡ ጋር በሚገባ ተዋህዶ እንዲኖር ለማስቻል በዚህ ንኡስ ክፍል መሠረት ተጨማሪ የድጋፍ አገልግሎቶችን እንዲያገኝ ማድረግ አለበት።

5) በጉዳይ ዕቅዱ ላይ ላይ የታዩ ለውጦች ይገመገማሉ እንዲሁም ከተዘጋጁት የማዋሃድ መለኪያዎች ጋር በማወዳደር ማሻሻያ ሊደረግባቸው ይችላል፡፡

6) በጉዳይ ዕቅዱ ላይ የሰፈሩ ግቦች እና የተቀመጡ መለኪያዎች መሳካታቸውና የሕፃኑን መዋሀድ ዘላቂነት ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ጉዳዩ ይዘጋል፡፡

7) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (6) ድንጋጌ ቢኖርም በአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ውስጥ ጉዳይ መዛወር እንጂ የጉዳይ መዝጊያ አይካሄድም።

8) መልሶ የተቀላቀለው ሕፃን ከቤተሰቡ ጋር መዋሀድ ያልቻለ ከሆነ በሕፃኑ ፍላጎቶች እና ሁኔታ እንዲሁም በብሔራዊ ጉዳይ አያያዝ ስርዓት ማዕቀፍ መሰረት በማረግ የተሻሻለ የጉዳይ ዕቅድ መዘጋጀት አለበት።

9) ማንኛውም ሕፃን ካለበት ክብካቤ ለማስወጣት ወይም ክብካቤን በማቋረጥ ወደ ሌላ አማራጭ የማዛወር ውሳኔ በዚህ መመሪያ ክፍል ሶስት ውስጥ ክብካቤን ስለማቋረጥ በተመለከቱት አኳኋን የሚፈጸም ይሆናል፡፡

## ንኡስ ክፍል ሶስት
## የተቋጥሮ ዝምድና ክብካቤ

## 27. የተቋጥሮ ዝምድና ክብካቤ አገልግሎት አሰጣጥ

1) የተቋጥሮ ዝምድና ክብካቤ አንድ ሕፃን የሚመለከተው የመንግስት አካልን ፈቃድ ሳይጠየቅ በእናት ወይም በአባት በኩል የተቋጥሮ ዝምድና ባላቸው ቤተሰብ ውስጥ በጊዜያዊነት ወይም ለረጅም ጊዜ ተገቢውን ጥበቃ እያገኘ የሚቆይበት የክብካቤ አይነት ነዉ።

2) አንድንሕፃን ከአንድ ክብካቤ አማራጭ ዓይነት ወደ ቋጥሮ ዝምድና ክብካቤ አይነት ለማሸጋገር በቅድሚያ አግባብነት ባለው ቢሮ ወይም በማህበረሰብ አቀፍ ጥምረት ወይም በሕፃን ጥበቃ ባለሙያ ተመርምሮ አስፈላጊነቱ ታሞኖበት ሲፀድቅ ብቻ ነው፡፡

3) የተቋጥሮ ዝምድና ክብካቤ ለመስጠት አላማ የቤተሰብ አባላት የሚባሉት አያት፣ አክስት፣ አጎት፣ የአክስት ወይም የአጎት ልጅ ወይም ታላቅ እህትና ታላቅ ወንድም ናቸው፡፡

## 28. የተቋጥሮ ዝምድና ክብካቤ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች

1) ማንኛውም ህጻን በተቋጥሮ ዝምድና አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን፣

ሀ) ከወላጆቹ ጋር መኖር ያልቻለ ወይም ወላጆቹ ተፈልገው ሊገኙ ያልቻሉ ወይም በህይወት የሌሉ መሆኑ ሲረጋገጥ ወይም ሕፃኑ ከወላጆቹ ጋር መቆየት የሕፃኑን ጥቅምና ደህንነት የሚጎዳ ሆኖ ሲገኝ፣

ለ) ሕፃኑን የተመለከቱ  የትምህርት፣ የክትባት፣ የልደት እና የመሳሰሉት መረጃዎችን ማሟላትና በአካባቢው ባለ የመመዝገብ ስልጣን ያለው የመንግስት አካል መመዝገብ አለበት፡፡

ሐ) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፣) (ለ) ድንጋጌ ቀደም ሲል መደበኛ ያልሆነ ወይም ባህላዊ አገልግሎት ተጠቃሚ የነበሩ ሕፃናትንም በተመለከተ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

መ) በዚህ አንቀጽ ከንኡስ አንቀጽ (1) (ሀ) እስከ (ሐ) የተቀመጡትን መስፈርቶች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱና የሚመለከታቸው አካላት የሚከተለውን ሂደት መከተል ይኖርባቸዋል፣

፣) የተቋጥሮ ዝምድና ክብካቤ አገልግሎት ያለውን ሚና እና አስፈላጊነት መገንዘብ፤ እንዲሁም በሚያከናውነው የዳሰሳ ጥናት መሰረት የተሻለ የአገልግሎት አሰጣጥን ለማጠናቀር የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን የመውሰድ፣

2) ሕፃናት እና ቤተሰቦች በተቋጥሮ ዝምድና ክብካቤ ድጋፍ የሚሹ መሆናቸው ሲታወቅ፣ አግባብነት ያለው ቢሮ ወይም በቀበሌ በማስመዝገብ ከአገልግሎት ሰጪ አካላት ጋር በማገናኘት አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ ይቻላል።

ሠ) በወላጆች ስምምነት፣ የክብካቤ ሁኔታውን ከተወሰነ ቆይታ በኋላ መደበኛ እንዲያደርጉ ማበረታታት እና ማስቻል አለበት። ማንኛውም አግባብነት ያለው ቢሮ ወይም ስልጣን ያለው አካል የህጻኑን ጥቅምና ደህንነት ለማስጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ህጻኑ ኢኮኖሚያዊ ወይም ሌሎች ማህበራዊ ድጋፍ የሚያገኝበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ እንዲሁም የክብካቤ ሁኔታውን ከተወሰነ ቆይታ በኋላ ወደ መደበኛ አገልግሎት እንዲቀይሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡

ረ) በዚህ መመሪያ ውስጥ ለቤተሰብ ማጠናከር እና አቅም ማጎልበት አገልገሎት እንዲሁም ወላጆቻቸውን ያጡ እና ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ሕፃናት የድጋፍ አገልግሎቶች አሰጣጥ መመርያ መሰረት የሚሰጡ አገልግሎቶች ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸምም ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

ሰ) የተመዘገበና ድጋፍ እያገኘ የሚገኝ የተቋጥሮ ዝምድና ቤተሰብ  ቀጣይነት ያለው ድጋፍ እንዲያገኝና ምደባው የሕፃኑን ጥቅም እና ደህንነት ያማከለ እና ፍላጎቱን የሚያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ በዚህ መመሪያ ውስጥ በተጠቀሰው የጉዳይ አያያዝ ሂደት መሠረት ክትትል ሊደረግበት ይገባል፡፡

ሸ) የተቋጥሮ ዝምድና ክብካቤ በተቋማዊ ክብካቤን ጨምሮ በሌሎች የአማራጭ ክብካቤ ውስጥ ላሉ ሕፃናት እንዲሁም ወላጆቻቸው ጋር መልሰው ሊቀላቀሉ እና ሊዋሃዱ ላሉ ሕፃናት  የአጭር ወይም የረጅም ጊዜ የክብካቤ አማራጭ ሊሆን ይችላል።

ቀ) ሕፃናት ከሌሎች የአማራጭ ክብካቤ ወደ ቋጠሮ ዝምድና ቤተሰብ እንዲመጡ ሲደረግ ለሕፃናቱ ተንከባካቢ ሊሆኑ የሚችሉ የቤተሰብ አባላትን ለመለየት፣ እንዲሁም ተገቢነታቸውን ለመገምገም የሕፃናት ልየታ፣ የሕፃናት የዳሰሳ ጥናት እና ቤተሰብን የማፈላለግ እና የቤተሰብ ዳሰሳ ጥናት ተግባራት በብሔራዊ የጉዳይ አያያዝ መመሪያ መሠረት መካሄድ አለባቸው። ወላጆቹ በሕይወት ኖረው አድራሻቸው የማይታወቅ ከሆነ፣ የጉዳይ ሠራተኞች ወላጆችን የማፈላለግ ተግባራትን በተሟላ መልኩ ማካሄዳቸውን መቀጠል እና የተደረጉ ጥረቶችን መሰነድ አለባቸው።

በ)  ወላጆቹ የሚታወቁ ሲሆን የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያው ወይም የጉዳይ ሠራተኛው መልሶ የማቀላቀል እና የማዋሃድ አማራጭን ለመውሰድ የተሟላየወላጆች የዳሰሳ ጥናት መካሄዱን ማረጋገጥ አለበት።

ተ)  በዳሰሳ ጥናቱ ውጤት መሰረት የተቋጥሮ ዝምድና ካላቸው ቤተሰቦች መካከል ለህፃኑ ተስማሚ የሆነውን እና የሕፃናኑን ልዩ ፍላጎት በተሻለ ማሟላት ከሚችለው የቤተሰብ አባል ጋር ህጻኑ መጣመር ይኖርበታል፡፡ ሕፃናትን ከቤተሰብ ጋር በማጣመር ሂደት ውስጥ ሕፃኑና በቤተሰቡ ውስጥ የሚገኙ ሌሎች ህጻናት በውሳኔው ላይ መሳተፍ አለባቸው፡፡ በኢ-መደበኛ ክብካቤ ውስጥ ያሉ ሕፃናትን ከጥቃት፣ ቸል ከመባል፣ ከሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ እና ከማንኛውም ብዝበዛ ለመጠበቅ በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል ተገቢውን እርምጃዎች መወሰድ አለበት።

## ንኡስ ክፍል አራት
## የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ

## 29. የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አገልግሎት አሰጣጥ

1) የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አንድን ሕፃን በአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ተቋም አስቀድሞ በተመረጠ፣ በቂ ስልጠና ባገኘ ፣ ለአደራ ቤተሰብነት ብቁነቱ የተረጋገጠ፣ የሕፃኑ ወላጅ፣ ዘመድ፣ ወይም ሞግዚት ባልሆነ ሕፃኑን ለመንከባከብ ፈቃደኛ በሆነ ቤተሰብ ውስጥ በጊዜያዊነት የመመደብ የአማራጭ ቤተሰብ ተኮር ክብካቤ ዓይነት ነው።

2) ህጻናት በተቋም ክብካቤ ውስጥ እንዲመደቡ ከመደረጉ በፊት የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አራጭ ተፈልጎ ያልተገኘ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡

3) በሚኒስቴሩ እውቅና የተሰጣቸው የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አገልገሎት ሰጪ ተቋማት ሕፃናትን በአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ውስጥ የመመደብ፣ ዕጩ የአደራ ቤተሰቦችን የመመልመል አሰፈላጊውን ተግባራት የማከናወን እንዲሁም በጉዳይ አያያዝ ድጋፍ እና ሥልጠና የመስጠት ሃላፊነት አለባቸው ።

4) ሚኒስቴሩ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አገልግሎት አሰጣጥን የመከታተልና ድጋፍ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

5) የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አገልገሎት መስጠት እና ክትትል የማድረግ ኀላፊነት አለበት።

6) የሕፃን ጥበቃ ባለሙያው የጉዳይ አያያዝን እንዲሁም በዚህ ክፍል የተጠቀሱ ሌሎች ተግባራትን በማህበረሰብ አቀፍ ጥምረት ውስጥ ለሚገኙ ወይም በአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለባለሙያው የተሰጡትን ተግባራት ተወክለው እንዲሰሩ ማድረግ ይችላል፡፡

7) ህጻኑ ለአደራ ቤተሰብ ከመሰጠቱ በፊት የሕፃኑ፣ የአደራ ቤተሰቡ፣ በህይወት ያሉ የሕፃኑ የተፈጥሮ ወላጆች እና የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት መብትና ሃላፊነትን የሚዘረዝር የአደራ ቤተሰብ ውል መዋዋል አለባቸው።

## 30. የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አፈጻጸም የሚከተላቸው መሰረታዊ መርሆዎች

1) ሕፃናትን በራሳቸው ማህበራዊ-ባህላዊ አካባቢ ቅድሚ ሰጥቶ መመደብ፣

2) ስደተኛ ሕፃናት በተቀባይ ማኅበረሰብ ውስጥ ማዋሃድ እና ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፣

3) ሕፃናት ከኑሮ ሁኔታቸው ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ላይ በሚደረጉ ውሳኔዎች ላይ መሳተፍ እንዲችሉ እና አዋቂዎች በእንክብካቤ አሰጣጥ ወቅት አጋዥ የሆኑ መረጃን እንዲያካፍሉ እድሜያቸውን በሚመጥን መንገድ ማበረታታት፡፡

4) በዚህ መመሪያ ውስጥ የቀረቡ መሰረታዊ መርሆዎች የሕፃኑን ጥቅም እና ደህንነትን ጨምሮ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አገልግሎት አሰጣጥ ወቅት ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## 31. የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ዓይነቶች

1) በዚህ መመሪያ መሰረት ሦስት ዓይነት የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ዘዴዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡ እነዚህም፡-

ሀ) የአስቸኳይ ጊዜ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ፣

ለ) ጊዜያዊ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ፣

ሐ) የረጅም ጊዜ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ፣

2) እንደ ቤተሰብ ድጋፍ አገልግሎት አይነቱ ለረዥም እና ለአጭር ጊዜ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ምደባዎች የሚያገለግል ተጨማሪም የእፎይታ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል።

## 32. የአስቸኳይ ጊዜ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ

1) የአስቸኳይ ጊዜ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አንድን ሕፃን ለዚህ አገልግሎት ቀድሞ በተመረጠ እና ብቁነቱ በተረጋገጠ የአስቸኳይ ጊዜ የአደራ ቤተሰብ ውስጥ በጊዜያዊነት እንዲቆይ የሚያስችል የምደባ ዓይነት ነው።

2) የአስቸኳይ ጊዜ የአደራ ቤተሰቦች ማለት ሕፃኑን ለመንከባከብና ጥበቃ ለመስጠት በአጭር ቅድመ ማስታወቂያ ወይም በተመሳሳይ ቀን ወይም ከ 24 ሰዓታት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ፈቃደኛ የሆኑ ቤተሰቦች ናቸው።

3) የመጀመሪያ የአስቸኳይ ጊዜ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ምደባ በሕፃናት ጥበቃ ባለሙያው ግምገማ ከመደረጉ በፊት ከአሥር እስከ አስራ አምስት ቀናት የሚቆይ ሲሆን፣ በቀጣይ እንደ ተስማሚነቱ እና አስፈላጊነቱ ምደባው ወደ ጊዜያዊ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ሊቀየር ይችላል።

4) የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያው ወይም የጉዳይ ሠራተኛው የአደራ ቤተሰቡ ሕፃኑን በአስቸኳይ ሁኔታዎች ውስጥ ለመቀበላቸው በጽሁፍ ስምምነታቸውን እንዲገልጹ ማድረግ አለበት፡፡

5) ሕፃኑ ከቀድሞ ተንከባካዎቹ ጋር መልሶ መቀላቀል ወይም የተቋጥሮ ዝምድና ካላቸው የቤተሰብ አባላት ጋር መመደብ እንደማይቻል ከተረጋገጠ፣ በሕፃኑ ጥቅም እና ደህንነት እንዲሁም በብሔራዊ የጉዳይ አያያዝ መመሪያ መሠረት ሕፃኑ በተመደበ ከአስራ አምስት ቀናት በኋላ በጉዳይ ሠራተኛው ወይም በአደራ ቤተሰቡ ማመልከቻ መነሻነት አግባብነት ቢሮ ወይም በማህበረሰብ አቀፍ ጥምረት ወይም በሕፃናት ጥበቃ ባለሙያ ውሳኔ የአስቸኳይ ጊዜ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ምደባ ወደ ጊዜያዊ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ሊቀየር ይችላል።

## 33. ጊዜያዊ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ

1) ጊዜያዊ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አንድ ሕፃን ቋሚነት ያለው ክብካቤ እስኪገኝለት ድረስ በታቀደ እና ደህንነቱ በተጠበቀ ግዚያዊ የቤተሰብ ተኮር ክብካቤ ውስጥ የሚደረግ ምደባ ነው።

2) አንድ ሕፃን እስከ አሥራ ሁለት ወራት በጊዜያዊ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ውስጥ ሊመደብ ይችላል፣ ምደባው አግባብነት ባለው ቢሮ ወይም በሕፃናት ጥበቃ ባለሙያው በየዓመቱ እየታደሰ እስከ ሦስት ዓመት ሊዘልቅ ይችላል።

## 34. የረጅም ጊዜ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ

1) የረጅም ጊዜ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አንድ ሕፃን ዕድሜው 18 ዓመት እስኪሞላው ድረስ በአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ውስጥ የሚቆይበት የምደባ አይነት ነው።

2) የረጅም ጊዜ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ተገቢ የሚሆነዉ ሕፃኑን ከቤተሰብ ጋር መልሶ ማቀላቀል የማይቻል ወይም የሕፃኑን ጥቅምና ደህንነት ያላማከለ ሲሆን እንዲሁም ሌሎች ተስማሚ ቋሚ አማራጮች ሳይገኙ ሲቀር ነው።

3) የረጅም ጊዜ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ቀደም ብሎ በአደራ ክብካቤ ሥር ላለ ሕፃን ተስማሚ እና አስፈላጊ የክብካቤ ዓይነት ሆኖ ሲገኝ እና የአደራ ቤተሰብ ተንከባካቢው ለሕፃኑ ላለፉት ሦስት ዓመታት እንክብካቤ ሲያደረጉ የቆዩ ከሆኑ፣ የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያው አግባብነት ላለው ቢሮ ምደባው ወደ ረጅም ጊዜ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ እንዲቀየር ትእዛዝ እንዲሰጥለት ማመልከቻ ሊያቅረብ ይችላል።

4) የረጅም ጊዜ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ከዚህ ከታች የተዘረዘሩትን ጨምሮ ለሕፃኑ ዘለቄታዊ ምደባ የተደረጉ ጥረቶች ሳይሳኩ ሲቀር የሚፈጸም ነው፡፡

   ሀ) ሕፃኑን ከወላጅ ጋር መልሶ የማቀላቀል ወይም የተቋጥሮ ዝምድና ካላቸው የቤተሰብ አባላት ጋር የመመደብ ጥረቶች ገና በሂደቱ ላይ የሚገኙ ሲሆን፣

   ለ) በሕፃኑ ጥቅም እና ደህንነት መሰረት ከወላጁ ጋር መልሶ ማቀላቀል የማይቻል ሆኖ ሲገኝ፣

   ሐ) ሕፃኑን የተቋጥሮ ዝምድና ክብካቤ እና ጉዲፈቻን ጨምሮ በሌሎች የቤተሰብ ተኮር የክብካቤ ዓይነቶች ለመመደብ ካልተቻለ ወይም የሕፃኑን ጥቅምና ደህንነት ያማከለ ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር፣

   መ) ሕፃኑ ከተመደበበት የጊዚያዊ የአደራ ቤተሰብ ጋር ጉልህ የሆነ ትስስር እና ቤተሰባዊ ግንኙነት አዳብሮ ከሆነ፣

   ሠ) ሕፃኑ አሥር ዓመት እና ከዛ በላይ ከሆነ ባለበት የአደራ ቤተሰብ ውስጥ ለመቆየት ፈቃዱ ከሰጠ፣

   ረ) ሕፃኑ በጉዲፈቻ ቤተሰብ ውስጥ ለማደግ የማይፈልግ ሲሆንና ዕድሜው አሥር ዓመት እና ከዛ በላይ ሆኖ፣ አስተያየት ስለሚሰጥበት ጉዳይ በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ግንዛቤ ሲኖረው፣

   ሰ) ሕፃኑ በጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰብ ውስጥ ለመመደብ ቢያንስ አንድ ዓመት የጠበቀ ከሆነ።

## 35. የእፎይታ ጊዜ ክብካቤ

1) የእፎይታ ጊዜ ክብካቤ ለአደራ ጊዜ ቤተሰቦች ጊዜያዊ እረፍት እና የመረጋጋት ጊዜ የሚሰጥ እንዲሁም ሕፃናት ላይ ሊደርስ የሚችል ጉዳትን ወይም ቸል የመባል ስጋትን የሚቀንስ የአጭር ጊዜ ክብካቤ ነው።

2) የእፎይታ ጊዜ ክብካቤ የአደራ ቤተሰብ ተንከባካቢዎች እንደአስፈላጊነቱ እስከ አንድ ሳምንት ድረስ ከእለት ተእለት የእንክብካቤ ሃላፊታቸው እረፍት በመስጠት ለአጭር ጊዜ እፎይታ እንዲያገኙ የሚያስችል የክብካቤ አይነት ነው።

3) የእፎይታ ጊዜ ክብካቤ አማራጭ ቤተሰብ ተኮር የክብካቤ አይነት አይደለም፣ ሆኖም ሕፃናት እና ታዳጊዎች በጊዜያዊነት እንዳስፈላጊነቱ እና እንደተስማሚነቱ ቀድመው በተለዩ እና ብቁነታቸው በተረጋገጠ የአደራ ቤተሰብ ተንከባካቢዎች ጋር ተመድበው ባሉበት ጊዜ ለተንከባካቢ ቤተሰቦች የሚሰጥ የቤተሰብ ድጋፍ አገልግሎት ነው።

4) ከሕፃናት ጥበቃ ባለሙያ ወይም ከማህበረሰብ አቀፍ ጥምረት እውቅና ውጪ ማንኛውም ሕፃን በእፎይታ ጊዜ ክብካቤ ውስጥ አይመደብም።

5) የአደራ ቤተሰቦች የእፎይታ ጊዜ ሲያስፈልጋቸው፣ የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (4) መሰረት በማድረግ በአደራ የተረከቡትን ሕፃን ለአጭር ወይም ለረጅም ጊዜ በአደራ ለሚንከባከቡ ቤተሰቦች በጊዜዊነት ሊሰጡ ይችላሉ።

6) አግባብነት ያለው ቢሮ የእፎይታ ጊዜ ክብካቤን ለመስጠት የሚችሉ አስቀድሞ የተመለመሉ፣ የሰለጠኑ እና ብቁነታቸው የተረጋገጠ ተንከባካቢዎችን ዝርዝር በአደራ ቤተሰብ ክብካቤ መዝገብ ይይዛል።

7) የእፎይታ ጊዜ ክብካቤ ማጣመር እና ድልድል በተመለከተ የሚሰጥ ውሳኔ የህጻኑ ፍላጎት መሰረት በማድረግ የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያውን ወይም የጉዳይ ሥራ አስኪያጅ ወይም ሠራተኛውን በማማከር በአደራ ቤተሰቦች የሚካሄድ ይሆናል።

## 36. የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ሕጋዊ ውጤቶች

1) የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ሕፃኑን እንደወላጅ የመጠበቅ እና የመንከባከብ ኀላፊነቶችን ለአደራ ቤተሰቡ ይሰጣል።

2) የአደራ ቤተሰቡ ከሀገር እንዲወጣ የሚያደርግ የተለየ ሁኔታ ሲያጋጥመው በቅድሚያ ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት ሳይፈቅድ ሕፃኑን ከሀገር ይዞ መውጣት አይችልም።

3) ለሕፃኑ የእፎይታ ጊዜ ክብካቤ በሚሰጥበት ወቅት ሕፃኑን የመጠበቅ እና የመንከባከብ የአደራ ቤተሰቡ ኀላፊነቶች አይቋረጡም።

## 37. የተገቢነት ደረጃዎች

1) የአደራ ቤተሰብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አገልግሎቶች ተገቢነት፣ አገልግሎቱ የሚያስፈልግበትን ጊዜ፣ የህጻኑን ፍላጎት ማሟላቱን እና ሌሎች መስፈርቶች መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

## 38. ሕፃናትን በአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ለመመደብ የተገቢነት መስፈርቶች

1) የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ተገቢ የምደባ ዓይነት የሚሆነው፡-

ሀ) ሕፃናቱ ሁለቱንም ወላጆች በሞት ያጡ፣ ተጥለው የተገኙ፣ ኑሮአቸውን በጎዳና ያደረጉ እና ወላጆቻቸው ወይም የተቋጥሮ ዝምድና ያላቸው የቤተሰብ አባላት ተፈልገው ሊገኙ የማይችሉ ሲሆን፤

ለ) ሕፃኑ ከወላጁ ወይም የተቋጥሮ ዝምድና ካላቸው ቤተሰቦቻቸው ወይም ዘመዶቻቸው ጋር መኖር የሕፃኑ ጥቅምን እና ደህንነትን ያልጠበቀ ሆኖ ሲገኝ፤

ሐ) ሕፃኑ በሚኖርበት ቤት ውስጥ በቂ የሆነ እንከብካቤና ጥበቃ ሳይሰጠው ሲቀር፤

መ) የሕፃኑ ወላጆች በማይድን በሽታ ወይም በአእምሮ ህመም ወይም መታወክ መጠቃታቸውና ለሕፃኑ ተገቢውን ክብካቤ መስጠት አለመቻላቸው በሚመለከተው አካል ሲረጋገጥ፣

ሠ) ሕፃኑ ከወላጆቹ ጋር በእስር ወይም በሌላ ድንገተኛ አደጋ ምክንያት የተለያየ ሲሆን እና በተቋጥሮ ዝምድና ካላቸው የቤተሰብ አባላት ጋር መመደብ የሕፃኑ ጥቅም እና ደህንነት የሚጎዳ ሲሆን፤

ረ) ሕፃኑ በቤተሰብ ውስጥ እያለ ቸል የመባል፣ የብዝበዛ ወይም የአካል፣ የወሲብ ወይም ሌላ የጥቃት ዓይነት ሰለባ ከሆነና በወላጅ ወይም በተቋጥሮ ዝምድና የቤተሰብ ክብካቤ ውስጥ ቢቆይ ለተጨማሪ ጉዳት ይጋለጣል የሚል ሥጋት ሲኖር፤

ሰ) ሕፃኑ ባለው የአካላዊ ወይም የአእምሮ እክል ምክንያት ወላጆች ለህፃኑ በቂ እንክብካቤ ማድረግ ሳይችሉ በመቅረታቸው ለተቋማዊ ክብካቤ ምደባ ተጋላጭ ሆኖ ሲገኝ፤

ሸ) ሕፃኑ በተፈጥሮ አደጋ ወይም በጦርነት ምክንያት የተፈናቀለና ከወላጆቹ የተለየ ሆኖ ሲገኝ።

2) የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ተገቢ የማይሆነው፡-

ሀ) ሕፃኑ ከሚኖርበት ቤተሰብ በገንዘብ ወይም በቁሳቁስ ድህነት ምክንያት የተለየ ከሆነ፣

ለ) ለሕፃኑ ጥቅም እና ደህንነት የሚጠቅም ካልሆነ በስተቀር ሕፃኑ ከእህቱ ወይም ከወንድሙ የመነጠል አደጋ ሲኖር።

## 39. ዕጩ የአደራ ቤተሰቦች ብቁነት መስፈርቶች

1) አንድን ሕፃን በአደራነት ለመንከባከብ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የብቁነት መስፈቶች ሊያሟሉ ይገባል፣

ሀ) በዜግነት ኢትዮጵያዊእና በቋሚነት ኢትዮጰያ ውስጥ ነዋሪ የሆነ፤

ለ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተደደነገገው ቢኖርም ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የውጭ ሃገር ዜጎች ከአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ምደባው በፊት በኢትዮጵያ ውስጥ ቢያንስ ለተከታታይ ሁለት ዓመታት መኖራቸውን ማረጋገጥ የሚችሉ፤

ሐ) ከአደራ ቤተሰቡ አንዳቸው ዕድሜያቸው ከ25 ዓመት ያላነሰ፣

መ) የአደራ ቤተሰቦቹ የትዳር አጋሮች ከሆኑ ሁለቱም ሕፃኑን ለመቀበል፣ እንዲሁም ልጆችን ጨምሮ ሌላ ማንኛውም የቤተሰቡ አባል ፈቃደኝነታቸው በጽሁፍ ስምምነታቸውን ሲገልጹ ፣

ሠ) የሕፃናኑን ደህንነት ለመጠበቅ እና በጤናማ ሁኔታ ለመንከባከብ እና የዕድገት ፍላጎቱን ለማሟላት ዕውቀቱ እና ክህሎቱ ያላቸው መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ረ) ሕፃኑን ለማሳደግ የጤንነት ሁኔታቸው ብቁ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፣

ሰ) ህጻኑን ለመንከባከብ በቂ ገቢ ያላቸው መሆኑን ማሳየት የሚችሉ፣

ሸ) ከሕፃናት ጥቃት ጋር የተያያዘ ወይም በማንኛውም ወንጀል በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ሆነው ያልተቀጡ፣

ቀ) የመልካም ሥነ-ምግባርን የሚያረጋገጥ ሁለት የምሥክርነት ደብዳቤዎችን ማቅረብ የሚችሉ፣

በ) የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ የሚገኙ አመልካቾች የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ የሚገኙ ህጻናትን በአደራ ቤተሰብነት ለማሳደግ ብቁ ናቸው።

## 40. ለአደራ ቤተሰብ ምዝገባ የሚቀርብ ማመልከቻ

1) አግባብነት ያለው ቢሮ ወይም የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያ ወይም የማህበረሰብ አቀፍ ጥምረት ፈቃድ ያልተሠጠው ማንኛውም ሰው አንድን ሕፃን ወይም ሕፃናትን በአደራነት እንዲንከባከብ ሊሰጠው አይችልም።

2) **ለአደራ ቤተሰብ ለመሆን የሚቀርብ ማመልከቻ** ከላይ የተጠቀሱትን የብቁነት መስፈርቶችን የሚያሟላ ማንኛውም ሰው አግባብነት ላለው ቢሮ ወይም ለአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ተቋም በአደራ ቤተሰብነት ለመመዝገብ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሰነዶች በማሟላት ለማመልከት ይችላሉ፣

ሀ) የታደሰ መታወቂያ/ፓስፖርት

ለ) የጋብቻ የምስክር ወረቀት፣

ሐ) የገቢ ማስረጃ

መ) ከወንጀል ነፃ መሆናቸውን የሚገለፅ የፖሊስ ማስረጃ

ሠ) የሕክምና ማስረጃ

መ) የመልካም ሥነ-ምግባር ማረጋገጫ/ የምሥክርነት ደብዳቤ ከሁለት ሰዎች

ረ) ጉርድ ፎቶ ግራፍ

ሰ) ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ለሆኑ የውጭ ሃገር ዜጎች ከአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ምደባው በፊት በኢትዮጵያ ቢያንስ ለሁለት ዓመታት መኖራቸውን የሚያሳይ ማስረጃ፣

3) ማመልከቻው እና የብቁነት መስፈርቶች የተሟሉ ሆነው ሲገኝ፣ የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያው የቤተሰቡን የዳሰሳ ጥናት ያካሂዳል፣ ወይም እንደ አፈላጊነቱ ለአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ወይም ለማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረት የዳሰሳ ጥናቱን እንዲያካሂዱ ውክልና ይሰጣል።

4) የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ማመልከቻው የሚጸድቅው ከሕፃናት ጥበቃ ባለሙያው ወይም እንደ ጉዳዩ ሁኔታ ከተወከለው የጉዳይ ሠራተኛ ብቁነትን የሚያረጋገጥ የቤት ለቤት የዳሰሳ ጥናት ውጤት ሲገኝ ብቻ ነው።

## 41. የአደራ ቤተሰብ ሥልጠና

1) ለአደራ ቤተሰቦች የዝግጅት፣ የድጋፍ እና የማማከር አገልግሎቶች ጊዜውን በጠበቀ መልኩ ከምደባ በፊት፣ በምደባ ጊዜ እና ከምደባ በኋላ ለተንከባካቢዎች ስልጠና እንዲሰጣቸው መደረግ አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሠረት ስልጠና ለወሰዱ እጩ የአደራ ቤተሰቦች አግባብነት ያለው ቢሮ የብቁነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሠጣል፡፡

3) የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያው ወይም የተወከለው የጉዳይ ሠራተኛ ለዕጩ እና ለነባር የአደራ ተንከባካቢዎች በነጠላ ወይም በቡድን በየጊዜው ሥልጠና ማዘጋጀት አለበት። ሥልጠናዎቹ አዎንታዊ የህፃናት አስተዳደግ፣ አዎንታዊ የባሕርይ አያያዝ፣ የሕፃናት መብቶች እና ዕድገት፣ ጤና እና ደህንነት፣ የአእምሮ ጉዳት/ቁስለት፣ የማማከር አገልግሎት እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ሊሆኑ የሚችሉ ርዕሶችን ሊያካትት ይችላል።

## 42. የአደራ ቤተሰብ ምዝገባ

1) አግባብነት ያለው ቢሮ የአደራ ቤተሰብ ምደባ የጸደቀላቸውን ሁሉም ሕፃናት፣ ብቁነታቸው ከተረጋገጠ የአደራ ቤተሰብ ዝርዝር እና የአደራ ቤተሰቡ እና የሕፃናቱ የመኖሪያ አድራሻን የያዘ መዝገብ መያዝ አለበት።

## 43. የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አገልግሎት አሰጣጥ ዝቅተኛ መስፈርቶች

### 1) የጉዳይ ሠራተኞች እና የጉዳይ ስራ አስኪያጅ ብቃት

ሀ) የጉዳይ ሰራተኛ ወይም የጉዳይ ስራ አስኪያጅ ለመቅጠር የሚያስፈልጉ መስፈርቶች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 በተመለከተው መሰረት መፈጸም አለበት፡፡

### 2) የአደራ ቤተሰብ አገልግሎቶችን ለማዳበር ግንዛቤን መፍጠር

ሀ) ሚኒስቴሩ፣ አግባብነት ያለው ቢሮ፣ የአደራ ቤተሰብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት፣ የማህበረሰብ አቀፍ ጥምረቶች እንዲሁም ሌሎች በአማራጭ ክብካቤ ላይ የሚሠሩ የመንግሥት የስራ ክፍሎች እና ባለድርሻ አካላት ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን እየቀረጹ ተግባራዊ የማድረግ ሃላፊነት አለባቸው።

ለ)የአደራ ቤተሰብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበርና የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በጠቀም ብቁ የአደራ ቤተሰቦችን ለመመልመል አላማ ያደረጉ የግንዛቤ ማስጨበጫ መልእክቶችን በማስተላለፍ በአደራ ቤተሰብ አገልግሎት ዙሪያ ህብረተሰቡን የማሳወቅ ሃላፊነት አለባቸው፡፡

ሐ) ዕጩ የአደራ ቤተሰቦች በግንዛቤ ማስጨበጫ ወይም ቅስቀሳ ፕሮግራሞች ላይ በመሳተፋቸው ምክንያት ምንም ዓይነት የስጦታ ወይም የገንዘብ ድጋፍ እንደሚደረግላቸው ቃል ሊገባላቸው አይገባም።

### 3) የሕፃናት ቅበላ እና ዝግጅት ሂደት

ሀ) የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያው፣ የማህበረሰብ አቀፍ ጥምረት፣ የአደራ ቤተሰብ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ወይም የጉዳይ ሠራተኛው ከሚከተሉት ምንጮች ሕፃናትን የመመደብ ጥያቄ ሊቀበሉ ይችላሉ፣

1) አግባብነት ካላቸው ቢሮዎች፣

2) ከማህበረሰብ አቀፍ ጥምረቶች፣

3) ከተቋማዊ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት፣

4) ከፖሊስ፣

5) ከሆስፒታል፣

6) ከማኅበረሰብ አቀፍ ድርጅቶች፣

7) ከሃይማኖት ተቋማት፡፡

ለ) የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ እና የትኛው የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አይነት ለሕፃኑ ተስማሚ እንደሆነ ለመወሰን የቅበላ ማጣሪያ የዳሰሳ ጥናት በ48 ሰዓታት ውስጥ መደረግ አለበት። የቅበላ ማጣሪያው የሕፃኑን መሠረታዊ መረጃ፣ የኋላ ታሪክ፣ የሕፃኑን አስቸኳይ ጉዳዮች እንዲሁም ሕፃኑ ለሥጋት የተጋለጠበትን መጠንን የሚያሳይ መሆን አለበት፡፡

ሐ) በአስቸኳይ ሁኔታዎች ውስጥ የመነሻ ቅበላ መረጃ የሕፃኑን በአደራ ቤተሰብ ክብካቤ መመደብ ተስማሚ መሆኑን እንዲሁም የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያው፣ የማህበረሰብ አቀፍ ጥምረቱ ወይም የጉዳይ ሠራተኛው የሕፃኑን አስቸኳይ ፍላጎቶች ለማሟላት ተስማሚ መኖሪያ እንዲለዩ የሚያግዙ መረጃዎችን መያዝ ይኖርበታል፡፡

መ) ሕፃኑ በአደራ ቤተሰብ ውስጥ በተመደበ በ24 ሰዓታት ውስጥ የሕክምና ምርመራ ወይም የጤና ሁኔታ ማጣሪያ ሊደረግለት ይገባል።

ሠ) ለስራ ክፍሉ ተብራርተው ተቀባይነት ያገኙ ሁኔታዎች ከሌሉ በስተቀር የአደራ ቤተሰብ አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ፣ የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያው ወይም የጉዳይ ሠራተኛው ሕፃኑ በአደራ ቤተሰብ ስለመመደቡና የተደረገውን ጥልቅ የመነሻ የዳሰሳ ጥናት ሕፃኑ ከተመደበ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ አግባብነት ላለው ቢሮ ማቅረብ አለባቸው።

ረ) የሕፃኑን የአጭር እና የረጅም ጊዜ ፍላጎቶች የሚያስቀምጥ ዝርዝር የአግልግሎት ዕቅድ ማዘጋጀት እና ምደባው በተካሄደ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አግባብነት ላለው ቢሮ ማሳወቅ ይኖርበታል።

## 4) ማጣመር፣ ማቀራረብ እና ትሥሥር እንዲሁም የተለዩ የሕፃናት ፍላጎቶችን የሚያሟላ ምደባ

ሀ) ዕጩ የአደራ ቤተሰቦች በአደራ ከተመደበው ሕፃን ጋር ለመጣመር ከመስማማታቸው በፊት በምደባው ወቅት የሕፃኑን የኋላ ታሪክ፣ ጤና፣ ስሜታዊ እና የእድገት ፍላጎቶች፣ እንዲሁም ሕፃኑን ማሳደግ የሚያስከትለውን ውጤት ለመረዳት የሚያግዛቸውን መረጃ ሊሰጧቸው ይገባል። ይህም ለአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ተቋም፣ ለሕፃናት ጥበቃ ባለሙያው፣ ለጉዳይ ስራ አስኪያጅ ወይም አግባብነት ላለው ቢሮ መገለጽ አለበት።

ለ) የአስቸኳይ ጊዜ የአደራ ቤተሰቦች በአስቸኳይ ሁኔታዎች ውስጥ ስለሚመደቡ ሕፃናት የሚገኙ መረጃዎች ጥቂት ሊሆኑ እንደሚችሉ በመገንዘብ ተገቢውን ድጋፍና እንክብካቤ ለመስጠት ዝግጁ መሆን እና በክብካቤው ወቅትም ስለሕፃኑ የዕድገት ፍላጎቶች ለሕፃናት ጥበቃ ባለሙያው ወይም ለጉዳይ ስራ አስኪያጅ ሠራተኛው ማሳወቅ አለባቸው።

ሐ) ሕፃኑ ሁለንተናዊ ፍላጎቶቹን በአስተማማኝ ሁኔታ የማሟላት አቅም ካላቸው የአደራ ቤተሰቦች ጋር መጣመር አለበት።

መ) የህጻኑ ምደባ የማንነት ስሜቱን ለማስጠበቅ እንዲቻልበተቻለ መጠን የሕፃኑን ባህል፣ ቋንቋ እና ሃይማኖት ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት። ሆኖም ሕፃናት የተለየ መጣመርን ሲጠብቁ ለረጅም ጊዜ መቆየት ስለሌለባቸው የጥበቃ እና የደህንነት መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸውን ቅድሚያ ለመስጠት በአስቸኳይ ጊዜ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ውስጥ ሊመደቡ ይችላሉ።

ሠ) የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያው ወይም የጉዳይ ሠራተኛ/ስራ አስኪያጅ ሕፃናትን ለአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ምደባ ለማዘጋጀት ግልጽ የክብካቤ ተግባራትን የያዘ የክብካቤ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ እንደ ሕፃኑ የእድገት አቅም እና እድሜን ባማከለ መንገድ ስለዕጩ የአደራ ቤተሰቦቹ ከምደባው በፊት የግንዛቤው ደረጃ እየታየ ለሕፃኑ መረጃ ሊሰጠው ይገባል። ሆኖም በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎች በወቅቱ መተግበር በሚችሉ ማዕቀፎች መሰረት የሚተገበሩ ይሆናል።

ረ) የአደራ ቤተሰቦች ለሕፃናቱ፣ ለሕፃኑ ወላጆች ወይም ዕጩ የጉዲፈቻ ቤተሰቦች፣ ለማኅበራዊ ሠራተኞችና ለበጎ ፈቃደኞች እንግዳ ተቀባይ፣ አካታች እና ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢን መፍጠር አለባቸው።

ሰ) የአደራ ቤተሰቦች የሌሎችን ሃሳብ ማክበር እና በሕፃናት፣ በወላጆቻቸው ወይም ዕጩ የጉዲፈቻ ቤተሰቦቻቸው፣ በሠራተኞች እና በጎ ፈቃደኞች መካከል ግልጽ የሆነ የትብብር ግንኙነትን ማበረታታት እንዲሁም ሕፃናቱን በሚመለከቱ ጉዳዮች በሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ ሕፃናቱ እንዲሳተፉ ማድረግ አለባቸው።

ሸ) የአደራ ቤተሰቦች ስለ ሕፃኑ አሳሳቢ የሆነን ማንኛውንም አጋጣሚ አግባብነት ያለው ቢሮ፣ ለሚመለከተው የአደራ ቤተሰብ አገልግሎት ሰጪ ተቋም፣ ለሕፃናት ጥበቃ ባለሙያ ወይም የማህበረሰብ አቀፍ ጥምረት በ24 ሰዓታት ውስጥ ጥቆማ ማድረግ አለባቸው። የተፈጸመው ድርጊት ደንብ መተላለፍን ወይም በወንጀል የሚያስጠይቅ ከሆነ ለፖሊስ ጥቆማ ማድረግ አለባቸው።

## 5) ምደባ፣ የድህረ ምደባ አገልግሎቶች እና የሽግግር ዕቅድ

ሀ) ሕፃኑ ወደ አዲሱ ምደባው ሲሄድ የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያው ወይም የጉዳይ ሠራተኛው መገኘት አለበት።

ለ) የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያው ወይም የጉዳይ ሠራተኛው የድህረ ምደባ የክትትል ጉብኝቶችን የማካሄድ ሃላፊነት አለበት።

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (ለ) መሰረት የሚካሄድ ክትትል የመጀመሪያው ጉብኝት ህጻኑ በተመደበ በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ፣ በቀጣይ ሁለት ወር፣ በሦስት ወር፣ በስድስት ወር፣ በአንድ ዓመት፣ በአንድ ዓመት ከስድስት ወር እንዲሁም ለረጅም ጊዜ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ደግሞ በየዓመቱ በማድረግ አስፈላጊ ሪፓርቶችን ማዘጋጀት እና የተለዩ ፍላጎቶች መሟላታቸውን ክትትል ማድረግ አለበት።

መ) ሕፃናት በክብካቤ ዕቅዱ መሠረት በአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ውስጥ እያሉ እና ወደ አዲስ ምደባ በሚሸጋገሩበት ጊዜ ማለትም ከድጋፍ ጋር ራስን ችሎ የመኖር አገልግሎት ወይም መልሶ ማቀላቀል እና ማዋሃድ ወይም ተቋጥሮ ዝምድና ክብካቤ ከምደባ በፊት ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል።

ሠ) የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያው ወይም የጉዳይ ስራ አስኪያጁ/ሠራተኛው የሁሉንም የምደባ ግንኙነት ጠቀሜታ፣ አስፈላጊ የሕፃናት የኋላ ታሪክ እና በምደባ ውስጥ ያላቸውን ሚና እና ኀላፊነቶች በዝርዝር

ማብራራት እና ከሕፃኑ ወይም ከሚመለከታቸው ሕፃናት እና ከአደራ ቤተሰቦች ጋር ግንኙነት ያላቸውን የተለያዩ ባለሙያዎች ሚናቸውን እና ኀላፊነቶቻቸውን ማብራራት እና ማስተባበር አለበት።

## 6) ክልል ተሻጋሪ ምደባ

ሀ) ሕፃናትን በቅድሚያ በተወለዱበት አካባቢ ለሚኖር የአደራ ቤተሰብ እንዲመደቡ ተገቢው ጥረት መደረግ አለበት። ሆኖም የክልል ተሻጋሪ ምደባ የአንድን ሕፃን ፍላጎቶች ለማሟላት የተሻለ መፍትሔ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ሕፃኑ ከሚኖርበት ክልል ሪፓርት በማዘጋጀት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተቀባይ/መዳረሻ ለሆነው ክልል መተላለፍ አለበት። በላኪው ክልል በሚመለከተው የሕፃናት ዘርፍ ቢሮ እና በተቀባይ/በመዳረሻ ክልሉ መካከል አስፈላጊ የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ መፈረም አለበት።

ለ) ከአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ምደባው ሽግግር ሁለት ወራት በኋላ፣ ተቀባይ/መዳረሻ ክልል ከላኪ የፌዴራል መንግስት ጋር በመስማማት በሕፃኑ ዘለቄታዊ ምደባ ጉዳይ ላይ የመወሰን ሥልጣን አለው።

## 7) በአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ውስጥ ላሉ ሕፃናት ዘለቄታዊ ዕቅድ ማውጣት

ሀ) ለሁሉም ሕፃናት ዘላቂነት ያለው ክብካቤ ከወላጆቻቸው ጋር መልሶ በማቀላቀል ወይም የተቋጥሮ ዝምድና ካላቸው ቤተሰቦች ጋር በመመደብ፣ በጉዲፈቻ ወይም በረጅም ጊዜ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ሊፈለግላቸው ይገባል። የማኅበረሰብ አቀፍ ክብካቤ ወይም ሆኖም ተቋማዊ ክብካቤ የመጨረሻ አማራጭ ሊሆኑ ይገባል።

ለ) የህፃናት ጥበቃ ባለሙያ ወይም የጉዳይ ስራ አስኪያጆች/ሠራተኞች ከተሟላ የዳሰሳ ጥናት በኋላ ሕፃኑን ወደ ዘላቂነት ያለው ክብካቤ እንዲሻገር ለማገዝ የአገልግሎት ዕቅድ ግቦችን ማዘጋጀት አለባቸው።

ሐ) ዘላቂነት ያለው ምደባ እስኪገኝ ድረስ ሕፃናቱ በተመደቡበት የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ውስጥ ባሉበት ጊዜ በዚህ መመሪያ በተቀመጠው አግባብ ክትትል ሊደረግላቸው ይገባል።

## 8) የአደራ ቤተሰብ አገልግሎት ተቋማት ሃላፊነት

ሀ) የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አግባብነት ባለው ባለሥልጣን መመዝገብና መንግሥት ለሚያወጣቸው ህጎች ተገዢ መሆን አለባቸው።

ለ) የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪዎች በተቋማቸው ውስጥ በቂ የሰለጠነ የሰው ሃይል መሟላቱን ማረጋገጥ አለባቸው።

ሐ) የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ለሰራተኞቹ የሥነ-ምግባር መመሪያ የማዘጋጀትና ለሁሉም ሠራተኞች ተደራሽ የማድረግ እንዲሁም መንግስት ያወጣቸውን ፖሊሲዎች የመፈጸም ሃላፊነት አለበት።

መ) የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ለሠራተኞቹ ተገቢ የሆኑ ሥልጠናዎችን መስጠት እና የሰነድ አያያዝ መስፈርቶችን መጠበቅ አለበት።

ሠ) የአደራ ቤተሰብ አገልግሎት ሰጪ ተቋም የሥራ አስኪያጆች፣ የሠራተኞች፣ የበጎ ፈቃደኞች እና የአደራ ቤተሰቦችን ተግባር፣ ተጠያቂነት፣ ሚና እና ኀላፊነትን ያካተተ ግልጽ መግለጫ ሊኖረው ይገባል።

ረ) የሕፃናትን ሕልውና እና ደህንነት ለማጎልበት ይቻል ዘንድ ቅሬታዎችን ለመቀበል እና ለመፍታት የሚያስችል የቅሬታ አያያዝ ሂደት በሚኒስቴሩ መዘጋጀት አለበት።

ሰ) የአደራ ቤተሰቦች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሚጠቀሙት የአደጋ ጊዜ መረጃ መስጫ አድራሻዎች ሊሰጣቸው ይገባል።

ሸ) የአደራ ቤተሰብ አገልግሎት ሰጪ ተቋም የክትትል እና የግምገማ መስፈርቶች፤ አመላካቾች፣ መተግበሪያዎች እና ሥርዓቶች ማዘጋጀት አለባቸው።

ቀ) የአደራ ቤተሰብ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ሚስጥራዊነትን፣ የመረጃ ተደራሽነትን እና የአገልግሎት አሰጣጥ መስፈርቶችን ጥራት እና፣ የመረጃ አያያዝ ሥርዓትን የተመለከተ ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ አለበት፡፡

በ) የአደራ ቤተሰብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ዝቅተኛውን የአገልግሎት አሰጣጥን የተመለከተ በህግ የተቀመጡ መስፈርቶችን የሚዘረዝር ፖሊሲ እና መመሪያ ማውጣት አለበት፡፡

## 9) ከወላጆች፣ ከጓደኞች እና ከሌሎች አስፈላጊ ከሆኑ ሰዎች ጋር መገናኘት

ሀ) መልሶ ማቀላቀልን አላማ በማድረግ እንዲሁም ሕፃናት ከጓደኞቻቸው እና አግባብነት ካላቸው ሰዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት መቀጠል ጥቅማቸውን እና ደህንነታቸውን ያማከለ ሆኖ ሲገኝ የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያዎች እና የጉዳይ ሠራተኞች ሕፃናት ከወላጆች እና ከተቋጥሮ ዝምደና ካላቸው ቤተሰቦች ጋር ያላቸውን ጤናማ ግንኙነት የመቀጠል መብት መከበሩን ማረጋገጥ አለባቸው።

ለ) የአደራ ቤተሰቦች ከወላጅ/ጆች እና/ወይም የተቋጥሮ ዝምድና ካላቸው የቤተሰብ አባላት ጋር ግንኙነት እንዲኖራቸው ማድረግ የሕፃኑን ጥቅም እና ደህንነት ያማከለ መሆኑ ከተረጋገጠ በሕፃናት ጥበቃ ባለሙያ ወይም በጉዳይ ሠራተኛ ወይም ሌሎች አሰፈላጊ በሆኑ የመንግሥት አካላት መታገዝ መታገዝ አለበት፣ የሕፃኑን ጥቅም እና ደህንነት ያላማከለ ሆኖ ካልተገኘ ወይም በፍርድ ቤት ካልተከለከለ በስተቀር፣ ሕፃኑ ከቤተሰቡ ጋር ያለውን ግንኙነት የመቀጠል እንዲሁም እህት እና ወንድሞቹን ወይም ሌሎች በሕይወታቸው ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ ሰዎችን የመጎብኘት መብት አለው።

ሐ) የአደራ ቤተሰቡን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያው፣ የጉዳይ ስራ አሰኪያጁ ወይም የሚመለከተው የመንግሥት አካል ወይም የሕፃኑወላጆች ጉብኝት የሚያደርጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

መ) አግባብነት ያለው ቢሮ፣ የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያ፣ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ወይም የጉዳይ ሠራተኛ ሕፃናትን እና ቤተሰቦችን ለማገናኘት ማዘጋጀት እንዲሁም የሥነ-ልቦናዊ-ማኅበራዊ ድጋፍን ጨምሮ አስፈላጊ የሆነ ግንኙነትን ለመደገፍ ተገቢውን እገዛ ማድረግ አለባቸው።

ሠ) ጉብኝቱ ከአደራ ቤተሰቡ ቤት ውጭ ሲሆን፣ ጉብኝቱ ከመደረጉ በፊት የሚገናኙበት ቦታ ደህንነቱ የተጠበቀና ምቹ መሆኑን ለማረጋገጥ የስጋት ግምገማ በሕፃናት ጥበቃ ባለሙያው፣ በአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ተቋም፣ ወይም በጉዳይ ሠራተኛው መካሄድ ይኖርበታል።

ረ) የእያንዳንዱ ግንኙነት ግብረ መልስ እንዲሁም በሕፃኑ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ በሕፃኑ የጉዳይ ማኅደር መመዝገብ አለበት።

### 10) የጉዳት አቤቱታ እና ጥርጣሬዎችን ማስተናገድ

ሀ) አግባብነት ያላቸው ሁሉም ቢሮዎች ፣ ሁሉም የአደራ ቤተሰብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት በአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ሥር ባሉ ሕፃናት ላይ ስለሚደርሱ አቤቱታ እና ጥርጣሬዎችን ለማስተናገድ ፖሊሲ እና በጽሑፍ መመርያ ሊኖራቸው ይገባል።

ለ) የአደራ ተንከባካቢዎች፣ የማህበረሰብ አቀፍ ጥምረቶች እና በጎ ፈቃደኞች አቤቱታን እንዴት እንደሚያስተናግዱ ወይም ሲደርሳቸው ወይም ሰው ላይ ጥርጣሬ ካደረባቸው የሚከተሉትን ማወቅ እና መረዳት ይኖርባቸዋል፦

1) ሕፃኑን በሚጎዳ መንገድ ወይም እንደጎዳ መረጋገጥ በሚችል መንገድ መፈጸሙን፣ ወይም

2) በሕፃኑ ላይ ወይም ከሕፃኑ ጋር በተያያዘ ወንጀል የፈጸመ ወይም ከሕፃናት ጋር ለመሥራት ብቁ እንዳልሆነ የሚያሳይ ባሕርይ በሕፃኑ ላይ ማንጸባረቁን።

ሐ) የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያው፣ የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪው ተቋም፣ የጉዳይ ሥራ አስኪያጁ/የጉዳይ ሠራተኛው ወይም ሌሎች የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት በማንኛውም አስፈላጊ ሁኔታ ውስጥ የሚወሰዱ እርምጃዎች አቤቱታን ለማጣራትና ለመወሰን በተዘጋጁ መመሪያዎች መሠረት መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው።

መ) አግባብነት ያለው ቢሮ፣ የማህበረሰብ አቀፍ ጥምረት እና የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሕፃናት ከምደባቸው ጋር በተያያዘ ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ ማንኛውም ችግሮችን ጥቆማ ማድረግ የሚችሉበትገለልተኛ ሥርዓት መዘርጋትና ስለስርዓቱ ተገቢውን መረጃ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

ሠ) በአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ውስጥ የተመደበ ሕፃንን በተመለከተ የቀረበ ማንኛውም ቅሬታ ግልጽና አስተማማኝ በሆነ መንገድ መጣራትና ለሕፃኑ ወይም ለቅሬታ አቅራቢው አስተማማኝ ጥበቃ መሰጠት አለበት፡ ፡ ማንኛውም በአደራ ቤተሰብ ክብካቤ ውስጥ የተፈጠረ የሕፃን ሞት ለአደራ ቤተሰብ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ተቋም፣ ለጉዳይ ስራ አስኪያጅ እና ለሚመለከተው የመንግሥት አካል 24 ሰአት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ጥቆማ መደረግ አለበት።

## ንኡስ ክፍል አምስት
## ጉዲፈቻ

## 44. የጉዲፈቻ አገልግሎት አሰጣጥ መሰረታዊ መርሆዎች እና ዓላማዎች

1) የሀገር ውስጥ ጉዲፈቻ በአንድ ኢትዮጵያዊ ሕፃንና በአንድ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ባለው ሰው መካከል በኢትዮጵያ ህግ መሰረት የሚፈጸም ቋሚ የልጅና የወላጅ ግንኙነትን የሚፈጥር ትስስር ሆኖ በፍርድ ቤት መጽደቅ አለበት፡፡
2) ሕፃኑ ከወላጅ ወይም ከተገኘበት ቤተሰብ ጋር ያለውን የስጋ ዝምድና እንደተጠበቀ ይቆያል፣ ለሁሉም ዓላማዎች በጉዲፈቻ አድራጊ እና በጉዲፈቻ ሕፃኑ መካከል ሕጋዊ የሆነ ጥብቅ ግንኙነትን ይፈጥራል።

3) ጉዲፈቻ ካለው የዘላቂነት ባህሪው የተነሣ ከወላጆቹ ጋር መሆን ለማይችል ሕፃን ቋሚ መፍትሔ እንጂ ውጤቱ እንደ አማራጭ ክብካቤ ተደርጎ አይወሰድም። ከአማራጭ ክብካቤ ጋር የተያያዙ መርሆዎች

ሕፃኑ ከወላጆቹ ከተነጠለ እና በአማራጭ ክብካቤ ውስጥ ከተመደበ እንዲሁም ሕፃኑ በእጩ የጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰብ ውስጥ ተመድቦ ጉዲፈቻው እንዲጸድቅ የፍርድ ቤት ውሳኔን በሚጠብቅበት ጊዜ ብቻ ወይም በሌላ መልኩ በዚህ መመሪያ ውስጥ በግልጽ እንደተቀመጠው ተፈጻሚ ይሆናሉ።

4) የቁሳቁስ ድህነት ለአንድ ሕፃን ከወላጆቹ ወይም የተቋጥሮ ዝምድና ካለው ቤተሰቦቹ ለመነጠል እና ለጉዲፈቻ መሰጠት ምክንያት አይሆንም። ቤተሰቦች ልጆቻቸውን መንከባከብ እንዲችሉ የሚያስችሏቸውን የማኅበራዊ ጥበቃ እና የስፖንሰርሺፕ ፕሮግራሞችን እንዲሁም ሌሎች የድጋፍ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ አስፈላጊ የሆኑ ጥረቶች ሁሉ ሊደረጉ ይገባል።

5) ጉዲፈቻ ለመጀመር እርምጃዎች ከመወሰዳቸው በፊት፣ ለወላጆች ወይም ለአሳዳጊዎች አግባብነት ባለው ቢሮ አማካኝነት ስምምነታቸውን ለመስጠት፣ የጉዲፈቻ ዘላቂነትን ለመገንዘብ፣ እንዲሁም ጉዲፈቻው በሕፃኑ፣ በወላጆች ወይም በአሳዳጊዎች ወይም በሞግዚት ላይ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ለመረዳት የሚያስችል ምክር እና ሥልጠና ሊሰጣቸው ይገባል።

6) ጉዲፈቻ አማራጭ የሚሆነው አንድ ሕፃን ከወላጁ ጋር መኖር እንደማይችል ወይም የተቋጥሮ ዝምድና ካላቸው የቤተሰብ አባላት ክብካቤን ማግኘት እንደማይችል በማረጋገጥ ሁሉም ምክንያታዊ ጥረቶች ከተደረጉ በኋላ ብቻ ነው።

7) ጉዲፈቻ ተስማሚ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሁሉም ሂደቶች ሳይጓተቱ መጠናቀቅ አለባቸው። ዕጩ የጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰቦች ብቁ ሆነው ሲገኙ፣ ዕድሜያቸው ከሦስት (3) ዓመት በታች ለሆኑ እና ልዩ ፍላጎት ላላቸው ሕፃናት ቅድሚያ ሊሰጥ ይገባል።

8) ሕፃናትን በጉዲፈቻ የመመደብ ዋና መርህ የሕፃኑን ጥቅም እና ደህንነት ቅደሚያ መስጠት ነው።

9) የሕፃናቱን ጥቅም እና ደህንነት ያላማከለ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር እህትማማቾች እና ወንድማማቾች በአንድ የጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰብ ውስጥ ሊመደቡ ይገባል።

10) የጉዲፈቻ ምደባ በሚወሰንበት ጊዜ፣ የሕፃኑ የትውልድ ቦታ፣ የሃይማኖት፣ የባህል እና የቋንቋ መሠረቶች በሕፃኑ ቀጣይ አስተዳደግ ውስጥ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል።

11) የሕፃኑ ጥቅም እና ደህንነት ያማከለ ሆኖ ሲገኝ ክልል ተሻጋሪ ጉዲፈቻ ሊመቻች ይችላል።

12) ለጉዲፈቻ ቤተሰብነት ብቁ ሆነው ከተገኙ፣ ለሕፃኑ የቤተሰብ አባላት ወይም የተቋጥሮ ዝምድና ላለው ቤተሰብ ቅድሚያ ሊሰጥ ይገባል።

13) የሕፃኑን ጉዲፈቻ መደረግ በተመለከተ ለጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋም፣ ለማኅበራዊ ሠራተኛ፣ ለወላጅ፣ ለተቋጥሮ ዝምድና ቤተሰብ ወይም ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ምንም አይነት ዋጋ ያላቸው ነገሮች መስጠት የለበትም።

## 45. በጉዲፈቻ ተጠቃሚ ስለሚሆኑ ሕፃናት

1) በጉዲፈቻ አማራጭ የህጻናት እንክብካቤ ተጠቃሚ የሚሆን ህጻን ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች መሆን አለበት፡፡

2) በጉዲፈቻ አማራጭ የህጻናት እንክብካቤ ተጠቃሚ የሚሆነው ህጻን እድሜው አሥር ዓመትና ከዛ በላይ ከሆነው የጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰቡ ጋር ለመኖር ፈቃደኛነቱን መግለጽ አለበት፡፡

3) ከጉዲፈቻ አድራጊው ቤተሰብ አንደኛው የትዳር አጋር የሌላውን የትዳር አጋር ልጅ በጉዲፈቻ ሊወስድ ይችላል፡፡

4) ተጥለው የተገኙ ህፃኑናትን ለጉዲፈቻ ቤተሰብ ለመስጠት ወላጆች ወይም የተቋጥሮ ዝምድና ያላቸው የቤተሰብ አባላት ሊገኙ የማይችሉ መሆናቸውን ወይም ቢያንስ ለስድስት ወራት የተሟላ የማፈላለግ ጥረት ተደርጎ ያልተገኙ መሆናቸው በማስረጃ መረጋገጥ አለበት፡፡

5) ወላጅ፣ ሞግዚት ወይም የተቋጥሮ ዝምድና ያለው ቤተሰብ ሊገኝለት ያልቻለ ወይም አንዱን ወላጅ በሞት ያጣ ህፃን ወይም፣ ሁለቱን ወላጆች በሞት ያጣ እና ሕፃኑን ለመንከባከብ ፈቃደኛ የሆነ ሞግዚት ወይም የተቋጥሮ ዝምድና ያለው ቤተሰብ ተለይቶ ማግኘት ካልተቻለ፣ አንዱን ወይም ሁለቱንም ወላጅ በሞት ያጣ ህፃን ነገር ግን የቤተሰብ አባላት ተገኝተው ለጉዲፈቻ ብቁ ሆነው ካልተገኙ ህጻኑን ለጉዲፈቻ ቤተሰብ ለመስጠት ብቁ ያደርገዋል።

6) ወላጆች በጤና እክል ወይም በአካል ጉዳት ምክንያት ሕፃኑን ለመንከባከብ አለመቻላቸው በሕክምና ቦርድ ሲረጋገጥ ወይም በኢኮኖሚ አቅም ማነስ ምክንያት ሕፃኑን ለመንከባከብና ድጋፍ ለማድረግ እንደማይችሉ የሚገልፅ ማስረጃ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ሲቀርብ ህጻኑን ለጉዲፈቻ ቤተሰብ ለመስጠት ይቻላል።

7) በዚህ መመሪያ ውስጥ በተጠቀሰው የጉዳይ አያያዝ ሂደት መሠረት፣ ከስድስት ወራት ላላነሰ ጊዜ በተደረጉ እና በተመዘገቡ የቤተሰብ ፍለጋ ጥረቶች ወላጅ፣ ሞግዚት ወይም የቅርብ ዘመድ ተንከባካቢ ሊገኝ ካልቻለ ሕፃኑ ያለወላጅ ክብካቤ የቀረ ሕፃን እንደሆነ ተቆጥሮ ለጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰብ ሊሰጥ ይችላል፡፡

8) ሕፃኑ በተቋማዊ ክብካቤ ውስጥ የሚኖር እና ቋሚ ምደባ የሚያስፈልገው ከሆነ፣ ወላጆችን ወይም የቤተሰብ አባላትን ፈልጎ ለማግኘት ጥረቶች ከተደረጉ እና ሌሎች የአማራጭ ክብካቤ ዓይነቶች የሕፃኑን ጥቅም እና ደህንነት ያላማከሉ መሆኑ ሲረጋገጥ ህጻኑን ለጉዲፈቻ አገልግሎት ብቁ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

9) ህጻኑ ለጉዲፈቻ ቤተሰብ ከተሠጠ በኋላ ወላጆቹ ወይም የተቋጥሮ ዝምድና ያላቸው ቤተሰቦች ቢገኙ የሕፃኑ ከቤተሰቡ ጋር መልሶ ማቀላቀሉ የሕፃኑ ጥቅምን እና ደህንነትን የማያስጠብቅ መሆኑ ከተረጋገጠ ከጉዲፈቻ ቤተሰቡ ጋር ያለው ህጋዊ ግንኙነት አይቋረጥም፡፡

10) ሕፃኑ የተፈናቀለ ወይም ከቤተሰብ የተነጠለ ሲሆንና የሕፃኑ ወላጆች ወይም የተቋጥሮ ዝምድና ያለው ሰው ቢያንስ ለስድስት ወራት ያህል ለመፈለግ አስፈላጊው ጥረቶች ተደርገው ማግኘት ካልተቻለ ህጻኑ ለጉዲፈቻ አገልግሎት ብቁ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

11) የሕፃኑ ወላጆች ወይም ሞግዚት ሕፃኑ ላይ ጥቃት እና ቸል የማለት ድርጊት ከፈጸሙ ወይም ሆን ብለው ለጥቃት እና ቸል መባል እንዲጋለጥ ምክንያት መሆናቸው በፍርድ ቤት ወይም በሚመለከተው የመንግሥት አካል ከተረጋገጠ እና የአደራ ቤተሰብ እና የተቋጥሮ ዝምድና ክብካቤን ጨምሮ ሌሎች አማራጭ የክብካቤ አይነቶች የሕፃኑን ጥቅም እና ደህንነት የማያረጋግጡ ሆነው ሲገኙ ህጻኑን የጉዲፈቻ አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል፡፡

## 46. የጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰብ ብቁነት

1) አንድ አመልካች ለአገር ውስጥ ጉዲፈቻ ብቁ የሚሆነው የሚከተሉትን ሲያሟላ ነው፡-

ሀ) የሚመደበው ቤተሰብ ለሕፃኑ ጥቅም እና ደህንነትን ተስማሚ መሆኑ ሲረጋገጥ፣ ለሕፃኑ የተቋጥሮ ዝምድና ላላቸው የቤተሰብ አባላት ቅድሚያ መሰጠት አለበት።

ለ) በዜግነት ኢትዮጵያዊ የሆነ እና በጉዲፈቻ ለማሳደግ ከማመልከቻው አስቀድሞ ኢትዮጵያ ውስጥ ቢያንስ ለሁለት ዓመታት የኖረ።

ሐ) ማንኛውም ሰው ጉዲፈቻ ለማድረግ ቢያንስ ዕድሜው 25 ዓመት በላይ መሆን ይኖርበታል፣ ጉዲፈቻ አድራጊዎቹ በትዳር የተሳሰሩ ከሆነ አንደኛው የትዳር አጋር 25 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆነ፣ እንዲሁም በሕፃኑና በጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰብ መካከል ያለው የዕድሜ ልዩነት ከፍተኛው 50 ዓመት እና ዝቅተኛው ደግሞ 18 ዓመት ከሆነ።

መ) ሕፃኑን ለማሳደግ የሚያስችል በቂ ገቢ ያለው መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ ማቅረብ የሚችል እና በጉዲፈቻ ማኅበራዊ ሠራተኛው ወይም በጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ የዳሰሳ ጥናት የተረጋገጠ ሲሆን።

ሠ) ለሕፃኑ እንክብካቤ ለመስጠት እና ለማሳደግ የጤና ችግር የሌለባቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ እውቅና ካለው የጤና ተቋም ማቅረብ የሚችል።

ረ) ከሰብአዊ መብት ጥሰት ጋር በተያያዘ ወንጀል ያልተከሰሰና ያልተቀጣ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማቅረብ የሚችል።

ሰ) ጉዲፈቻ አድራጊው ያገባ ከሆነ የጋብቻ የምስክር ወረቀት፣ ያላገባ ከሆነ ያላገባ መሆኑን የሚገልፅ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል።

ሸ) አመልካች ያገባ ከሆነ፣ ሕፃኑ በጉዲፈቻ ለማሳደግ የትዳር አጋሩን ስምምነት በጽሁፍ ማቅረብ የሚችል።

ቀ) ቢያንስ ለሁለት ዓመታት አመልካቹን ከሚያውቁ የሃይማት ተቋም፣ የአመልካች ቀጣሪ እና ከቅርብ የማህበረሰብ አባል የመልካም ሥነ-ምግባር ምስክርነት ማቅረብ የሚችል።

በ) ህጻኑ የተቋጠሮ ዝምድና ላላቸው የቤተሰብ አባላት በጉዲፈቻ ካልተሰጠ በስተቀር ቅድሚያ ባለትዳር ለሆኑ ዕጩ የጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰቦች መሰጠት አለበት።

ተ) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) (በ) እንደተጠበቀ ሆኖ አንድን ህጻን ላላገባ ወይም የትደራ አጋሩ ለሞተበት ወይም ትዳሩን በፍቺ ላቋረጠ ሰው ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 47. የጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና ማኅበራዊ ሠራተኞች ዝቅተኛ መስፈርቶች

### 1) የጉዲፈቻ ማኅበራዊ ሠራተኞች/የጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ዝግጅት እና ብቃት

ሀ) በተለያዩ ደረጃዎች በጉዲፈቻ ላይ እንዲሁም ከጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር የሚሰሩ የመንግሥት አካላት እና የማኅበራዊ ሠራተኞች ተዛማጅ ሙያዊ ብቃት እና ልምድ ሊኖራቸው ይገባል።

ለ) ለእያንዳንዱ የሥራ መደብ ተፈላጊውን የትምህርት ደረጃ ወይም ብቃት ወይም የሥራ ልምድ በግልጽ የሚያስቀምጥ ወቅቱን የጠበቀ የሥራ ዝርዝር መኖር አለበት።

ሐ) በጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ተቀጥረው የሚሠሩ ሠራተኞች ዕውቀታቸውን እና ልምዳቸውን መጠበቅ እና ማዳበር አለባቸው። የጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ ለሰራተኞቹ ቀጣይነት ያለው የእድገት እና የሥልጠና እድሎችን እንዲያገኙ ማመቻቸት ይገባዋል።

መ) በጉዲፈቻ ላይ የሚሠራ ማንኛውም ሰው በጉዲፈቻ ሊሰጡ ስለሚችሉ ወይም እንዲሰጡ ስለታሰቡ ሕፃናት የሚያውቁትን መረጃ እና የኋላ ታሪክ በሚስጥር የመጠበቅ ሃላፊነት አለባቸው፡፡

ሠ) በጉዲፈቻ ስራ ላይ ለመስራት የሚመደቡ የጉዳይ ሰራተኞችን የሚመለከተው ፈቃድ ሰጪ ባለስልጣን መመዝገብ አለባቸው፡፡ ሚኒስቴሩ በጉዳይ ሰራተኛ ለመመደብ የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ይወስናል፡፡

ረ) የጉዲፈቻ ማኅበራዊ ሠራተኞች ከፖሊስ ከወንጀል ነፃ መሆናቸውን የሚገልፅ የምስክር ወረቀት እንዲሁም ሁለት የመልካም ሥነ-ምግባር ምስክሮች ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

### 2) በጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪዎች እና በጉዲፈቻ ዙሪያ ግንዛቤን መፍጠር እና ማስተዋወቅ

ሀ) የጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከመንግሥት እና ሌሎች በአገልግሎቱ ላይ ከሚሰሩ ባለድርሻ አካላት ጋር በጉዲፈቻ ዙሪያ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የስልጠና ፕሮግራሞችን መቅረጽ እና መተግበር አለባቸው።

ለ) የጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን እና ቴክኒኮችን በመጠቀም ብቁ የጉዲፈቻ ቤተሰቦችን ለመመልመል አላማ ያደረጉ የግንዛቤ ማስጨበጫ መልእክቶችን በማስተላለፍ በጉዲፈቻ ቤተሰብ አገልግሎት ዙሪያ ህብረተሰቡን የማሳወቅ ሃላፊነት አለባቸው፡፡

ሐ) የሕፃናትን የግል መረጃ፣ ታሪኮች፣ ምስል፣ ተንቀሳቃሽ ምስል ወይም ሌሎች ምስሎችን ሕጋዊ ሥልጣን ላለው አካል ካልሆነ በስተቀር ማሳየት ወይም ማስተላለፍ አይቻልም።

መ) ዕጩ የጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰቦች በግንዛቤ ማስጨበጫ ወይም ቅስቀሳ ላይ በመሳተፋቸው ምክንያት ምንም ዓይነት የስጦታ ወይም የገንዘብ ድጋፍ እንደሚደረግላቸው ቃል ሊገባላቸው አይገባም።

ሠ) የጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከመንግሥት እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በጉዲፈቻ ዙርያ የሚነሱ የተሳሳቱ አስተሳሰቦችንና ልማዶችን ለማስተካከል የሚያስችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ማዘጋጀት አለባቸው።

ረ) አግባብነት ያለው ቢሮ ወይም የጉዲፈቻ አገልግሎት እንዲሰጥ የተወከለ ተቋማት ዕጩ የጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰቦች የጉዲፈቻን ሕጋዊ አንደምታዎች፣ ተግባር እና ኃላፊነቶችን እንዲሁም በኢትዮጵያ የጉዲፈቻን አፈጻጸም ሂደት እንዲገነዘቡ የሚያስችል አስፈላጊ ግንዛቤ ማስጨበጥ አለባቸው።

## 3) ዕጩ የጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰቦች ምልመላ፣ የዳሰሳ ጥናት፣ ሥልጠና እና ብቁነት መወሰን

ሀ) የጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ክብካቤን ሊሰጧቸው የሚችሉ ሕፃናትን ፍላጎቶች ለማሟላት የሚችሉ የጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰቦችን መመልመል፣ ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፣ ማሰልጠን እና ብቁነታቸውን መወሰን እንዲሁም ለጉዲፈቻ ምደባ ብቁ የሚሆኑ ሕፃናትን ወቅታዊ እና የወደፊት ፍላጎቶች የመለየት ሃላፊነት አልባቸው።

ለ) የጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከመንግሥት ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ብቁ የጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰቦች ህጻናትን በጉዲፈቻ ወስደው እንዲያሳድጉ ለማበረታታት ውጤታማ ስልት መተግበር አለባቸው።

ሐ) የጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰቦች ለመሆን ፍላጎት ያሳዩ ሰዎች ምልመላ ያለ አድሎኦ፣ በግልጽ፣ በአክብሮት መፈጸም አለበት፣ እንዲሁም ዝርዝር መረጃቸው በምስጢር መያዝ ይኖርበታል።

መ) ዕጩ የጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰብ ለመሆን ለሚያመለክቱ ሰዎችወቅታዊ እና ተገቢ የሆነ መረጃ ሊሰጣቸው እንዲሁም ማመልከቻቸው ስለ ደረሰበት ደረጃና ውሳኔ በታቸለ ፍጥነት ምላሽ ሊሰጣቸው ይገባል።

ሠ) ለዕጩ የጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰብነት የታሰቡ ሁሉም ግለሰቦች ሕፃኑን ለመንከባከብ ብቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ አጠቃላይ የዳሰሳ ጥናት እና የቤት ለቤት የዳሰሳ ጥናት ጉብኝት ሂደት ውስጥ ማለፍ አለባቸው። እንዲሁም አጠቃላይ የዳሰሳ ጥናቱ እና የቤት ለቤት ዳሰሳ ጉብኝት ግኝቶች ተገቢ በሆኑ ቅጾች ላይ መሞላት አለባቸው።

ረ) የቤት ለቤት እና ሌሎች የዳሰሳ ጥናቶች በዕጩ የጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰብ መኖሪያ ቤት ውስጥ ያሉ የሕፃናት ዕድሜ እና ፆታ፣ ከሕፃኑ ወላጅ ወይም ወላጆች መኖሪያ ጋር ያለውን ቅርበት፣ ከዕጩ ጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰቡ የጤና፣ የኢኮኖሚ፣ የባህል፣ የሃይማኖት እንዲሁም የቤተሰብ የኋላ ታሪክን የሚመለከቱ መረጃዎችን በዝርዝር ማካተት አለባቸው።

ሰ) የዕጩ ጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰቦች ህፃናቱን በመንከባከብ ወቅት ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ ጉዳዮችን በብቃት መወጣት የሚያስችሏቸውን ስልቶች፣ የሚያስፍልጓቸውን ወይም ያሏቸውን ብቃቶች እና ጥንካሬዎች በምክር አገልግሎት እንዲሁም ሌሎች የማስተማሪያ መንገዶችን በመጠበቀም እንዲያዳብሩ መደረግ አለበት።

ሸ) ዕጩ ጉዲፈቻ ቤተሰቦች፣ ለአንድ ሕፃን ደህንነቱን በተጠበቀ እና ሃላፊነት በተሞላ መንገድ የመንከባከብ እንዲሁም ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ሕፃናት የዕድገት ፍላጎቶቻቸውን የሚሟላት ብቃታቸው ታይቶ ለጉዲፈቻ ቤተሰብነት በእጩነት ይመዘገባሉ።

ቀ) ብቁነታቸው የተረጋገጠ የጉዲፈቻ ቤተሰቦች ብክብካቤአቸው ስር ያሉ ሕፃናትን በእኩልነት መንከባከብ፣ ያላቸውን የባህል ልዩነት ማክበር እና ሕፃናቱን በሚመለከቱ ውሳኔዎች ውስጥ ህጻናቱ እንዲሳተፉ ማድረግ አለባቸው።

በ) ከሕፃኑ የጉዲፈቻ ምደባ አስቀድሞ፣ የሚመለከተው የመንግሥት አካል ወይም የጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ወይም የጉዲፈቻ ጉዳይ ሰራተኛ ለጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰቡ የሕፃናት ጥበቃ ሥርዓቶችን፣ አዎንታዊ የሕፃናት ባሕርይ ግንባታን፣ ቤተሰብን ማጠናከርን እና አቅም ማሳደግን ጨምሮ አስፈላጊውን የሥነ-ልቦና ዝግጅት እንዲያደርጉ የሚያስችል ተገቢ ሥልጠና መስጠት አለበት። ሥልጠናው እንደ አስፈላጊነቱ አዎንታዊ የልጅ አስተዳደግ፣ ልዩ ፍላጎቶች ላላቸው ሕፃናት ክብካቤን መስጠት ላይ ያተኮሩ እና የመሳሰሉ ርዕሶችን ማካተት አለበት።

ተ) በጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ውስጥ የሚሰራ ሠራተኛ በተቀጠረበት ድርጅት በኩል ሕፃን በጉዲፈቻ ለማሳደግ የሚያመለክት ከሆነ የአመልካቹን ብቁነት ለማረጋገጥ የሚከናወነው የቤት ለቤት የዳሰሳ ጥናት ጉብኝት እና የግምገማ ሪፖርትበሌላ ገለልተኛ በሆነ የጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋም እና ማህበራዊ ሰራተኛ በኩል መከናወን አለበት፡፡

## 4) የሕፃናትን ፍላጎቶች የሚያሟላ ማጣመር፣ ማቀራረብ፣ ትሥሥር እና ምደባ

ሀ) ለጉዲፈቻ የተለየውን ሕፃን በጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰብ ጋር ለመመደብ የሦስት ወር የመጣበቅ እና ትስስር ጊዜ በኋላ ብቻ መሆን አለበት።

ለ) እጩ የጉዲፈቻ አድራጊው ቤተሰብ በምደባው መጽደቅ ከመስማማቱ በፊት የጉዲፈቻ አገልገሎት ሰጪው ተቋም ወይም የማኀበራዊ ሠራተኛው ስለ ሕፃኑ የኋላ ታሪክ፣ የጤና ሁኔታ፣ የሥነ-ልቦና እና የዕድገት ፍላጎቶች እንዲሁም ሕፃኑን መንከባከብ ስለሚያስከትላቸው ውጤቶች እጩ ቤተሰቡ የተሟላ ግንዛቤ እንዲኖረው ማድረግ አለባቸው፡፡

ሐ) የጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ለቤተሰብ ሕፃንን ከመፈለግ ይልቅ የአንድን ሕፃን የግል ፍላጎቶችን ለማሟላት ብቁ የሆነ የጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰብን መፈለግ ላይ ትኩረት ሊያረግ ይገባል።

መ) ከሕፃኑ ጋር ቅርርብ እና ትሥሥር በሚደረግበት ጊዜ አስቀድሞ የጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰቦች ስለ ሕፃኑ የተሻለ ለመረዳት እና ከሕፃኑ ጋር ለመጣመር እንዲወስኑ የሚያስችላቸውን የጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ወይም ማኀበራዊ ሠራተኛው እጅ የሚገኝ የፎቶ እና የዳሰሳ ጥናት ሪፖርት ጨምሮ ማንኛውም ሕፃኑን የሚመለከት መረጃ ማግኘት አለባቸው።

ሠ) የጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ወይም ማኀበራዊ ሠራተኛው የጉዲፈቻ ቤተሰቦች ልዩ ፍላጎት ካለው ሕፃን ጋር በሚያጣመሩበት ጊዜ ወደፊት የሚገጥሟቸውን ተግዳሮቶች ለመቋቋም የሚያስችሉዋቸውን ጥንካሬዎች፣ ልምዶች እና ክህሎቶች እንዳላቸው መገንዘብ አለባቸው።

ረ) በተከናወኑ የማጣመር ተግባራት ላይ በመመስረት የጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪው ተቋም ወይም ማኀበራዊ ሠራተኛው ሕፃኑ ከዕጩ የጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰቡ ጋር እንዲተዋወቅ የሚደረገው በእጩ የጉዲፈቻ አድራጊው መኖሪያ ቤት መሆን አለበት፡፡

ሰ) የጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰብ እና ጉዲፈቻ ተደራጊ ሕፃንን በማስተዋወቅ ሂደት ጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰቦች፣ ማኅበራዊ ሠራተኛውና ሕፃኑ መገኘት አለባቸው፡፡ እንዲሁም በጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰብ ውስጥ የሚኖሩ ሌሎች ሕፃናት ሊገኙ የማይችሉበት ሁኔታ ካልኖረ በስተቀር ህጻናቱ ባሉበት መከናወን አለበት፡፡

ሸ) ሁሉም የቅድመ ምደባ እንዲሁም የማቀራረብ እና ትስስር በሚካሄድበት ጊዜ የማኅበራዊ ሠራተኞች ክትትል ሊያደርጉና በየጊዜ የሚኖረውን ለውጥ የሚያመላክት ሪፖርት በአግባቡ ሊሰነዱ ይገባል።

ቀ) የጉዲፈቻ ስምምነት ውል በጉዲፈቻ አድራጊው ቤተሰብ እና በሕፃኑ ወላጅ ወይም በሞግዚትነት በሚያስተዳድር አካል መካከል መፈጸም አለበት። ስምምነቱም የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡፡

1) የሕፃኑ እና የጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰቡ ስም፣ አድራሻ እና ፎቶግራፍ፣

2) የሕፃኑ የምደባ ቀን፣

3) የውል ፈጻሚ ወገኖች ግዴታዎች ማለትም ሕክምና፣ ትምህርት፣ ልብስ፣ መጠለያ፣ ምግብ፣ የሕግ ጥበቃ እና የመሳሰሉ የሕፃኑን መሠረታዊ ፍላጎቶች ማሟላት እንዲሁም ሌሎች በቤተሰቡ ሊሰጡ የሚገባቸው ድጋፎች የሕፃኑ ደህንነት እና ስኬታማ ዕድገት ማረጋገጥ፣

4) የጉዲፈቻ ውሳኔ ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ ለሁለት አመት በሚዘልቅ እና ከዚህ በታች በተጠቀሱ የድህረ ጉዲፈቻ አገልግሎት መስፈርቶች መሰረት በሚመለከተው የመንግሥት አካል ወይም በጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋም የሚከናወኑ የክትትል ዘዴዎችን።

በ) ለፍርድ ቤት የሚቀርበው ማመልከቻ በማኅበራዊ ሠራተኛው ወይም በጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋም በሦስት ቅጂ መዘጋጀትና በተቋማቱ ሃላፊዎች መፈረም እንዲሁም በሁለት ምስክሮች ፊርማ መረጋገጥ አለበት።

ተ) የስምምነቱ ግልባጭ ጉዲፈቻውን ለማፅደቅ ሂደት ከቀረበበት የፍርድ ቤት ማመልከቻ ጋር መያያዝ አለበት።

ቸ) ከፍርድ ቤቱ ውሳኔ በኋላ፣ የሚመለከተው የመንግሥት አካል ወይም የጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋም በጉዲፈቻ የተሰጠውን ሕፃን የልደት ምሥክር ወረቀት እዲያገኝ የሚያስችል የድጋፍ ደብዳቤ ለሚመለከተው የመንግስት አካል መጻፍ አለበት።

ኀ) ከፍርድ ቤት ውሳኔ በኋላ፣ የጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰቦች ሕፃኑን ለማለማመድና ከቤተሰቡ ጋር ቅርበት ለመፍጠር እንዲችል ለማድረግ ቀጣሪ መስሪያ ቤቶች ለጉዲፈቻ ቤተሰቦች የድህረ ወሊድ ፈቃድ መስጠት አለባቸው፡፡

## 5) **የድህረ ጉዲፈቻ አገልግሎቶች**

ሀ) የሚሰጠው የድህረ ጉዲፈቻ አገልግሎት ሕፃናቱ ደህንነትና እንክብካቤ የማግኘት ስሜት እንዲሁም ዋጋ እንደተሰጣቸው እንዲሰማቸው የሚያደርግ መሆን አለበት፡፡

ለ) የጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ ወይም ማኅበራዊ ሠራተኛው የድህረ ምደባ ክትትሎች መከናወናቸውን እና ሪፖርት መደረጋቸውን ማረጋገጥ አለበት።

ሐ) የድህረ ጉዲፈቻ አገልግሎቶችን ለመቀጠል የሚያስፈልጉ ምክንያቶች ከሌሉ በስተቀር የድህረ ጉዲፈቻ ክትትል ከሁለት አመት መብለጥ የለበትም። ክትትል በሚደረግበት ሁለት ዓመት ውስጥ ህጻኑ በተመደበበት ቀን፣ እስከ ሁለት አመት ድረስ በየስድስት ወሩ መከናወን አለበት፡፡

መ) የጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪው ተቋም ወይም ማኅበራዊ ሠራተኛው የሕፃኑን መላመድ እና ዕድገት ለመከታተል፣ እንደ አስፈላጊነቱም በችግር ጊዜ የምክር እና ድጋፍ ሰጪ ተጓዳኝ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ለሕፃኑ እና ለጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰቡ ቀጣይነት ያለው ድጋፍ መስጠት ይኖርበታል።

ሠ) የጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪው ወይም የጉዲፈቻ ማኅበራዊ ሠራተኛው የሕፃኑን ሕልውና እና ደህንነት የሚጎዱ ጥቃት፣ ቸል መባል፣ ወይም ሕፃኑን ተቀባይነት ማሳጣት እና ሌሎች ሁኔታዎች ሲኖሩ በዚህ መመሪያ ክፍል ሁለት እና በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 195 መሠረት ሕፃኑን ከጉዲፈቻ ምደባው ለማስወጣት አስፈላጊ ሁኔታዎች ማመቻቸት አለበት።

## 6) የጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ተግባርና ሃላፊነት

ሀ) የጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አግባብ ባለው የመንግስት አካል የተመዘገቡና መንግሥት ለሚያወጣቸው ህጎች ተገዢ መሆን አለባቸው።

ለ) የጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በቂ የሰለጠነ የሰው ሃይል ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው።

ሐ) ብሔራዊ የሕፃናት ጉዳይ ፖሊሲ እና የወጡ የሥነ-ምግባር ደንቦችን በስራ ላይ የመዋል እንዲሁም ለሠራተኞች፣ ለወላጆች ወይም ለእጩ ጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰቦች እና ለማኅበራዊ ሠራተኞች ተደራሽ ማድረግና ስልጠና መስጠት አለባቸው።

መ) የማኅበራዊ ሠራተኞች እና የጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪው ተቋም ሠራተኞች መንግስት ያወጣቸውን ፖሊሲዎች፣ የሥነ-ምግባር ደንብን ለመፈጸም እና በስራቸው ምክንያት ያወቁት ሚስጥር ለመጠበቅ ቃለ መሐላ መፈረም አለባቸው፡፡

ሠ) የሕፃናትን ሕልውናና ደህንነት ለማጎልበት ይቻል ዘንድ ከጉዲፈቻ አገልግሎት ጋር ተያይዞ የቀረበ ቅሬታን ለመቀበል እና ለመፍታት የሚያስችል የቅሬታ አቀባበልና አፈታት ስነ-ስርዓት በሚኒስቴሩ መዘጋጀት አለበት።

ረ) ማንኛውም የጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ትክክለኛ ወይም የታቀዱ የገቢ እና ወጪ መግለጫን፣ የበጀት እና የገንዘብ ዕቅድ እና ያለውን ንብረት የሚያሳይ መዝገብ ሊኖረው ይገባል።

## 7) በሕፃናቱ ላይ ጉዳት ስለመድረሱ የሚቀረቡ አቤቱታዎችና የጥርጣሬ ጥቆማዎች ስለሚስተናገዱበት ሁኔታ

ሀ) ማንኛውም የጉዲፈቻ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም በሕፃናት ላይ ጉዳት ስለመድረሱ አቤቱታ ወይም የጥርጣሬ ጥቆማ ሲደርሰው የሚከተሉትን አሰራሮች በመከተል ጉዳዩን ማጣራት ይኖርበታል፣

1) ጥቆማ ለሚያቅርበው ሕፃን ወይም ማንኛውም ሰው አስተማማኝ ጥበቃ እና ድጋፍ እንዲሰጠው የማድረግ፣
2) የሚቀርቡ አቤቱታዎችን እና ጥርጣሬዎችን ለማጣራት የሚያስችል የህፃናት ጥበቃ የውስጥ መመሪያ የማዘጋጀት፣
3) የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ለማጣራትና ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ስልጠና ለሰራተኞቻቸው የመስጠት፣

4) በሕፃኑ ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛ ከሆነና በወንጀልና በሌሎች ህጎች ጭምር የሚያስጠይቅ ሆኖ ከተገኘ አቤቱታውን ወይም ቅሬታውን የተቀበለው አካል በአስቸኳይ ለሚመለከተው አካል ጥቆማ የማድረግ ሃላፊነት አለበት።

## 8) መረጃዎችን አያያዝ

ሀ) የጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ፍጻሜ ያገኙ የጉዲፈቻ ጉዳዮች፣ ከሕፃኑ የዘር ሐረግ አመጣጥ፣ ከወላጆቹ እና የጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰቦቹ ጋር የተያያዙ መለያ ዝርዝር መረጃዎችን በአግባቡ የመያዝና የመጠበቅ እንዲሁም ብሔራዊ የጉዲፈቻ መዝገብ የመያዝ እና የመጠበቅ ሃላፊነት ለተሰጠው የመንግሥት መስሪያ ቤት በየሶስት ወሩ የድህረ ጉዲፈቻ ሪፓርት የማቅረብ ሃላፊነት አለበት።

ለ) 16 ዓመት የሞላው ህጻን ወይም የጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰቡ ካልሆኑ በስተቀር ማንኛም ሰው የሕፃኑን ማህደር ማየት አይችልም። ሆኖም ህጻኑ ወይም የጉዲፈቻ አድራጊው ከፈቀዱለት ማንኛውም ሰው የህጻኑን ማህደር ማየት ይችላል፡፡

## 9) ጉዲፈቻን ለማረጋገጥ ለፍርድ ቤት የሚቀርቡ የማመልከቻ ሰነዶች እና መስፈርቶች

ሀ) ሕፃኑ ወላጆች ካሉት፣ ሁለቱም ወላጆች በጉዲፈቻው ውሳኔ መስማማታቸውን ለመግለጽ ፍርድ ቤት መቅረብ አለባቸው።

ለ) ሕፃኑ አንድ ወላጅ ብቻ ያለው ከሆነ በህይወት ያለው ወላጁ በጉዲፈቻው መጽደቅ መስማማቱ ለመግለጽ ፍርድ ቤት መቅረብ አለበት።

ሐ) ለፍርድ ቤት የሚቀርበው የጉዲፈቻ ማመልከቻው  የሚከተሉትን ማካተት አለበት፣

1) የህጻኑ የተፈጥሮ የወላጆች ወይም የሞግዚቶቹ እና የዕጩ ጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰቡን ፊርማ እና ስምምነቱ ተፈጻሚ የሚሆንበትን ቀን፣ የህጻኑን ፎቶ ግራፍ የያዘ የጉዲፈቻ ስምምነት፣

2) የተፈጥሮ ወላጆች ወይም የተቋጥሮ ዝምድና ያላቸው ዘመዶች ወይም ሞግዚት/አሳዳጊ ዝርዝር መረጃ እና የሕፃኑ ግለ ታሪክ፣

3) የሕፃኑ የልደት ምሥክር ወረቀት፣ አጭር የሕይወት ታሪክ፣ የጤና ምሥክር ወረቀት፣ እና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶች፣

4) የቤት ለቤት የዳሰሳ ጥናት ሪፓርቶች ግልባጭ፣

5) ከእጩ የጉዲፈቻ አድራጊ ቤተሰቡ ጋር በተያያዘ ማንነታቸውን የሚገልፅ ሰነዶች፣ የገቢ፣ የመልካም ሥነ-ምግባር፣ ከወንጀል ነፃ፣ የጋብቻ ሁኔታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፣ እና በታወቀ የጤና ተቋም የተሰጠ የሙሉ ጤና ምርመራ ምሥክር ወረቀት፣ ከማመልከቻው ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት።

# ክፍል ስምንት

## ማኅበረሰብ አቀፍ ክብካቤ

### 48. ማኅበረሰብ አቀፍ ክብካቤ ዘዴ

1) ማህበረሰብ አቀፍ ክብካቤ ማለት ሕፃኑ በማኅበረሰቡ ውስጥ አገልግሎት የሚያገኝበት እና ከማኅበረሰቡ ጋር ቁርኝት መፍጠሩን የሚያረጋግጥ የክብካቤ አማራጭ ዘዴ ነው፡፡

### 49. ከድጋፍ ጋር ራስን ችሎ መኖር

1) ከድጋፍ ጋር ራስን ችሎ መኖር አገልግሎት ማለት ሕፃናት እና ታዳጊዎች በአገልግሎት ሰጪው ተቋም እውቅና እና የቅርብ ክትትል ውስጥ ራሳቸውን ችለው የሚኖሩበት አማራጭ የክብካቤ ዘዴ ነው።

2) አገልግሎቱ ከሕፃናት እና ታዳጊዎች ጋር በመሆን የሚቀረጽ እና ህጻናቱን ተጠቃሚ የሚያደርግ የአገልግሎት ዓይነት ነው።

3) አገልግሎቱ የሕፃናትን እና የታዳጊዎችን ልዩ ፍላጎት ተደራሽ በማድረግና ያላቸውን ጥንካሬ በማጎልበት ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን እንዲችሉ የሚያደርግ መሆን አለበት፡፡

4) ከድጋፍ ጋር ራስን ችሎ የመኖር አገልግሎቶች እድሜያቸው 14 ለሆኑና ከተለያዩ አማራጭ የሕፃናት ክብካቤ አገልግሎቶች ሙሉ በሙሉ ራስን ወደ መቻል በመሸጋገር ላይ ላሉ ወይም በተለያየ ምክንያት ከቤተሰብ ክብካቤ ውጪ ለሆኑ ሕፃናት እና ታዳጊዎች የሚሰጥ የአገልግሎት አይነት ነው።

5) ከድጋፍ ጋር ራስን ችሎ የመኖር አገልግሎት ዕድሜያቸው 14 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆናቸው ወይም በአንድ ቤት ውስጥ ከአንድ የሚበልጡና የቤተሰቡን የእለት ተእለት የማስተዳደር እና የመንከባከብ ሀላፊነትን የሚወጡ ሕፃናትን እና ታዳጊዎችን ተጠቃሚ ያደርጋል።

6) ህጻናት የዚህ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚሰጠው ውሳኔ የአገልግሎቱ አስፈላጊነትን በሚያረጋግጥ የዳሰሳ ጥናት ላይ በመመስረት የትምህርት፣ የመጠለያ፣ የጤና እና የሕክምና አገልግሎቶች፣ የቅጥር ወይም የሥራ ዕድል፣ የሙያ ሥልጠና፣ የገንዘብ አያያዝ፣ ክህሎቶችን የማዳበር፣ የምክር አገልግሎት፣ የመልሶ ማቋቋም፣ የወሳኝ ኩነት ምዝገባና መረጃ ተጠቃሚነትና ሌሎች አስፈላጊ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ በማድረግ ሕፃናት እና ታዳጊዎችን ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን ለመቻል እንዲዘጋጁ በማገዝ ነው።

### 50. ለአገልግሎቱ የብቁነት መስፈርት

1) የሕፃናትን እና የታዳጊዎችን ከድጋፍ ጋር ራስን ችሎ የመኖር አገልግሎት ተጠቃሚነትን ለመወሰን ከላይ የተዘረዘሩት የብቁነት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ሁኔታዎች መሟላታቸው መረጋገጥ አለበት፡፡

   ሀ) የሕፃኑ ወይም የታዳጊው ዕድሜ 14 ዓመት እና ከዚያ በላይ መሆኑ፣

ለ) በአንድ ቤት ውስጥ ዕድሜው 14 ዓመት የሞላው አንድ ወይም ከአንድ የሚበልጡ ሕፃናት ወይም ታዳጊዎች የቤተሰቡን የእለት ተእለት ህይወታቸውን የማስተዳደር እና የመንከባከብ ሀላፊነት የሚወጡ ሲሆን፣

ሐ) በአማራጭ ክብካቤ ሥር ከስጋ ቤተሰቦቻቸው ጋር ወይም ከተንከባካቢዎቻቸው ጋር መኖር ወይም መልሶ መቀላቀል የማይችሉ ወይም የማይፈልጉ ከ18 እስከ 24 ዓመት ያሉ ታዳጊዎች ሆነው ሲገኙ፣

መ) በሌሎች አማራጭ ክብካቤ ውስጥ ለመካተት እድሜያቸው ያለፈ እና ከድጋፍ ጋር ራስን ችሎ የመኖር አገልግሎት ውስጥ የመካተት ፍላጎት እና ብቁነቱ ያላቸው ሲሆኑ፣

ሠ) ሕፃኑ ወይም ታዳጊው በአዕምሮ የበሰለ፣ በተረጋጋ አእምሮአዊ እና ስሜታዊ ሁኔታ ውስጥ የሚገኝ፣ እንዲሁም በዳሰሳ ጥናት የተረጋገጠ ራስን ችሎ ለመኖር የሚያስችል የሥነ-ልቦና ዝግጁነት ያለው ሲሆን፣

ረ) ሕፃኑ ወይም ታዳጊው ከቤተሰቡ ክብካቤ ውጪ የሆነ እና በሌሎች አማራጭ የሕፃናት ክብካቤ አገልግሎቶች ተጠቃሚ ከሆነ፣

ሰ) ሙሉ በሙሉ ራሱን ችሎ ለመኖር ድጋፍ የሚሻ ሕፃን ወይም ታዳጊ ሲሆን፣

ሸ) አገልግሎቱ የሚጠብቅበትን ሃላፊነቶች ላይ ለመሳተፍ እና ለመወጣት በስምምነት ቅጽ ላይ ለመፈረም ፈቃደኛ ሲሆን ነው፡፡

## 51. የሚሰጡ አገልግሎቶች

1) ከድጋፍ ጋር ራስን ችሎ የመኖር አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚሰጧቸው አገልግሎቶች፣

ሀ) መሠረታዊ ፍላጎቶች (ምግብ፣ መጠለያ እና ልብስ)፣

ለ) መደበኛ ወይም መደበኛ ያልሆነ የትምህርት ድጋፍ፣

ሐ) የሁለተኛ ደረጃ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የትምህርት ድጋፍ፣

መ) ለስራ ስምሪት ማዘጋጀት፣

ሠ) የሙያ ሥልጠና፣

ረ) የበጀትና የገንዘብ አያያዝ ሥልጠናና ልምምድ፣

ሰ) የቤት አያያዝ ሥልጠና፣

ሸ) የጤና አጠባበቅ ትምህርትና ሥጋትን መከላከል፣

ቀ) በመቀራረብ ላይ የተመሰረተ አዎንታዊ የባህሪ፣ የሥነ-ምግባርና የአመለካከት ለውጥን ግብ ያደረገ ማማከር እና ክትትል፣

በ) ከማህበረሰቡ ጋር የማዋሀድ እና የማኅበራዊ ክህሎቶች ሥልጠና፣

ተ) ወጣት-መር ትምህርት እና ሥራን ግብ ያደረገ የሽግግር እንዲሁም የዘላቂነት እቅድ ዝግጅት፣

ቸ) የሕክምና እና የጤና አገልግሎቶች፣

ኀ) ከአካል ጉዳት ጋር ለሚኖሩ ህጻናት ተመጣጣኝ ማመቻቸት፣

ነ) የህግ ድጋፍ አገልግሎት፣

2) ከድጋፍ ጋር ራስን ችሎ የመኖር አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ራሳቸው ችለው ለመኖር ብቁ የሆኑ ታዳጊዎችን የሚደግፉ የሽግግር ዕቅድ የማዘጋጀት እና እቅዱ ቀጣይነትን ያለው አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ የሚያመቻች መሆኑን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለባቸው፡፡

## 52. ልየታ

1) ከድጋፍ ጋር ራስን ችሎ የመኖር አገልግሎት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ፣ ከማህበረሰቡ ድጋፍ የማያገኙ እና ብቻቸውን የሚኖሩ ተጋላጭ ሕፃናትን ወይም ታዳጊዎችን በማኅበረሰቡ አባላት ወይም በማኅበረሰብ አቀፍ ጥምረቶች ሊለዩ ይችላሉ።

2) በዕድሜያቸው ምክንያት በአማራጭ ክብካቤ መታቀፍ የማይችሉ፣ ከቤተሰብ ጋር መቀላቀል የማይችሉ ወይም የማይፈልጉ ሆኖም ከድጋፍ ጋር ራስን ችሎ የመኖር አገልግሎት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ሕፃናትን ወይም ታዳጊዎችን በሕፃናት ጥበቃ ባለሙያ፣ በጉዳይ አያያዝ ስራ አስኪያጅ ወይም በአደራ ቤተሰብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሊለዩ ይችላሉ።

3) የልየታ እና የዳሰሳ ጥናቱ የሕፃናቱን ወይም ታዳጊዎቹን ብቁነት ያረጋገጠ እና ሌሎች የቤተሰብ ተኮር ክብካቤ አማራጮችን በሚገባ የፈተሸ መሆን አለበት።

4) ሌሎች የክብካቤ አይነቶች የሕፃናቱን ወይም የታዳጊዎቹን ጥቅም እና ደህነትን ያላሟሉ ወይም ተገቢ ሆነው ካልተገኙ ወይም ሕፃናቱ ወይም ታዳጊዎቹ ፈቃደኛ ያለመሆናቸው ከመረጋገጡ በፊት ከድጋፍ ጋር ራስን ችሎ የመኖር አገልግሎት እንደ አማራጭ መወሰድ የለበትም፡፡

5) የሕፃናቱን ወይም የታዳጊዎችን ከድጋፍ ጋር ራስን ችሎ በመኖር አገልግሎት ውስጥ ድጋፍ ለማግኘት ብቁነታቸውን የሚያረጋግጥ የዳሰሳ ጥናት መካሄድ አለበት፡፡

6) በዳሰሳ ጥናቱ ወቅት የተገኘውን የሕፃኑን ወይም የታዳጊውን መረጃ በጉዳይ አያያዝ ሂደት ውስጥ ለሕፃናቱ ወይም ታዳጊዎቹ መካሪ ለመለየት፣ ከድጋፍ ጋር ራስን ችሎ ወደ መኖር አገልግሎት የሚያደርጉትን ሽግግር ለማገዝ እና ከማህበረሰቡ ጋር ለማቀላቀል ሂደትን ለመገምገም  ጥቅም ላይ መዋል አለበት፡፡

## 53. መካሪዎች (ሜንቶር)

1) ሕፃኑ ወይም ታዳጊው ወደ ማህበረሰብ በሚቀላቀልበት ጊዜ ሙሉ በሙሉ ከማህበረሰቡ ጋር እስኪቀላቀል፣ እያንዳንዱ በቤተሰብ ውስጥ የሚገኝ ሕፃን ወይምታዳጊ ራሱን ችሎ መኖር እስኪችል እና ሕፃናቱን ወይም ታዳጊዎቹን ያማከለ ዘላቂ አማራጭ እስኪገኝ ድረስ መካሪው ስሜታዊ፣ ማህበራዊ እና ተግባራዊ ድጋፍ መስጠት ይኖርበታል።

2) መካሪው ከድጋፍ ጋር ራስን ችሎ የመኖር አገልግሎት እና የምክር አገልግሎቱ ጥገኝነትን በማይፈጥር መልኩ ማከናወን አለበት፡፡

3) ሕፃናትን ወይም ታዳጊዎችን ከሌላ አማራጭ ክብካቤ ወደ ከድጋፍ ጋር ራስን ችሎ የመኖር አገልግሎት ለማዘዋወር ዝግጅት በሚደረግበት ወቅት የጉዳይ ባለሙያው ሕፃናቱ ወይም ታዳጊዎቹ በሚገቡበት ማህበረሰብ ውስጥ ቢያንስ አንድ በመካሪነት ሊያገለግል የሚችል እንዲሁም እርዳታ እና ምክር በነጻነት ሊጠይቁ የሚችሉት አዋቂ ሰው  ሕፃናቱን ወይም ታዳጊዎቹን በማሳተፍ መለየት አለበት።

4) ከድጋፍ ጋር ራስን ችሎ የመኖር አገልግሎት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ከማህበረሰቡ ድጋፍ የማያገኙ እና ብቻቸውን የሚኖሩ ተጋላጭ ሕፃናትን ወይም ታዳጊዎችን በማኅበረሰቡ አባላት እንደተለዩ  የማኅበረሰብ አቀፍ ጥምረቶች ወይም የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያዎች በፍጥነት መካሪ መለየት ይኖርባቸዋል።

5) መካሪዎች በህጋዊ መንገድ በማህበረሰብ አቀፍ ጥምረቶች ወይም በሕፃናት ጥበቃ ባለሙያ መመዝገብና የኋላ ታሪካቸውን የተመከተ የዳሰሳ ጥናት መደረጉን ማረጋገጥ አለበት፡፡

6) የመካሪዎች የብቁነት መስፈርቶች፡-

   ሀ) እድሜያቸው ከ25 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ፣

   ለ) ለሕፃኑ ወይም ለታዳጊው ስሜታዊ፣ ማህበራዊ እና ተግባራዊ ድጋፍ ለመስጠት ፍቃደኝነቱ እና ችሎታው ያለው፣

   ሐ) በሕፃኑ ወይም በታዳጊው እምነት የሚጣልበት እና እንደ ድጋፍ ሰጪ የሚታይ፣

   መ) ራሱን ችሎ የሚኖር እንዲሁም ለሕፃናቱ/ታዳጊዎቹን ለማስተማር ወይም ለማሰልጠን የሚያስችል በቂና ተግባራዊ የህይወት ክህሎቶችን ያዳበረ፣

   ሠ) በማኅበረሰቡ ውስጥ የመልካም ባሕሪ እና ጤናማ አኗኗር ምስክርነት  እንዲሁም መልካም ግንኙነት ያለው ማለትም ለሕፃኑ ወይም ለታዳጊው መልካም አርአያ መሆን የሚችል፣

7) መካሪው የሚከተሉት ሚናና እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) መደበኛ ክትትል በማድረግ በቤቱ ውስጥ ለየሚገኙ ሕፃናት/ታዳጊዎች መሰረታዊ ፍላጎቶች መሟላታቸውን ማረጋገጥ እና ህጻናቱ ስላሉበት ሁኔታ ለሕፃናት ጥበቃ ባለሙያ መረጃ የመስጠት፣

ለ) ሕፃናቱን/ታዳጊዎቹን በሕፃናት መብት፣የህይወት ክህሎት፣ ጤናማ አኗኗር፣ የተመጣጠነ አመጋገብ፣ የቤተሰብ ግንኙነት፣ ንጽህና፣ የሥነ-ተዋልዶ ጤና እና የኤች.አይ.ቪ መከላከል ላይ ስልጠና እንዲያገኙ በማመቻቸት ጤናማ ህይወት መኖር እንዲችሉ የማዘጋጀት፣

ሐ) ሕፃናቱ/የታዳጊዎቹ የትምህርት ቤት ወጪዎቻቸው እንዲሸፈኑ እና በቤት ውስጥ የሚገኙ ሕፃናት/ታዳጊዎች በሚገባ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ መሆኑን የማረጋገጥ

መ) ሕፃናቱ/ታዳጊዎቹ በትምህርት ወቅት የሚያስፈልጓቸውን የትምህርት እና የሥነ-ልቦና ድጋፎችን በተመለከተ ከአስተማሪዎቻቸው ጋር መወያየት እና በቅርበት መስራታቸውን የማረጋገጥ፣

ሠ) ሕፃናቱን/ታዳጊዎቹን በመሠረታዊነት በትምህርት፣ በቤት አያያዝ፣ በግብርና፣ በአነስተኛ እና ጥቃቅን የንግድ ሥራ አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ ስልጠናዎችን ማግኘት እንዲችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

ረ) ሕፃናት/ታዳጊዎች ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ለማስቻል በቤት ውስጥ ያሉ እድሜያቸው ለትምህርት ያልደረሰ ሕፃናትን በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኙ የሕፃናት ማቆያ አማራጮችን በመፈለግ/በማመላከት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማመቻቸት፣አለባቸው፡፡

8) ሕፃናቱ/ታዳጊዎቹ በሚገኙበት ማህበረሰብ ውስጥ እንደ መካሪ ሊያገለግል የሚችል ሰው መለየት ካልቻሉ የማህበረሰብ አቀፍ ጥምረቶች ወይም የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያ በሕፃኑ በታዳጊው ዙርያ የሚገኙ ሰዎችን በማሳተፍ መካሪ መለየት እንዲችሉ ያደርጋሉ።

9) የሕፃናቱን ምርጫ መሰረት በማድረግ የሚመደበው መካሪ ፆታን ለይቶ መወሰን ይቻላል፡

10) የማህበረሰብ አቀፍ ጥምረቶች ወይም የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያ ሕፃናቱ/ታዳጊዎቹ ከመካሪዎች የሚጠብቋቸውን አገልግሎቶች እና አማራጭ እጩ መካሪዎች ላይ ከሕፃናቱ/ከታዳጊዎቹ ጋር መወያየት ይጠበቅባቸዋል።

11) የአገልግሎት ሰጪ ተቋም ለአንድ መካሪ የሚመደብለት የጉዳይ ብዛት ሃላፊነቱን በሚገባ እንዳይወጣ ጫና የሚፈጥርበት መሆን የለበትም፡፡

12) የማህበረሰብ አቀፍ ጥምረቶች ወይም የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያው መካሪዎች ሃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት እንዲችሉ የሚያስችሏቸውን ማንኛውም አይነት ድጋፍ መስጠት አለባቸው፡፡

13) የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለመካሪዎች የገንዘብ ድጋፍ ወይም ያወጡትን ወጪን ተመላሽ እንዲደረግላቸው ሲጠይቁ ተገቢውን ድጋፍ ወይም ወጪቸውን የመተካት ሃላፊነት አለባቸው፡፡

14) አግባብነት ያለው ቢሮ ከአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር በመቀናጀት የመካሪዎችን አጠቃላይ ክትትል እና የማስተባበር ተግባርን ያከናውናል።

15) መካሪው አገልግሎቱን መስጠት ማቋረጥ መፈለጉን ሲገልጽ የአገልግሎት ሰጪው ተቋም፣ የማህበረሰብ አቀፍ ጥምረት ወይም የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያው ተተኪ መካሪ መለየት እና መሰየም ይኖርባቸዋል።

## 54. የድጋፍ እና የቅብብሎሽ አገልግሎት

1) አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሕፃናቱ ወይም ታዳጊዎቹ የሚያስፈልጓቸውን አገልግሎቶች በቅድሚያ የመለየት እና የማመቻቸት ሃላፊነት አለባቸው።
2) ለሕፃናቱ ወይም ለታዳጊዎቹ አስፈላጊ ሊሆኑ የሚችሉ አገልግሎቶችን አግባብነት ያለው ቢሮ፣ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ወይም የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያ የአግልግሎት አይነቶችን እና አቅራቢዎችን ልየታ ማካሄድ አለባቸው።
3) በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚሰጡ አግልግሎቶች ዓላማ ሕፃናት ወይም ታዳጊዎች የመቋቋም ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ እና ራሳቸውን ችለው መኖር እንዲችሉ ማብቃት ነው፡፡
4) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (3) መሰረት የሚሰጠው የክህሎት ስልጠናዎች ቢያንስ ራስን የማኅልበት እና ደህንነትን የመጠበቅ፣ አደጋን የመከላከል፣ የገንዘብ አያያዝ፣ የጤና እና የማኅበራዊ ግንዛቤ እንዲሁም የማኅበረሰብ አገልግሎት ተሳትፎን ማካተት አለበት፡፡
5) ሕፃናቱ ወይም ታዳጊዎቹ በሚመርጡት የስራ ወይም የሙያ ዘርፍ አስፈላጊውን ስልጠና ማግኘት ይኖርባቸዋል።
6) ስልጠናውን ተከትሎ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሕፃናቱ ወይም ታዳጊዎቹ በማህበረሰቡ ውስጥ ተቀባይነት ባለው ሥነ-ምግባር መኖር፣ ፍላጎታቸውን በተገቢው መንገድ ለሚመለከተው አካል መግለጽ እና ለራሳቸው መሟገት የሚችሉበት አቅም ላይ መድረሳቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።
7) የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሕፃናቱን ወይም የታዳጊዎቹን ጥቅም እና ደህንነት ያማከለ ሆኖ ሲገኝ ከተገኙበት ቤተሰብ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማበረታታት እና ማስተባበር ይኖርባቸዋል።
8) አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሕፃናቱ ወይም ታዳጊዎቹ ስላለፈ የህይወት ታሪካቸው እንዲያውቁ እንዲሁም ማህበራዊ፣ ሀይማኖታዊ እና ባህላዊ ማንነታቸውን እንዲጠብቁ መርዳት ይጠበቅባቸዋል።
9) ሕፃናቱ ወይም ታዳጊዎቹ የተቋጥሮ ዝምድና ካላቸው የቤተሰብ አባላት፣ ከእህት እና ከወንድም እንዲሁም ከማህበረሰቡ ጋር ያላቸውን ትስስር ማበረታታትና መጠበቅ አስፈላጊ ነው።
10) አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከድጋፍ ጋር ራስን ችሎ የመኖር አገልግሎት ተጠቃሚ ለሆኑ ሕፃናት እና ታዳጊዎች ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን ወጪ የሚሸፍን የገንዘብ ድጎማ የማድረግ ሃላፊነት አለባቸው።
11) የገንዘብ ድጎማው ለቤት ኪራይ፣ ለአገልግሎት ክፍያዎች፣ የቤት ውስጥ መገልገያ እቃዎችን ለሟሟላት፣ ለምግብ፣ ለአልባሳት፣ ለግል ንጽህና መጠበቂያ፣ ለትራንስፖርት፣ ለመዝናኛ ፣ ለአደጋ ጊዜ መጠባበቂያና ለትምህርት መገልገያ መሳሪያዎች ግዢ የሚውል ነው፡፡
12) በከፍተኛ ትምህርት ወይም በስልጠና ተቋማት የሚገኙ የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች በየዓመቱ የአልባሳት እንዲሁም ወርሃዊ የገንዘብ ድጎማ ሊሰጣቸው ይገባል።
13) ሕፃናቱ ወይም ታዳጊዎቹ የመረጡትን የትምህርት ወይም የስልጠና እና የስራ ዘርፍን በተመለከተ ስምምነት ላይ ከተደረሰ በኋላ በመረጡት መስክ ተጠቃሚ መሆን አለባቸው።
14) በትምህርት ወይም በስልጠና ላይ ያሉ ሕፃናት ወይም ታዳጊዎች ትምህርታቸውን ወይም ስልጠናቸውን እንደሚከታተሉበት አካባቢ ወይም የቦታ እርቀት የቤት ኪራይ፣ የኪስ ገንዘብ እና ሌሎች ወጭዎችን መሸፈኛ እንዲያገኙ መደረግ አለበት፡፡
15) አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለሕፃናቱን ወይም ለታዳጊዎቹን የስራ ልምምድ ወይም የቅጥር እድሎችን በማመቻቸት ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን ችለው የመኖር ጥረታችውን የመደገፍ ሀላፊነት አለባቸው።
16) እድሜያቸው 15 እና ከ15 አመት በላይ የሆናቸው ሕፃናት ወይም ታዳጊዎች እራሳቸውን እንዲደግፉ የሚመቻቹላቸው የስራ እድሎች ከትምህርት የማያስተጓጉላቸው፣ ደህንነታቸውን አደጋ ላይ የማይጥል እንዲሁም ለብዝበዛ የማያጋልጣቸው መሆኑን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ማረጋገጥ አለባለቸው፡፡
17) ከድጋፍ ጋር ራስን ችሎ የመኖር አገልግሎት በሕፃናቱ እና በታዳጊዎቹ ልዩ ፍላጎት እና ጥንካሬ ላይ የተመሰረተ ሆኖ የህጻናቱን ወይም የታዳጊዎቹን ተሳትፎን ያማከለ መሆን አለበት።

18) አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ቀጣይነት ያላቸውን እድሜን ያማከለ የሥነ-ተዋልዶ ጤና ስልጠናዎችንና አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ማመቻቸት አለባቸው።

19) የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ሕፃናት እና ታዳጊዎች ጥንካሬያቸውን በመለየት እና በመጠቀም፣ ተግዳሮቶችን ለመቋቋም፣ አገልግሎቶችን ያለእንቅፋት ለማግኘት እና ለመጠቀም እንዲሁም ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው ስኬታማ ህይወት መምራት እንዲችሉ ማገዝ አለባቸው።

## 55. የአገልግሎት ዕቅድ እና ስምምነት

1) በአገልግሎት ዕቅድ ቀረፃ ፣በአገልግሎት አሰጣጥ ጊዜ እና ማግኘት ስለሚገባቸው ክብካቤ በሚደረግ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ሕፃናቱ ወይም ታዳጊዎቹ ተሳታፊ መሆን አለባቸው።

2) የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት በአገልግሎቱ ውስጥ ለመሳተፍ የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን እና የሚጠበቁ ሃላፊነቶችን ያካተተ የአገልግሎት ስምምነት በማዘጋጀት ሕፃናቱ ወይም ታዳጊዎቹ አንበበውት እና ተረድተውት እንዲፈርሙ ማድረግ አለባቸው፣ ስምምነቱም በተጠቃሚዎቹ ማህደር ውስጥ በአግባቡ ተያይዞ መቀመጥ አለበት።

3) ሕፃናት ወይም ታዳጊዎች በአገልግሎት ስምምነቱ የተጠቀሱትን መስፈርቶች እና የሚጠበቁባቸውን ሃላፊነቶች ተላልፈው ሲገኙ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሁኔታውን በመመርመር፣ ችግሩን በመለየት እና ተገቢ እርምጃዎችን በመውሰድ ሕፃናቱ ወይም ታዳጊዎቹ በአገልግሎት ስምምነቱ ላይ የተዘረዘሩትን ምክረ ሃሳቦች እንዲያከብሩ ለማስረዳት አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ አለባቸው።

4) የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ህጻናቱ ወይም ታዳጊዎቹ ወጣቶቹ ራሳቸውን ወደ መቻል ወይም ለአካለ መጠን ለመሸጋገር የሚጠበቅባቸውን ሃላፊነት እንዲያውቁ እና እንዲቀበሉ ማድረግ አለባቸው።

5) የአገልግሎት ስምምነቱ የተመረጠውን የመካሪ ስም፣ግላዊ መረጃ እና አድራሻ ማካተት አለበት።

6) ሕፃኑ ወይም ታዳጊው በመካሪው ላይ ቅሬታ ሲያቀርብ፣ አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ የቅሬታው መነሻ ምክንያቶች ተቀባይነት ያላቸው መሆን እና አለመሆኑን በምርመራ ካጣራ በኋላ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል። ቅሬታው የመካሪ እና የተመካሪን ግንኙነት አደጋ ላይ የሚጥል ሆኖ ሲገኝ መካሪው በሌላ ብቁ መካሪ መተካት ይኖርበታል።

## 56. የአገልግሎት መጠናቀቅ

1) የማህበረሰብ አቀፍ ጥምረቱ፣ የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያው ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ አገልግሎቱን መስጠት ማቋረጥ የሚችለው ሕፃናቱ ወይም ታዳጊዎቹ ሙሉ በሙሉ በራሳቸው መሰረታዊ ፍሎጎቶቻቸውን በማሟላት ሁለንተናዊ ደህንነታቸውን ማስጠበቅ መቻላቸው ሲረጋገጥ ነው፡፡

2) በሕፃቱ ወይም በታዳጊዎቹ እና በመካሪው መካከል በወጣይ የሚኖረው ግንኙነት ድጋፋዊ እንዲሆን ይበረታታል።

## ክፍል ዘጠኝ

## ተቋማዊ ክብካቤ አገልግሎት

### 57. ተቋማዊ ክብካቤ

1) ተቋማዊ ክብካቤ ተገቢውን ሥርዐት በመከተል በመንግሥት ወይም መንግሥታዊ ባልሆነ ድርጅት ወይም በግለሰብ በተቋቋመ ድርጅት አማካኝነት ከቤተሰብ ውጪ ሕፃናት ድጋፍና እንክብካቤ የሚያገኙበት የክብካቤ አይነት ነው። ሆኖም አዳሪ ትምህርት ቤቶች በዚህ አይነት ድጋፍና እንክብካቤ ውስጥ የሚካተቱ አይደሉም፡፡

2) ተቋማዊ ክብካቤ ቤተሰባዊ ክብካቤ ላላገኙ ሕፃናት ከቤተሰብ ውጪ የሚደረግ ጊዜያዊ፣ የአጭር ጊዜና የመጨረሻ አማራጭ የሆነ የክብካቤ አይነት ነው።

3) ከሕፃኑ ልዩ ፍላጎቶች የተነሳ የረዥም ጊዜ ተቋማዊ ክብካቤ የተሻለ አማራጭ እንደሆነ ካልታመነ በስተቀር ተቋማዊ ክብካቤ ጊዜያዊ ምደባ ነው።

4) በተቋማዊ ክብካቤ ሥር የሚሰጡ የድጋፍና የክብካቤ አገልግሎቶች በተቋማት ውስጥ ያሉ ሕፃናትን አካላዊ፣ ሥነ-ልቦናዊና ማኅበራዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት የሚያስችሉ ሆነው ሙያዊ ብቃት ወይም በሰለጠኑና ልምድባላቸውሠራተኞች ይሰጣል፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ(4) መሰረት የሚሰጠው አገልግሎት ሕፃናቱ ከቤተሰቦቻቸው ጋር መልሰው እስከሚቀላቀሉ ወይም ቤተሰብ ተኮር ወደ ሆነ ሌላ አማራጭ እስከሚመደቡ ድረስ ደረጃቸውን ጠብቀው የሚሰጡ ሊሆን ይገባል።

6) ሁኔታዎች ካላስገደዱ በስተቀር አንድ ሕፃን ከሁለት ወር በላይ በተቋም ውስጥ መቆየት የለበትም፡፡

### 58. የተቋማዊ ክብካቤ ዓይነቶች

1) **የተቀናጀ ማኅበረሰብ አቀፍ የሕፃናት ክብካቤ**

   ሀ) ይህ የክብካቤ አይነት በቁጥር ከስምንት ለማይበልጡ ሕፃናት አስፈላጊውን ስልጠና በወሰደ እና በቅጥር በተመደበ አዋቂ ተንከባካቢነት በማህበረሰብ ውስጥ በሚገኝ የመኖሪያ ቤት ውስጥ የሚሠጥ ጊዜያዊ የክብካቤ ዓይነት ነው።

   ለ) በቅጥር የሚመደበው ተንከባካቢ በተቋጥሮ ዝምድና ምክንያት ሕፃናቱን የመንከባከብ ኀላፊነት የሌለበት ወይም በማኅበረሰቡ ውስጥ የአደራ ቤተሰብ ተንከባካቢ ያልሆነ ሰው ሊሆን ይገባል።

   ሐ) በተቀናጀ የማኅበረሰብ አቀፍ የሕፃናት ክብካቤ አገልግሎቶችን ለማስፈጸም፣ ለሕፃኑ ተንከባካቢዎችን ለመመልመልና ለማሠልጠን፣ ፣ ለመደገፍና ለመከታተል ኀላፊነትና ፈቃድ በተሰጠው የክብካቤ አገልግሎት ድርጅት አስተባባሪነት ተፈጻሚ መደረግ አለበት።

   መ) በተቀናጀ የማኅበረሰብ አቀፍ የሕፃናት ክብካቤ አገልግሎት ተጠቃሚ የሚሆኑ ሕፃናት ሌሎች ዘላቂ የክብካቤ አማራጮች እስኪገኙላቸው ድረስ ብቻ በጊዜያዊነት የሚመደቡበት የክብካቤ አይነት ነው፡፡

2) **ልዩ ፍላጎት ላላቸው ሕፃናት አገልግሎት የሚሰጥ ተቋማዊ ክብካቤ**

ሀ) ይህ በተፈጥሮ ወይም በአደጋ በደረሰ የአካል ጉዳት፣ በታወቁ የባሕርይ ችግሮች፣ ወይም በሕክምና ምርመራ ለታወቁ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ሕፃናት አገልግሎት የሚሰጥ ተቋማዊ ክብካቤ ዓይነት ነው።

ለ) ይህ ልዩ ተቋማዊ ክብካቤ ሕፃናቱ ተከታታይና ሙያዊ ክብካቤ እያገኙ እንዲያገግሙ ለመርዳት፣ ወደ ቤተሰባቸው መልሰው እንዲቀላቀሉ ለማዘጋጀት፣ ወደ አማራጭ ቤተሰብ እንዲመደቡ ለማመቻቸት ወይም ራሳቸውን ችለው የሚኖሩበትን ሁኔታ ለመፍጠር በብሔራዊ ሕፃናት ፖሊሲ መሠረት በጊዜያዊነትና ለአጭር ጊዜ የሚሰጥ ነው።

ሐ) ይህንን አይነት ክብካቤ የሚሰጡ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችም ሆኑ ሠራተኞቻቸው በማኅበረሰቡ ውስጥ ለሚኖሩና የተጠቀሱት ልዩ ፍላጎቶች ላላቸው ሕፃናት አገልግሎቶችን መስጠት የሚያስችላቸው ዝግጅት ሊኖራቸው ይገባል።

3) **መደበኛ ተቋማዊ የሕፃናት ክብካቤ**

ሀ) ይህ የክብካቤ አይነት ሥልጣን ባላቸው ባለድርሻ አካላት ለሕፃናቱ ቋሚ የክብካቤ አማራጭ እስከሚያመቻቹ ድረስ ሕፃናት በጊዜያዊነትና ለሽግግር ክብካቤ የሚያገኙበት ተቋም ነው።

ለ) የመደበኛ ተቋማዊ ክብካቤ ተቋማት ሕፃናት ሌላ የቤተሰብ ወይም የማኅበረሰብ-አቀፍ ክብካቤ አማራጮች እስኪመቻችላቸው ድረስ ጊዜያዊና የአጭር ጊዜ ክብካቤ እያገኙ የሚቆዩበት ተቋም ነው፡፡

ሐ) በዚህ ተቋማዊ ክብካቤ ማዕከል የሚመደቡ ሕፃናት ቁጥር የተወሰነ መሆን አለበት። የክብካቤ ተቋማት መቀበል በሚችሉት ከፍተኛ የሕፃናት ቁጥርን የሚወስን ዝርዝር የአፈጻጸም ደረጃ ሚኒስቴሩ ያወጣል።

## 59. የተቋማዊ ክብካቤ ዝርዝር ዓላማዎች

1) የአጭር ጊዜ አማራጭ ክብካቤ የመስጠት፤

2) በተቋማት ውስጥ ክብካቤ የሚደረግላቸውን ሕፃናት ሁለንተናዊ ዕድገት ለማረጋገጥ የሕፃናቱን መሠረታዊና ሥነ-ልቦናዊ እና ማኅበራዊ ፍላጎቶች (ምግብ፣ መጠለያ፣ ልብስ፣ ትምህርት፣ ንጽህና፣ የጤና አጠባበቅ፣ የጨዋታና የመዝናኛ፣ የማማከር፣ የሥነ-ቦናዊ ፍላጎቶች፣ እንዲሁም ማኅበራዊ መስተጋብር) የማሟላት፤

3) ሕፃናት ተመልሰው በቤተሰብ ውስጥ አብረው እንዲኖሩ ወይም ይህ የማይቻል ወይም የተሻለ አማራጭ ሆኖ ካልተገኘ ዘላቂና ተስማሚ አማራጭ ክብካቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ፣

4) ማንኛውም ተቋማዊ ክብካቤ የሕፃናትን በቤተሰብ ውስጥ የማደግ መብትን የሚያሟላ ቋሚ የክብካቤ አማራጭ ተደርጎ መታየት የለበትም።

## 60. የተቋማዊ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ምዝገባ እና ሪፖርት

1) ማንኛውም የተቋማዊ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የማኅበረሰብ አቀፍ የሕፃናት ክብካቤ አገልግሎቶችን ጨምሮ በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1113/2011 ዓ.ም መሰረት መመዝገባቸውና ፈቃድ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

2) ማንኛውም ድርጅት ከሚመለከተው ፈቃድ ባለስልጣን ተቋም የተቋማዊ ክብካቤ ተቋም ለማቋቋም እውቅና ካልተሰጠው በስተቀር መስራት አይችልም።

3) የሚመለከተው ፈቃድ ሰጪ ባለስልጣን ማመልከቻቸውን እንደተቀበለ፣ የሚከተሉትን ያከናውናል:-

   ሀ) መስፈርቶቹን የማያሟላ ሲሆን ማመልከቻውን በሙሉ ወይም በከፊል ውድቅ ያደርጋል፤ ወይም

   ለ) መስፈርቶቹን ካሟላ የቀረበውን የፕሮግራም መርሀ ግብር በሙሉ ወይም በከፊል ያጸድቃል፤ ወይም

   ሐ) ለተቋሙ የፈቃድ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል።

4) የሚመለከተው ፈቃድ ሰጪ ባለስልጣን የፈቃድ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን የሚሰርዝ ከሆነ፣ የክብካቤ አገልግሎቱን የሚሰጠው ተቋም በክብካቤው ሥር ያሉ ሕፃናትን ወደ ሌላ የክብካቤ ዓይነት ለማዘዋወር ዝግጅቶችን ማድረግና ከተሰጠው ቀነ ገደብ በፊት ስራዎቹን ማጠናቀቅ አለበት።

## 61. መደበኛ ተቋማዊ፣ የተቀናጀ ማኅበረሰብ አቀፍ እና ልዩ ፍላጎት ላላቸው ሕፃናት የክብካቤ ተቋም ምስረታ ማመልከቻ

1) ተቋሚዊ ክብካቤ ማዕከል ለማቋቋም ማመልከቻ የሚያቀርብ ድርጅት፣ አገልግሎቱን ለማቅረብ የሚያስችለው የገንዘብ፣ የቁሳቁስ፣ መነሻ የሰው ኃይልና የሙያ ብቃት ያለው መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ ማቅረብ አለበት። ተቋማዊ ክብካቤ አገልግሎት በመንግሥት፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ወይም በማኅበረሰብ ቡድኖች ሊካሄድ ይችላል። ተቋማዊ ክብካቤ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ዓመታዊ ገቢያቸውን፣ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ምንጮችን በመለየት ምዝገባውን ላካሄደው ባለስልጣን መስሪያ ቤት በግማሽ ዓመትና በዓመታዊ የሥራ ሂደት ሪፖርቶች ማሳወቅ ይኖርባቸዋል።

2) ተቋሚዊ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላወጧቸው አስተዳደራዊ ወጪዎች ሁሉ ተገቢውን ሰነድ መያዝና ወቅታዊ ክትትልና ግምገማ በሚደረግበት ወቅት ለሚመለከተው መዝጋቢ አካል ለቁጥጥር ማቅረብ አለበት።

3) የተቋሚዊ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሥራ አመራሮችና ሠራተኞች ለሕፃኑ ጥቅምና ደህንነት ቅድሚያ ይሰጣሉ፤ የትኛውም የአገልግሎት ሰጪ ተቋም ለግል ጥቅም ሲባል መቋቋም የለበትም።

4) የገንዘብና የቁሳቁስ ድህነት፣ ወይም የትምህርትና የጤና አገልግሎቶች ተደራሽነት እጦትን እና ሌሎች በቀጥታና በተዘዋዋሪ ለተመሳሳይ ድህነት የሚያጋልጡ ሁኔታዎች ሕፃናትን ተቋሚዊ ክብካቤ ውስጥ ለመመደብ ብቸኛ ምክንያት መሆን የለባቸውም። ሆኖም እነዚህ ሁኔታዎች በዚህ መመሪያ ላይ የቤተሰብ ጥበቃና ማጠናከርን በተመለከተ በተገለጸው ሀሳብ መሠረት ለቤተሰቡ ተገቢ ድጋፍ ለመስጠት እንደ አስፈላጊነቱ መነሻ ምክንያት ተደርገው መወሰድ አለባቸው።

5) የተሻለ የትምህርት አቅርቦት ሕፃናትን ከቤተሰባቸው ለመነጠልና በተቋሚዊ ክብካቤ ለመመደብ ምክንያት አይሆንም፡፡

6) ተቋሚዊ ክብካቤ አገልግሎቶ ሰጪ ተቋማት ከታች ከተጠቀሱት አገልግሎቶች በተጨማሪ ከቤተሰብ ጋር መልሶ የማቀላቀል እና የማዋሃድ ወይም በአማራጭ የሕፃናት ክብካቤ ውስጥ በክብካቤያቸው ሥር ላሉ ሕፃናት ቤተሰቦቻቸውን ፈልጎ የማግኘትና እንዲቀላቀሉ የማድረግ ወይም በተቋጥሮ ዝምድና ክብካቤ የሚታቀፉበትን መንገድ የማመቻቸት ሀላፊነት አለባቸው፡፡

7) የሕፃኑ ከወላጁ/ወላጆቹ ጋር ተመልሶ መቀላቀል ወይም በተቋጥሮ ቤተሰብ ክብካቤ ሥር ማድረግ የማይቻል ሲሆን፣ ወይም ለሕፃኑ የተሻለ አማራጭ ሆኖ ካልተገኘ፣ ሌላ የቤተሰብ ክብካቤ አማራጭ ይፈለጋል፡፡ እንደዚህ ዓይነቶቹ አማራጮች የአደራ ቤተሰብን፣ እንዲሁም በራሳቸው ቤተሰቦች ማደግ ለማይችሉ ሕፃናት የሀገር ውስጥ ጉዲፈቻ አገልግሎቶች ማመቻቸትን እንደ ተገቢነቱና አስፈላጊነቱ ያካትታሉ፡፡ ከሦስት ዓመት (3) ዕድሜ በታች የሆኑ ሕፃናት በተቋማዊ ክብካቤ አገልግሎቶች ውስጥ መግባት የለባቸውም፤ ይህም ከዓለም አቀፍ የላቀ ተሞክሮ አኳያ ሲሆን፣ ተቋማዊ እንክብካቤ የግዴታ ከሆነ ያለጥርጥር ጊዜያዊ፣ ወይም ወዲያውኑ የአደራ ቤተሰብ ወይም ማኅበረሰብ አቀፍ ምደባን ለማስከተል ታሳቢ ያደረገ መሆን አለበት፡፡

8) በተቋሚዊ ክብካቤ ያለ ሕፃን የልደት የምስክር ወረቀት የሌለው ከሆነ፣ የተቋሙ ሥራ አስኪያጅ ወይም ምክትል የልደት ሰርተፊኬቱን ለማግኘት ተገቢ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

## 62. የተገቢነት የዳሰሳ ጥናት እና የቅበላ ሂደት

1) የማንኛውም ተቋማዊ አገልግሎት ቅበላ በዚህ መመሪያ ክፍል አሥራ አንድ ስለጉዳይ አያያዝ የተመለከተውን ሂደት ተከትሎ መፈጸም አለበት፡፡

2) የተቋማዊ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ተቋም የሚከተሉትን ማከናወን አለበት፡-

ሀ) ከምደባ በፊት የሕፃኑ አጠቃላይ የጤና ምርመራ በታወቀ የጤና ተቋም የሚደረግበትን ሁኔታ ማመቻቸት፡፡

ለ) ሕፃኑ በሚተላለፍ በሽታ ተጠቅቶ ከሆነ የተገለለ ቦታ በማዘጋጀት ተገቢ የጤና ሕክምና እንክብካቤ አግኝቶ ከበሽታው ሲያገግም ከሌሎች ሕፃናት ጋር እንዲቀላቀል ማድረግ ፡፡

3) የተቋማዊ ክብካቤ አገልግሎት ላይ የሚሳተፉ በጎ ፈቃደኞችና ጎብኚዎች በዚህ መመሪያ ላይ ስለጎብኚዎችና በጎ ፈቃደኞች ለተቀመጡ ሚናዎችና ኃላፊነቶች ተገዢ መሆን አለባቸው፡፡

## 63. የቅበላ ቅጽ

1) በተቋም ክብካቤ እንዲያገኝ ቅበላ የተደረገለት የእያንዳንዱ ሕፃን የቅበላ ቅጽ የሚከተሉትን የሕፃኑን መረጃዎች ማካተት አለበት፡-

ሀ) ስም፣

ለ) ዕድሜና ፆታ፣

ሐ) የቤተሰብ ስም፣

መ) የልደት ቦታና ቀን፣

ሠ) የቀድሞና የአሁን አድራሻ፣

ረ) ሃይማኖት፣

ሰ) የትምህርት ደረጃ፣

ሸ) የጤና ሁኔታ፣ የአመጋገብ ሁኔታ፣

ቀ) የአካል ጉዳት (ካለ)፣ የሥነ-ልቦናዊ ሁኔታ፣

በ) የጥቃት የኋላ ታሪክ (ካለ)፣

ተ) በቅበላ ወቅት የሕፃኑ ሁኔታ (ወላጅ የሞተበት፣ የተተወ፣ ወላጆች ሕመምተኛ ከሆኑ ወይም በአእምሮ ብቁ ካልሆኑ)፣

ቸ) የሕፃኑ የኋላ ታሪክ መረጃ፣

ኘ) ስለ ሕፃኑ ወላጆችና ዘመዶች መረጃ (ካለ)፣

ነ) የሕፃኑ ወላጅ ወይም ሞግዚት ስምምነት (ካለ)፣

ሃ) የሕፃኑ የልደት የምሥክር ወረቀት (ካለ)፣

ኘ) የወላጆች የሞት/የቀብር ሥርዓት የምሥክር ወረቀት (እንደ ተግባራዊነቱ)፣

አ) የወላጆች/የሞግዚት መታወቂያ (እንደ ተግባራዊነቱ)፣

ከ) ተጥለው/ተትተው ለተገኙ ሕፃናት የፖሊስ ማስረጃ እንዲሁም የጉዳይ ቁጥርን (እንደ ተግባራዊነቱ)፣

ኸ) የሕፃኑ ፎቶግራፍ፣

ወ) ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ለሕፃኑ ሌሎች አማራጮች ለምን ተጠቃሚ መሆን እንዳልቻለ ምክንያቶችን የሚገልጽ የድጋፍ ደብዳቤ፡፡

2) ተቋማዊ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ተቋም የእያንዳንዱ ሕፃን የህይወት ታሪክ ቅጽ፣የትምህርት፣ የጤና ሁኔታ፣ የአመጋገብ ሁኔታ፣ የአካል ዕድገት፣ የማኅበራዊ ዕድገትና ስሜታዊ ደህንነት ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ያካተተ የጉዳይ ማኅደር ማደራጀት አለበት።

3) የተቋማዊ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪው ተቋም ውስጥ የተሰጡ ሁሉም አገልግሎቶች የሕፃኑ የግል ማኅደር አካል መደረግ አለባቸው።

4) እያንዳንዱ ሕፃን በቅበላ ወቅት የሚከፈት እንዲሁም በየጊዜው የሚዳብር ማኅደር ሊኖረው ይገባል። እያንዳንዱ ማኅደር ቢያንስ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-

ሀ) የፍርድ ቤት የምደባ ትእዛዝ (እንደ ተግባራዊነቱ) ፤

ለ) የሕፃኑ እና የቤተሰብ ዳሰሳ ጥናት ሪፖርት፣

ሐ) የሕፃኑ መኖሪያ ቤት ልዩ ሥፍራ ወይም ሕፃኑ የተገኘበት ሥፍራ፣

መ) የሕፃኑ የክብካቤ ዕቅድ፣

ሠ) ሁሉም የዳሰሳ ጥናት ሪፖርቶች፣

## 64. ከተቋም ውጪ ያሉ አማራጮች መታየታችውን ማረጋገጥ

1) ማንኛውም ተቋማዊ ክብካቤ ቅበላ ከመከናወኑ በፊት ከዚህ በታች የተቀመጡትን ግልጽ የቅበላ መስፈርት ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለበት።

ሀ) ሁለቱንም ወላጆች በሞት ያጣ፣ የተጣለ፣ ወይም በጎዳና ላይ የሚኖር፣ ወይም ወላጆቹ ወይም የተቋጥሮ ዝምድና ያላቸው ቤተሰቦች ተፈልገው ያልተገኙለት ሕፃን፤

ለ) ከሥጋ ወላጅ ወይም የተቋጥሮ ዝምድና ካላቸው የቤተሰብ አባላት ጋር መኖር የሕፃኑን ጥቅም እና ደህንነት የማይጠብቅ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

ሐ) ሕፃኑ ወላጅ ወይም ወላጆች ያለው ቢሆንም ወላጆቹ ድጋፍ ተደርጎላቸው ሕፃኑ ለማሳደግ ብቁ አለመሆናቸው ሲረጋገጥ፤

መ) ሕፃኑ ልዩ ፍላጎት ኖሮት በቤተሰብ ወይም በማኅበረሰብ ውስጥ ክብካቤ ማግኘት የማይችል ወይም የሕፃኑ ቤተሰብ ድጋፍ ተደርጎለትም ሕፃኑን ለመደገፍና ለመንከባከብ የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ፤

ሠ) ሕፃኑ በጊዜያዊነ ወይም ለረዥም ጊዜ በአደራ ቤተሰብ ወይም በተቋጥሮ ዝምድና ክብካቤ ለመመደብ ያልተቻለ ሆኖ ሲገኝ፤

ረ) ለቤት ውስጥ ጥቃት ወይም ለሌላ አስቸጋሪ ሁኔታ የተዳረጉ ሕፃናት መሆናቸው ሲረጋገጥ።

2) የተቋማዊ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ስለ ሕፃኑ የኋላ ታሪክ ለማወቅ በሚደረገው የቅድመ ቅበላ የዳሰሳ ጥናት ላይ አግባብነት ካለው ቢሮ ባለሙያዎች ወይም ከሕፃናት ጥበቃ ባለሙያ ጋር በመሆን መሳተፍ አለበት።

3) የማኅበረሰብ የተቀናጀ የሕፃናት ክብካቤ አቅራቢ አካላትና የሚመለከታቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶች የዳሰሳ ጥናትና ምደባ አሠራራቸው ጥልቀት ያለው ሊሆን ይገባል፡፡

4) የዳሰሳ ጥናቱና ምደባው የቅበላ መስፈርቱን የሚያሟሉ ሕፃናት ብቻ ቅበላ የሚደረግላቸው መሆኑን ማረጋገጥ አለበት። እንዲሁም ከቅበላው በተጓዳኝ ሕፃናቱን ከቤተሰባቸው ጋር መልሶ ለማቀላቀል ወይንም በሌላ ቤተሰብ ተኮር ቋሚ የክብካቤ አማራጭ እንዲታቀፉ ለማድረግ ጥረት ማድረግ አለባቸው።

5) ሕፃናት ያለአግባብ ወደ ተቋም እንዳይገቡ ለመከላከል ያስችል ዘንድ የሕፃናቱንና የወላጆቻቸውን የኋላ ታሪክ ሙሉ መረጃ ወይም ሕፃኑ ከወላጆች ጋር የማይኖር ከሆነ የሕፃኑ ወቅታዊ የኑሮ ሁኔታዎች ለመረዳት የሕፃኑን የቅበላ ዳሰሳ ጥናት በሚያደርገው አገልግሎት ሰጪ ድርጅት በኩል ተገቢ መረጃዎች መሰብሰብ አለበት። የመረጃ አሰባሰብ ሂደቱ በዚህ መመሪያ የተቀመጡት የጉዳይ አያያዝ አካሄዶች መሠረት ሕጋዊና ሕጋዊ ያልሆኑ ሰነዶችን በሙሉ ማካተት አለበት።

6) የተቋማዊ ክብካቤ ምደባ ሌሎች አማራጮች ከተፈተሹ በኋላ እና የሕፃናቱን ፍላጎት፣ ጥቅምና ደህንነት ታሳቢ አድርጎ ለሕፃኑ ተገቢ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ተግባራዊ ይሆናል።

7) አስፈላጊ እና ተገቢ ሆኖ በሚገኝበት አጋጣሚ ሁሉ የሕፃኑ አስተያየትና ተሳትፎ ግምት ውስጥ መግባት አለበት። የሕፃኑ ሐሳቦች በቅድመ ዳሰሳ ጥናትና በጉዳይ አያያዝ ፋይል ውስጥ መካተት አለባቸው።

## 65. የተቀናጀ ማኅበረሰብ አቀፍ የሕፃናት ክብካቤ አገልግሎት ዝቅተኛ መስፈርቶች

### 1) የመኖሪያ ቤት

ሀ) በአንድ መኖሪያ ቤት የሚመደቡ ህጻናት ከስምንት መብለጥ የለባቸውም፡፡

ለ) ወንድ እና ሴት ሕፃናት በአንድ መኖሪያ ቤት ውስጥ ተቀላቅለው ሊኖሩ ይችላሉ።

ሐ) ከተፈቀደላቸው ሰዎች ውጪ ወደ መኖሪያ ቤቱ እንዳይገቡ አስፈላጊው ጥበቃ ሊደረግለት ይገባል።

መ) የመኖሪያ ቤቱ በሚገባ የተሠራና በቂ እድሳት የሚደረገለት ሊሆን ይገባዋል፡፡

ሠ) የመኖሪያ ቤቱ ለአካል ጉዳተኛና ለሌሎች ልዩ ፍላጎት ላላቸው ሕፃናት ምቹ መሆን አለበት።

ረ) ቋሚ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግባቸው በጾታ የተለዩ የመኝታ ክፍሎች በተቋሙ ውስጥ መኖር አለባቸው።

ሰ) በአንድ ክፍል የሚኖሩ ሕፃናት በተመሳሳይ የዕድሜ ክልል የሚገኙ መሆን አለባቸው።

ሸ) ለእያንዳንዱ ሕፃን አንድ አልጋ ሊሰጠው እና በእያንዳዱ አልጋ መካከልም የአንድ ሜትር ርቀት ሊኖር ይገባል።

ቀ) የመኝታ ክፍሎቹ  የሕፃኑን ደህንነት ግምት ውስጥ ያሰገቡ እንዲሁም በቂ የአየር ዝውውር ያላቸው ሊሆን ይገባል።

በ) የግል ንጽህና መጠበቂያ፣ መታጠቢያና የምግብ አገልግሎት ዝግጅቶች ለሕፃኑ ደህንነት ተስማሚ መሆን አለበት።

ተ) አስተማማኝ የመጫወቻ ቦታዎች እንዲሁም የመቀመጫ፣ የመመገቢያና የመዝናኛ ሥፍራዎች መኖር አለባቸው።

ቸ) ስድስት ዓመት ዕድሜና ከዚያ በላይ የሆነው ሕፃን የራሱ አስተማማኝ መቆያና የግል ሥፍራ ሊኖረው ይገባል። የሚቆለፍና አስተማማኝ ሳጥን ወይም መሳቢያ፣ ወይም ተመሳሳይ የግል ሥፍራ ሊሆን ይችላል። የሕፃኑ ሳጥን ለዋና ተንከባካቢው ለቁጥጥር ተደራሽ መሆን አለበት።

## 2) ተንከባካቢዎች

ሀ) እያንዳንዱ የማኅበረሰብ የተቀናጀ የሕፃናት ክብካቤ የመኖሪያ አገልግሎት የክብካቤ አገልግሎቱን የሚያስተዳድሩ/የሚመሩ አንድ ወይም ሁለት ዘላቂ ተንከባካቢዎች ሊኖረው ይገባል።

ለ) ተንከባካቢዎቹ ጥራት ያለው ክብካቤ ለመስጠት፣ ሕፃናቱን አብረው ሆነው ዕድገታቸውን፣ ከመጀመሪያ ቤተሰባቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነትና በተቋም ውስጥ ሲሰጣቸው የነበረው ክብካቤ ሲያበቃ ተገቢውን ሽኝት ለማድረግና ለመደገፍ፣ እንዲሁም የህጻናቱን ባሕርያትንና ሥነ-ልቦናዊ-ማኅበራዊ ፍላጎቶች ለማወቅ፣ ለመገንዘብና ለማስተዳደር ተገቢው ሙያዊ ክህሎት ያላቸው መሆን አለባቸው።

ሐ) በሕፃኑ እና በተንከባካቢው መካከል የሕፃን እና የተንከባካቢ ግንኙነትን ከግምት ያስገባ የእድሜ ልዩነት ሊኖራቸው ይገባል።

መ) ተንከባካቢዎች ቢያንስ ማንበብ እና መጻፍ የሚችሉ እንዲሁም በቂ የተንከባካቢነት ስልጠና የወሰዱ ሊሆኑ ይገባል።

ሠ) አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ በተንከባካቢዎች ቅጥር ወቅት እንዲሁም በስራው ላይ እያሉ በሕፃናት አያያዝ እና ክብካቤ ዙርያ ወቅታዊ ስልጠና ሊሰጥ ይገባል።

## 3) የድጋፍ ሥርዓት

ሀ) የማኅበረሰብ የተቀናጀ የሕፃናት ክብካቤ አገልግሎቶች የሁሉን አቀፍ የአካባቢያዊ የድጋፍ ሥርዓት አካል ሊሆኑ ይገባል።

ለ) አካባቢያዊ የድጋፍ ሥርዓት ማኅበራዊ ሠራተኞችን፣ አማካሪዎችን/የሥነ-ልቦና ባለሙያዎችን ወይም የጤና ክብካቤ ሠራተኞችን ወይም ሌሎች ልዩ አገልግሎት አቅራቢዎችን ወይም ዘርፈ ብዙ ባለሙያዎችን ወይም ቡድንና ቅንጅቶችን ሊያካትት ይችላል።

ሐ) በተንከባካቢዎች እና በአማራጭ ክብካቤ ሥር ባሉ ሕፃናት መካከል የሚደረግ የእርስ በርስ ግንኙነት የጋራ መደጋገፍ አካል እንደሆነ ሊቆጠር ይችላል።

## 4) ከማኅበረሰቡ ጋር ያለ ትስስር

ሀ) የማኅበረሰብ የተቀናጀ የሕፃናት ክብካቤ አገልግሎት መስጫዎች ሕፃናት የማኅበረሰባቸው አካል እንደ ሆኑ እንዲሰማቸው፣ ሕፃናቱን ከአካባቢው ማኅበረሰብ ጋር ግንኙነት እንዲኖራቸው ለማመቻቸት ተገቢ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው።

ለ) ሕፃኑ እና ቤተሰቡ በአካባቢ የሚገኙትን አገልግሎቶች በመጠቀም በማኅበረሰብ ውስጥ ቅንጅት ፈጥረው እንዲኖሩ መደረግ አለበት።

ሐ) አውዱን ታሳቢ ባደረገ መልኩ የተለያዩ የማኅበረሰብ አቀፍ የተቀናጁ የሕፃናት ክብካቤ አገልግሎት ማዕከሎች የጋራ ተደጋጋፊነትን በሚያረጋግጥና ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ አንዱ ከሌላው በቅርብ ርቀት ሊመሠረቱ ይችላሉ። በሌሎች ሁኔታዎች ደግሞ የማኅበረሰብ የተቀናጁ የሕፃናት ክብካቤ አገልግሎቶች ማኅበረሰቡ ውስጥ ተበታትነው ሊሰጡ ይችላሉ።

## 5) የባለሙያ ወይም ተባባሪ ባለሙያ አቀራረብና የክብካቤ ልዩ ትኩረት

ሀ) የማኅበረሰብ የተቀናጀ ክብካቤ አገልግሎት በባለሙያና በተባባሪ-ባለሙያ ክብካቤ ሰጪዎች በመታገዝ የሕፃናትን ልዩ ፍላጎቶች ለመደገፍ የላቀ ሙያዊ ስልትን መተግበር አለባቸው።

ለ) ተንከባካቢዎች፣ ቅጥር ባለሙያዎች ወይም ተባባሪ-ባለሙያዎች ዋና ትኩረታቸው በሕፃኑ የክብካቤ ፍላጎቶች ላይ ሊሆን ይገባል።

## 6) በማኅበረሰብ የተቀናጀ የሕፃናት ክብካቤ ውስጥ ለሕፃናት ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ መፍጠር

ሀ) በማኅበረሰብ የተቀናጀ የሕፃናት ክብካቤ አገልግሎቶችን በማቅረብ የሚሳተፉ ድርጅቶችና ግለሰቦች ህጻናትን ለመንከባከብ ከተሰጣቸው መብት ጋር ተያይዞ የሕፃናት ደህንነት ጥበቃ እርምጃዎችን በብሔራዊ የሕፃናት ጥበቃ ፖሊሲዎች፣ ኢትዮጵያ ተቀብላ ባጸደቀቻቸው ስምምነቶችና በመልካም ተሞክሮ ላይ በመመስረት ተግባራዊ ማድረግና ለሕፃናት አስተማማኝ አካባቢ የመፍጠር  ግዴታ አለባቸው።

ለ) ማንኛውም ተቋማዊ የክብካቤ ማዕከል የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ለሆኑ ሕፃናት የሕግ ጥበቃ መስጠት አለበት።

ሐ) የሕፃናት ጥበቃ እርምጃዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

1) ክንውኖች ወይም ኩነቶች ከማኅበረሰብ የተቀናጀ ክብካቤ አገልግሎት በሚሰጥበት አካባቢ ወይም ህጻናቱ ባለመዷቸው አካባቢዎች የሚደረጉ ከሆነ፣ የሕፃናቱን ደህንነት ለመጠበቅ ልዩ ጥንቃቄ መደረጉ በቅድሚያ መረጋገጥ አለበት፡፡

2) ሕፃናቱን የተመለከቱ መረጃዎች፣ ግለ-ታሪኮችንና ምስሎች ወይም ተንቀሳቃሽ ምስሎችን የህጻናቱን ጥቅም በሚጎዳ መልኩ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡

3) ከማኅበረሰብ የተቀናጀ የህጻናት ክብካቤ ውጭ የሚገኙ ህጻናት ላይ  ጥቃት መፈጸሙ ጥርጣሬ ሲኖር ወይም በተጨባጭ በህጻናት ላይ ጥቃት መፈፀሙ የሚያውቅ ማንኛውም ሰው ጥቆማ ማድረግ አለበት፡፡

4) ተንከባካቢዎች አዎንታዊ የጸባይ ማረሚያ ዘዴዎችን መጠቀም አለባቸው፡፡

5) ተንከባካቢዎች አስቸጋሪ ጉዳዮች ሲያጋጥማቸው የምክርና የድጋፍ አገልግሎት ተደራሽነት ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

6) አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለሕፃናቱ ተጨማሪ ድጋፍ ለመስጠት ከሕፃናቱ ጋር ግንኙነት እንዲኖረው የተለየ አጋር ድርጅት ወይም  አገልግሎት አቅራቢ ተገቢው ማጣራት በማድረግ መምረጥ አለባቸው፡፡

7) በማንኛውም ጊዜ ለሕፃኑ ክብካቤ የመስጠት ኀላፊነት ያለበት ማን እንደ ሆነ መታወቅ አለበት፡፡

8) ሕፃናቱ ደህንነት እንዲሰማቸውና እንዳይሰማቸው የሚያደርጋቸው ምክንያት ምን እንደ ሆነ ከሕፃናቱ ጋር መወያየትና ስለ ራሳቸው ወይም ስለ ጓደኞቻቸው የሚያሳስብ ነገር ካላቸው ሕፃናት ቅሬታ ስለሚያቀርቡባቸው መንገዶች በቅድሚያ ከህጻናቱ ጋር ስምምነት ላይ መደረስ አስፈላጊ ነው፡፡

9) ጉልበተኛነትን የማያበረታቱ መርሆዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ፤

10) የወንዶች ልጆችና ልጃገረዶች የተለያዩ ፍላጎቶች ግምት ውስጥ መግባታቸውንና የሕፃናትና ታዳጊ ወጣቶች የተለያዩ ፍላጎቶች ታሳቢ መደረጋቸውን ማረጋገጥ፤

መ) የማኅበረሰብ የተቀናጀ የሕፃናት ክብካቤ አገልግሎት አቅራቢዎች ከእያንዳንዱ ተንከባካቢ፣ አጋር ወይም ማኅበረሰብ ወይም በተቋሙ ውስጥ ከሰው ሐብት፣ የህዝብ ግንኙነት ወይም ድጋፍ ማሰባሰብን በመሳሰሉ የሥራ ክፍሎች ጋር የተያያዙ የሕፃናት ደህንነት ሥጋቶችን ለመመርመር፣ ለመተንተንና ለመቀነስ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው።

## 7) ድጋፍ የሚደረግላቸው ተንከባካቢዎች

ሀ) የማኅበረሰብ የተቀናጀ የሕፃናት ክብካቤ አገልግሎቶችን የሚሰጡ ድርጅቶች ተንከባካቢዎችን በስራ ላይ ከመሰማራታቸው በፊት ተገቢውን ሥልጠና እንዲወስዱ ማድረግ አለባቸው። ይህም ጥንቃቄ በተሞላ ተንከባካቢዎችን የመምረጥ ሂደትን በመከተል፣ በሥልጠና፣ እንዲሁም ዋና ተንከባካቢዎች ከመሆናቸው በፊት ረዳት ተንከባካቢ ሆነው የሚገመገሙበትን መንገድ በማመቻቸት ይካሄዳል።

ለ) ግለሰቦች የማኅበረሰብ የተቀናጀ የሕፃናት ክብካቤ አገልግሎቶችን ለማካሄድ ሲፈልጉ፣ አግባብ ባለው የመንግሥት ተቋም ተመዝግበው ለዚህ ሚና መሰልጠን አለባቸው።

## 8) ከቤተሰብ ጋር ማዋሃድን፣ በሌሎች አማራጭ የሕፃናት ክብካቤ ውስጥ መመደብን፣ ትምህርትን፣ ተሳትፎን እና ራስ መቻልን ለማበረታታት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች

ሀ) በቤተሰብ መልሶ ማቀላቀልና ማዋሃድ ወይም በሌላ የአማራጭ ክብካቤ ዓይነት መመደብ የማይቻል ሲሆን፣ የማኅረሰብ የተቀናጀ የሕፃናት ክብካቤ አገልግሎቶችን የሚያንቀሳቅሱ ድርጅቶችና አጋሮች እያንዳንዱ ዕድሜው የደረሰ ሕፃን ወይም ታዳጊ ራስን ወደ መቻል የሚያመሩ እርምጃዎችን እንዲወስድ የሚያስችሉ እድሎችን እንዲጠቀሙ መደገፍ አለባቸው።

ለ) ተቋማት ታዳጊ ወጣቶች ዕድሜያቸውንና የዕድገት ደረጃቸውን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ዘርፈ ብዙ ክህሎቶች እንዲያገኙ በማድረግ በኅብረተሰብ ውስጥ ኃላፊነትን ለተላበሰ አኗኗር እንዲዘጋጁ፤ ስራ የማግኘት ዕድላቸውን ለማስፋት የሙያ ስልጠናን እንዲያገኙ ማመቻቸትን ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ድጋፎችን ማድረግ አለባቸው።

# 66. ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሕፃናት ልዩ ተቋማዊ ክብካቤ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ዝቅተኛ መስፈርቶች

1) በብሔራዊ የሕፃናት ፖሊሲ መሰረት ተቋማዊ ክብካቤን የሚሰጡ አገልግሎቶች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ሕፃናት ክብካቤን አካታች መሆን እንዳለባቸው የሚያስቀምጠውን መርህ መከተል አለባቸው፡፡

2) የልዩ ተቋማዊ ክብካቤ አገልግሎት ተጠቃሚ የሚሆኑ ሕፃናት የከፋ የአካል፣ የአዕምሮ ወይም የስሜት ህዋሳት ጉዳት ወይም እክል ያሏቸው ሕፃናት ሲሆኑበሕብረተሰቡ ውስጥ በዕኩልነት ተሳትፎ ማድረግ ያልቻሉና ድጋፍ እየተሰጣቸውም ቢሆን ከቤተሰባቸው ጋር መኖር የማይችሉ ሕፃናት ናቸው።

3) ማንኛውም ሰው የአካል ጉዳተኛ ሕፃንን ክብር በሚነካ ሁኔታ ማስተናገድ የለበትም እንዲሁም አንድ የአካል ጉዳተኛ ሕፃን እምቅ አቅሙን እስካለው ችሎታ እስኪያሳድግና በራስ መተማመን እስኪችል ድረስ የልዩ ክብካቤ፣ ትምህርትና ሥልጠና የማግኘት መብት አለው።

4) ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሕፃናት በፈጠራና በአዝናኝ ክንውኖች የመሳተፍ መብታቸውን መነፈግ የለባቸውም እንዲሁምአገልግሎቱን የሚሰጡ ተቋማት ከባድ የአካል ጉዳት ላሉባቸው ሕፃናት ምቹ የሆነ የጨዋታ እና የመዝናኛ ቦታ ማዘጋጀት አለባቸው።

5) ተንከባካቢዎች በሕፃኑ ልዩ ፍላጎቶች መሠረት ለሕፃናት ፍቅርን፣ ተቀባይነትን፣ ምክርን፣ ጥበቃንና ደህንነትን በማሳየት ለሕፃናቱ ጤናማ የክብካቤ ሁኔታን መፍጠር አለባቸው፡፡

6) ተንከባካቢዎች ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሕፃናት አገልግሎቶችን ለመስጠት በችሎታቸው እና አገልግሎቱን በመስጠት ባላቸው ልምድ መመረጥ አለባቸው።

7) ከባድ የአካል ጉዳት ላሉባቸው ሕፃናት የሚቋቋሙ ተቋማት ሕፃናቱ ተንቀሳቅሰው የመጫወት ዕድሎችን፣ በተለይም የመስክ ጨዋታዎችን የአካላዊ፣ የማኅበራዊ፣ የቋንቋና የመገንዘብ ክህሎታቸውን እንዲያሳደጉ ታሳቢ ያደረገ አካባቢን ያመቻቻሉ።

8) ተጨማሪ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው የአካል ጉዳተኛ ሕፃናት ፣ አገልግሎቱን የሚሰጡ ተቋማት የጭንቅላት መከላከያ ባርኔጣ፣ የአካል ጉዳተኞች ጋሪ፣ የወለል ምንጣፎች፣ ማንገቻዎች፣ የሆስፒታል አልጋዎች፣ መስተካከያ ድጋፍ፣ ሰው ሰራሽ አካላትና የመታጠቢያ ወንበሮች፣ እንዲሁም የብሬይል ሥልጠናና የምልክት ቋንቋ የመሳሰሉ ልዩ አገልግሎቶችና የሕፃኑን ልዩ ፍላጎቶች ለማሟላት የሚያስፈልጉ አጋዥ መሳሪያዎችን ማሟላት አለባቸው፡፡

9) በልዩ የክብካቤ ማዕከሉ የሕፃኑ ደህንነት የሚመለከቱ አሳሳቢ ሁኔታዎች ካሉ ተንከባካቢው ከሕፃኑ ሐኪም፣ የሥነ-አመጋገብ ወይም የፊዚዮቴራፒ ባለሙያ ጋር በመመካከር ለሕፃኑ የሚያስፈልገውን ክብካቤ ጥራት በሚመለከት ተገቢውን ውሳኔ መስጠት አለባቸው። ።

10) በልዩ የክብካቤ ማዕከሉ ለአካል ጉዳተኛ ሕፃናት አገልግሎት ሲሰጥ አገልግሎቱ ለሕፃናቱ ሙሉ በሙሉ ተደራሽ፣ ከፍላጎቶቻቸውና ከደህንነታቸው ጋር የተጣጣመ መሆኑ መረጋገጥ አለበት።

11) ልዩ ማዕከሉ ለሕፃናቱ የመኝታ፣ የመማሪያና የመዝናኛ ፍላጎቶቻቸውን የሚያሟላ በቂ ቦታ ሊኖረው ይገባል።

12) ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሕፃናት ምደባ ተገቢና ጥራት ያለው ክብካቤ እንዲሰጣቸውደህንነታቸውንና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መሟላቱን ማረጋገጥ አለባቸው።

13) ለሕፃናቱ የሚሰጠው አገልግሎት ትኩረት የሕፃናቱን ጊዜያዊ ፍላጎቶች ማሳካት፣ ክህሎታቸውን ማሳደግ እና ሁለንተናዊ ዕድገታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል መሆን አለበት።

14) ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሕፃናት የሚቻል በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ ክብካቤያቸውን እና ምርጫዎቻቸውን በሚመለከት የውሳኔ አሰጣጥ ላይ መሳተፍ አለባቸው።

15) ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሕፃናት ለፍላጎቶቻቸው ተስማሚ የሆነ ትምህርት የማግኘት መብት አላቸው።

16) የልዩ ፍላጎት ማዕከላት የአካል ጉዳተኛ ሕፃናትን በቤተሰቦቻቸውና በማህበረቡ ውስጥ የሚኖራቸው ተሳትፎ እና ማኅበራዊ መስተጋብር አካታች መሆኑን ማረጋገጥ እና የማኅበራዊ ዕድሎች ተደራሽ መሆን እንዲችሉ መደገፍ አለባቸው እንዲሁምልዩ ፍላጎት ያላቸውን ሕፃናት ከማህበረሰቡ ጋር ተዋህደው የመኖር አስፈላጊነት እንዲረዱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች መሰራት አለባቸው።

17) ልዩ ማዕከላት በክብካቤያቸው ሥር ለሚገኙ ሕፃናት የሕግ ጥበቃ የመስጠት ሃላፊነት አለባቸው።

18) ልዩ ማዕከላት የአካል ጉዳትን ከሕክምና ፅንሰ ሐሳብ አኳያ ብቻ ከመረዳት አካሄድ የማኅበራዊ አውድንና የአካታችነትን አስፈላጊነት ዕውቅና መስጠት አለባቸው።

19) ተንከባካቢዎችና የልዩ ፍላጎት አገልግሎቶችን ሰጪ ተቋማት፣ የአካል ጉዳተኛ ሕፃናትን በቤተሰቦቻቸው እና በማህበረሰባቸው ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ማካተት እና መሳተፍን እንዲሁም ለሕፃናቱ በቤተሰቦቻቸውና በማኅበረሰቡ ውስጥ ክብካቤ እያገኙ ከማህበረሰቡ ጋር እንዲዋሃዱ መደገፍና መታገዝ አለባቸው።

20) እያንዳንዱ ለሕፃናት የልዩ ፍላጎት አገልግሎቶች የሚሰጥ ማዕከል የራሱንየሕፃናት ጥበቃ ፖሊሲን ሥራ ላይ ማዋል አለበት።

21) እያንዳንዱ ድርጅት የሕፃናት ጥበቃ ኀላፊ ወይም ተተኪውን መመደብ አለበት።

22) የሕፃናት ጥበቃ እርምጃዎች የሚከተሉትን አሰራሮች ተከትለው መፈጸም አለባቸው :-

ሀ) የአካል ጉዳተኛ ሕፃናትንጥቃት ሊፈጸምባቸው መሆኑን የሚያሳዩ ምልክቶችን እንዲገነዘቡ የሠራተኞችንና የሕፃናትን አቅም መገንባት፤

ለ) የአካል ጉዳትኛ ያለባቸው ህጻናት ፍላጎትን የሚያካትት የሕፃናት ጥበቃ መመሪያ ማዘጋጀት፤

ሐ) ክንውኖች ወይም ኩነቶች ባልተለመዱ ቦታዎችና ከማኅበረሰብ የተቀናጀ ክብካቤ ማዕከላት ውጭ የሚካሄዱ ከሆነ፣ ሕፃናቱን ለመጠበቅና ከጉዳት ለመከላከል ተገቢ ዝግጅቶች መደረጋቸውን ማረጋገጥ፤

መ) የሕፃናትን መረጃ፣ ግለ-ታሪኮች፣ ፎቶግራፎች፣ ቪዲዮ ወይም በማህበራዊ ትስስር ድህረ ገጾች ላይ ተገቢ ካልሆነ አጠቃቀም መጠበቅ፤

ሠ) በማዕከሉ ውስጥም ሆነ ከማእከሉ ውጭ በሕፃናት ላይ ጥቃት ሊፈጸም ይችላሉ ተብለው የሚጠረጠሩ ወይም በተጨባጭ ስጋት ያለባቸውን አካባቢዎች በመለየት ዘገባዎችን ማጠናቀርና ተንከባካቢዎችንና ሕፃናቱን ማስገንዘብ፤

ረ) የጥቃት ወይም የብዝበዛ አሳሳቢ ሁኔታዎች ወይም ክስተቶች ሲኖሩ፣ለተንከባካቢዎችና ለሠራተኞች የምክር ድጋፍ አገልግሎትን ተደራሽ ማድረግ፣

ሰ) ከሕፃናት ጋር የቅርብ ግንኙነት ወይም ተጽዕኖ የሚኖረው አጋር ድርጅት ወይም የተለየ አገልግሎት አቅራቢ ጥልቅና ሙሉ በሆነ የዳሰሳ ጥናት ውስጥ ማለፉን ማረጋገጥ፤

ሸ) በማንኛውም ጊዜ ለሕፃኑ ክብካቤ ኀላፊነት ያለበት ሰው ማንነትን ማሳወቅ፤

ቀ) ከሕፃናቱ ጋር በመወያየት የደህንነት ስሜት እንዳይሰማቸው የሚያደርጋቸውን ነገር መለየትና ስለራሳቸው ወይም ስለ ጓደኞቻቸው የሚያሳስባቸው ጉዳይ ካለም አማራጭ የተግባቦት ዘዴዎችን ጨምሮ፣ ቅሬታ በሚያቀርቡባቸው መንገዶች ላይ መስማማት፤

በ) ማንኛውም ጥቆማ የቀረበለት የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያ አለ የተባለውን ሥጋት በጥንቃቄ ይመረምራል፤ የምርመራ ውጤቶቹ ላይ በመመሥረትም ተጨባጭ ውሳኔዎች ይሰጣል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣

ተ) ለሠራተኞችና ለሕፃናት የተለያየ የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት መኖሩን ማረጋገጥ፤

ቸ) የጸረ ጉልበተኝነት መርሆዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ማረገገጥ፤

ኀ) የልጃገረዶች፣ የወንድ ህጻናትና የታዳጊ ወጣቶችን የተለያዩ ፍላጎቶች ግንዛቤ ውስጥ መግባታቸውን ማረጋገጥ፤

23) ልዩ ፍላጎት ላላቸው ሕፃናት ልዩ ተቋማዊ ክብካቤ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ከእያንዳንዱ ተንከባካቢ፣ አጋርና ማኅበረሰብ፣ እንዲሁም በተቋሙ ውስጥ እንደ ሰው ሐብት፣ የውጭ ግንኙነት ወይም ድጋፍ ማሰባሰብን በመሳሰሉ የሥራ ክፍሎች ጋር የተያያዙ የሕፃናት ደህንነት ሥጋቶችን ለመመርመር፣ ለመተንተንና ለመቀነስ የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው።

## 67. መደበኛ ተቋማዊ የሕፃናት ክብካቤ

1) ወደ መደበኛ ተቋማዊ የሕፃናት ክብካቤ የሚገቡ ሕፃናትልየታ እና ቅበላ ሂደት በብሔራዊ የሕፃናት ጥበቃ የጉዳይ አያያዝ ማዕቀፍ ላይ የተቀመጡ መስፈርቶችን፣ በሚኒስቴሩ የተዘጋጁ የአሰራር ሂደቶች (ኤስ.ኦ.ፒ) እንዲሁም በዚህ መመሪያ በተደነገጉ የጉዳይ አያያዝ የአሰራር ስነ-ስርዓቶችን መከተል አለበት።

2) በሕፃናት ልየታ ወቅት የአገልግሎት ሰጪ ተቋም የእያንዳንዱን ሕፃን የተጋላጭነት ደረጃ ለመለየት ከዚህ በታች የተመለከቱትን ጉዳዮች ታሳቢ ማድረግ አለባቸው፡፡

ሀ) ከወላጅ ክብካቤ ውጭ የሆኑ እና አንድ ወይም ሁለት ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናት፤

ለ) መኖርያ ቤት የሌላቸው እና ከቤተሰቦቻቸው የተለዩ ሕፃናት፤

ሐ) ተጥለዉ የተገኙ እና ወላጆቻቸው ወይም ቤተሰቦቻቸው በፍለጋ ያልተገኙ ሕፃናት፤

መ) አካል ጉዳተኛ ሕፃናት፤

ሠ) ለተለያዩ አስከፊ የጉልበት ብዝበዛ ጥቃቶች የተጋለጡ ሕፃናት፤

ረ) ለፆታዊ ጥቃት እና ብዝበዛ የተዳረጉ ሕፃናት፤

ሰ) በሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ተጎጂ የሆኑ ሕፃናት፤

ሸ) የኤች. አይ. ቪ. ኤድስ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ የሚገኝ ህጻናት ፤

ቀ) የተፈናቀሉ ሕፃናት፤

በ) ወላጆቻቸው በህይወት እያሉ በሕመም፣ በጉዳት፣ ወይም በእሥር ምክንያት አስፈጊውን ክብካቤ ሊሰጧቸው ያልቻሉ ሕፃናት፤

ተ) ቤተሰብ የሚያስተዳድሩ ሕፃናት፤

ቸ) ከፍተኛ የባሕርይ ችግሮች ያሉባቸው ሕፃናት፤

ኀ) ከወላጆቻቸው ወይም ከቤተሰቦቻቸው ጋር የተለያዩ ሕፃናት፤

ነ) ስደተኛ ሕፃናት፣ እና

ኘ) እንደየአካባቢው የሥጋት ወይም ተጋላጭነት ትርጓሜ መሠረት ሌሎች ሕፃናትን ያካትታል።

3) ተቋሙ የሚገኝበት ስፍራ የሚከተሉትን መሠረተ ልማቶች ማሟላት እና ተደራሽነት ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፦

ሀ) የመጠጥ ውሃ አቅርቦት፣

ለ) መንገዶች (በበጋ ወይም በሁሉም ወቅቶች የሚያገለግሉ መንገዶች)፣

ሐ) የኤሌክትሪክ ኃይል ወይም ማመንጫ (ጄኔሬተር)፣

መ) የስልክ አገልግሎት፣

ሠ) በአካባቢው የትምህርት ተቋም መኖሩን፣

ረ) ቦታው አደገኛ ከሆኑ ወይም ለተደጋጋሚ አደጋዎች ሊያጋልጡ ከሚችሉ የወታደራዊ ካምፖች፣ ለጦርነት የተጋለጡ አካባቢዎች፣ አደገኛ የዱር እንስሳት ያሉባቸው ቦታዎች፣ ለጎርፍ የተጋለጡ አካባቢዎች፣ የተበከሉ እና ከፍተኛ የትራፊክ መጨናነቅ ካለባቸው ስፍራዎች የጸዳ መሆኑን፣

ሰ) በተቋሙ ባለው የቅበላ ቅጽ ላይ ከላይ የተጠቀሱትን መረጃዎች የተካተቱ መሆኑን፣

ሸ) አግባብ ካለው የመንግሥት ቢሮ ጋር ስምምነት የተደረገባቸው ምክንያቶች ከሌሉ በስተቀር በተቋሙ ክብካቤ ውስጥ የሚኖሩ የሕፃናት ፆታ እና ዕድሜ የተሰባጠረ መሆን አለበት።

## 68. መደበኛ ተቋማዊ የሕፃናት ክብካቤ አገልግሎት ዝቅተኛ መስፈርቶች

**1) መደበኛ ተቋማዊ የሕፃናት ክብካቤ ተቋማት መገኛ ቦታ፣ አጥር ግቢ እና ሠራተኞች**

ሀ) የተቋሙ ዋና ዋና የማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ስሜታዊ፣ የትምህርት እና የጤና ፍላጎቶች በሚኖሩበት ጊዜ ሁሉ ሊስተናገዱ በሚችሉበት አማካይ ሥፍራ ላይ መገኘት አለበት።

ለ) በተቋሙ ውስጥ ያሉ ማረፊያዎች በሚገባ የሚናፈሱ እና በቂ ብርሃን ያላቸው እንዲሁም በንጽህና የተያዙ መጸዳጃ ቤቶች፣ የመታጠቢያ ክፍሎች እና መታጠቢያ ገንዳዎች በቀላሉ ተደራሽ መሆን አለባቸው።

ሐ) መደበኛ ተቋማዊ የሕፃናት ክብካቤ አገልግሎት የሚሰጥ ሕንፃ ቢያንስ የሚከተሉት አገልግሎት መስጫ ክፍሎች ሊኖሩት ይገባል፣

1) ማረፊያ (የጋራ መኝታ ክፍል ወይም እራሳቸውን የቻሉ ቤቶች) ፤

2) የማማከር አገልግሎት የሚሰጥበት ክፍል፤

3) ቢያንስ አንድ የስብሰባ ወይም የምግብ አዳራሽ፤

4) አንድ የመጀመሪያ እርዳታ የሚሰጥበት ክፍል፤

5) የመዝናኛ መገልገያዎች (የቤት ውስጥ እና ከቤት ውጭ መገልገያዎች) ፤

6) የተቋሙ አንድ የአስተዳዳሪው ቢሮ፤አንድ መዝገብ ቤት እና የገንዘብ ቤት፤

7) የዕቃ ግምጃ ቤት፤

መ) ተቋሙ ውስጥ ያሉ የአገልግሎት እና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ቁጥር በተቋማዊ ክብካቤ ካሉት ሕፃናት ቁጥር ጋር የተመጣጠነ መሆን አለበት፡፡ በዚሁ መሰረት አንድ ክብካቤ ሰጪ ከስድስት (6) ሕፃናት በላይ መንከባከብ የለበትም።

ሠ) ሠራተኞች አቅማቸውን ለማሳደግ እንዲሁም ውጤታማ እና ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ በየጊዜው የሥራ ላይ ሥልጠና ሊሰጣቸው ይገባል።

ረ) መደበኛ ተቋማዊ የሕፃናት ክብካቤ ተቋማት የሚከተሉት ሠራተኞች ሊኖራቸው ይገባል፡-

1) ሥራ አስኪያጅ ወይም አስተዳዳሪ፤

2) የፋይናንስ ባለሙያ፤

3) የጥበቃ ሠራተኞች፤

4) የጤና ረዳት፤

5) የምክክር ባለሙያ፤

6) ተንከባካቢዎች፤ እና

7) የጽዳት ሰራተኛ፡፡

ሰ) ሠራተኞች ተቋሙ ውስጥ ሲቀጠሩ፣ በአዕምሮ ጤናማ እና ከወንጀል ነጻ ስለመሆናቸውና ቀደም ሲል ሕፃናት ላይ ጥቃት ስላለመፈጸማቸው ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው።

ሸ) ማንኛውም መደበኛ ተቋማዊ የሕፃናት ክብካቤ ተቋማት ከሠራተኞች የሚጠበቀውን ባሕርይ የሚገልጽ የሠራተኞች የሥነ-ምግባር ደንብ ሊኖረውና ለሰራተኞቹ ቅጂውን መስጠት ይኖርበታል።

ቀ) ማንኛውም ሠራተኛ በቅጥር ወቅት የሥነ-ምግባር ደንብን ማንበብና መረዳት እንዲሁም ደንቡ በሁለት ቅጂዎች ተዘጋጅቶ ሠራተኛው ከፈረመበት በኋላ አንዱ ቅጂ በሠራተኛው የግል ማኅደር ውስጥ ተያይዞ መቀመጥ አለበት፡፡

በ) ተቋሙ የሥራ ቦታ የአደንዛዥ ዕጽ እና የአልኮል መጠጥ የሚከለክል ፖሊሲ ሊኖረው ይገባል።

ተ) ተቋሙ ተቀባይነት ያለው የአለባበስ መመሪያ የማዘጋጀት፣ በሕፃናት መካከል ወይም በሠራተኞችና በህጻናት መካከል ወይም ሕጋዊ ጋብቻ ካልመሰረቱ በስተቀር በሠራተኞች መካከል የፍቅር ግንኙነት እንዳይኖር የሚከለክል መመሪያ ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

ቸ) ሁሉም ሕፃናት ግላዊነት መብት አላቸው፤ የሕፃኑ መረጃ የያዘ ማንኛውም በጽሑፍ የሰፈረ ሰነድ ወይም ማኅደር ለሁሉም ሰው እይታ ተጋልጦ መቀመጥ የለበትም። እያንዳንዱ የክብካቤ ተቋም የሕፃናት የግል ጉዳይ ማኅደሮች እና የክብካቤ ዕቅድ ሚስጥራዊነታቸው መጠበቅ አለበት፡፡ የሕፃናቱ ማኅደሮች መዳረሻ ውስን መሆን እና መረጃ የማወቅ አስፈላጊነት ላይ መመሥረት አለበት።

ኀ) መደበኛ ተቋማዊ የሕፃናት ክብካቤ ተቋማት በኢትዮጵያ የሠራተኛ ሕጎች መሠረት የሠራተኞች ፈረቃን እና የሥራ ሰዓትን መወሰን እና ለሁሉም ሠራተኞች ግልጽ የዕረፍት ቀናት እንዲኖራቸው መፍቀድ አለባቸው። ቀጣሪው የሠራተኞችን የአስተዋጽኦ ክፍያን እና ሌሎች በሕግ የተቀመጡ መስፈርቶችን መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት።

ነ) ተንከባካቢዎች በምሥጢራዊነት እና በጥንቃቄ መያዝ የሚገባቸው መረጃዎች ዙርያ ሊሰለጥኑ ይገባል። በሕፃኑ ወይም በሌሎች ሰዎች ፊት ስለ ሕፃኑ ሚስጥራዊነት ያላቸውን ጉዳዮች በይፋ ውይይት መደረግ የለበትም።

ኘ) የሕፃናት ማቆያ ተቋማት ለሕፃኑ ጥቅም እና ለሕፃናቱ ደህንነት፣ ለመልቀቅያ እና ለሌሎች ተዛማጅ አወንታዊ ዓላማዎች አስፈላጊ ሆነ ከተገኘ መረጃውን ለሚመለከተው ሰው ማጋራት አለባቸው፡፡

አ) ሕፃናት ተቋሙ ውስጥ እያሉ ወይም ከተቋሙ ከወጡ በኋላ እንደ ዕድሜያቸው እና እንደ አዕምሮ ብስለታቸው የግል ማኅደሮቻቸውን የማየትና ቅጂው የማግኘት መብት አላቸው።

ከ) የሕፃናት ማኅደሮች በተቋሙ ውስጥ ቢያንስ ለ7 ዓመት መቀመጥ አለበት። በቀጣይ በማህደርን በቋሚነት ለማስቀመጥ ሃላፊነት ለተሠው አግባብነት ላለው ቢሮ ወይም ለሚኒስቴሩ መላክ አለባቸው። የሰባት አመት ጊዜው ከማብቃቱ በፊት ተቋሙ ከተዘጋ፤ ማህደሮቹን ደህንነት ለመጠበቅ ወደ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ላለው ቢሮ ማስተላለፍ አለባቸው።

ኸ) እያንዳንዱ መደበኛ ተቋማዊ የሕፃናት ክብካቤ ተቋም ከተቋሙ ውጭ ላለ ባለሥልጣን ቅሬታዎችን ማቅረብ የሚችል የቅሬታ ሂደትን ጨምሮ ምሥጢራዊነቱን የጠበቀ የቅሬታ ማቅረቢያ ሥርዓት ሊኖረው ይገባል።

ወ) የቅሬታ ማቅረቢያ ሂደቱ ቅጂ በማቆያ ተቋሙ ውስጥ ለተገልጋዩ ግልጽ በሆነ ቦታ እንዲቀመጥ ማድረግ እና ሕፃኑ ከማብራሪያው ለመጠቀም በሚያስችል ዕድሜ እና የግንዛቤ ደረጃ ላይ ከሆነ በማቆያ ተቋሙ ቅበላ ወቅት ለእያንዳንዱ ሕፃን መብራራት አለበት።

## 2) መጠለያ እና አልባሳት

### ሀ) መጠለያ

1) መደበኛ ተቋማዊ የሕፃናት ክብካቤ ተቋሙ ለሕፃናት በቂ ሥፍራ ሊኖረው እና አካባቢውም ሕፃናት ሊኖራቸው የሚችለውን ማንኛውንም ልዩ ፍላጎት ከግምት ያስገባ መሆን አለበት።

2) ተቋሙ የአስተዳደር የተለዩ ቢሮዎች፣ የምግብ፣ የቴሌቪዥን ወይም የመዝናኛ ክፍሎች፣ መጋዘን፣ የማብሰያ ማእድ ቤት፣ መጸዳጃ ቤቶች፣ የልብስ ንፅህና መጠበቂያ ክፍል፣ በቂ ሥፋት ያላቸው በሚገባ የሚናፈሱ መኝታ ክፍሎች፣ ከቤት ውጭ ያሉ የሕፃናት የመጫወቻ ስፍራዎች እና ለቤት ውስጥ ጨዋታዎች የሚሆን ክፍል ሊኖረው ይገባል።

3) የመኝታ ክፍሉ በጾታ መከፋፈል እንዲሁም ከተቻለ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚተኙ ሕፃናት በተመሳሳይ የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሕፃናት መሆን አለባቸው።

4) ለእያንዳንዱ ሕፃን አንድ አልጋ ሊሰጠው እንዲሁም ከተቻለ በእያንዳዱ አልጋ መካከልም የአንድ ሜትር ርቀት ሊኖር ይገባል።

5) አንድ የመኝታ ክፍል ከስድስት ሕፃናት በላይ መያዝ የለበትም።

6) እያንዳንዱ የመኝታ ክፍል ሕፃናቱ የግል ዕቃዎቻቸውን የሚያስቀምጡበት አንድ የቁም ሳጥን ወይም ደህንነቱ የተጠበቀ ሳጥን ፣ መሳቢያ ወይም ተመሳሳይ የግል ስፍራ ሊኖረው ይገባል።

7) ዕድሜያቸው ከሰባት ዓመት በታች ለሆኑ ሕፃናት መወጣጫ ባላቸው ተደራራቢ አልጋዎች ላይ እንዲተኙ መደረግ የለበትም፡፡

8) የመኝታ ክፍሎቹ በሚገባ የሚናፈሱ፣ የመታጠቢያ ክፍል እና ለልብስ ማጠቢያ የሚሆን የተለየ ቦታ ሊኖራቸው ይገባል። የመኝታ ክፍሉ ሕፃናቱ ነጻነት እንዲሰማቸው የሚያደርግ እና በምሽት ጊዜ ለሚከናወን ክትትሎች በቂ ቦታ ሊኖረው ይገባል።

9) የሕፃናት ማቆያ ተቋሙ ቢያንስ የሚከተሉትን የጽዳት ቁሳቁሶችን የንጽህና መጠበቂያ ፎጣዎችን ጨምሮ የልጃገረዶች የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ፣ ለተጠቃሚ ሕፃናት ያቀርባል፣ ይህም የግል ንጽህና መጠበቂያ፣ የልብስ የማጠቢያዎች፣ የአካባቢያቸውን እና የሕንፃውን ንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች፣ በተጨማሪም ለቆሻሻ ማስወገጃ የሚሆኑ መገልገያዎችን አሟልቶ መያዝ አለበት።

### ለ) አልባሳት

1) አልባሳት በሚኒስቴሩ የተቋማዊ ክብካቤ የአገልግሎት አሰጣጥ መስፈርት መሠረት መፈጸም አለበት።

## 3) የምግብ አቅርቦት

ሀ) የሕፃናቱን የግል እና የተመዘገበ የዘወትር የምግብ ፍላጎቶች እና ምርጫዎች የሚያሟላ በአልሚ ምግብ የበለጸገ እንዲሁም የተመጣጠነ ምግብ መቅረብ አለበት።

ለ) የምግብ አዘገጃጀቱ በሥነ-ምግብ እና በሌሎች ባለሙያዎች በሚሰጡት መመሪያ መሰረት መዘጋጀት አለበት።

ሐ) የተቋሙ ሰራተኞች የሕፃናቱን አመጋገብ በተመለከተ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን ሊያውቁ መደረግ አለበት፡፡ እንዲሁም ለሕፃናቱ አስፈላጊውን ድጋፍ ለመስጠት በቂ የሠራተኞች ቁጥር ሊኖር ይገባል።

መ) የምግብ አቅርቦት ሚኒስቴሩ ባወጣው የተቋም ክብካቤ አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል።

## 4) ትምህርት

ሀ) መደበኛ ተቋማዊ የሕፃናት ክብካቤ ተቋም ውስጥ የሚሰጥ የትምህርት ድጋፍ ትኩረት በክብካቤ ሥር ያሉ ሕፃናትን ሁሉ የትምህርት ተደራሽነት እና የትምህርት እድል ያገኙ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

ለ) ሕፃናት የቅድመ መደበኛ ትምህርት፣ የመጀመሪያ ደረጃ፣ ሁለተኛ ደረጃ፣ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ፣ የሙያ እና ልዩ ትምህርት ሊያገኙ ይገባል። ሁሉም የትምህርት ዓይነቶች ከሕፃናት ማቆያ ተቋሙ ውጪ በሆኑ የማኅበረሰብ መገልገያዎች ቢሰጡ ይመረጣል።

ሐ) ልዩ ፍላጎቶች ላላቸው ሕፃናት ጥራት ያለው ትምህርት ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ የመደበኛ ተቋማዊ የሕፃናት ክብካቤ ተቋሙ አግባብነት ካላቸው የመንግሥት አካላትና ሌሎች አጋር ሊሆኑ ከሚችሉ አካላት ጋር በመተባበር የትምህርት እና የመዝናኛ ቦታዎችን ተደራሽ እና አካታች ማድረግ አለባቸው።

መ) የተቋሙ ሠራተኞች በተቋሙ ቅበላ ሊደረግላቸው የሚችሉ ሕፃናትን ልዩ ፍላጎቶች ለማስተናገድ ብቁ የሚያደርጋቸውን ተገቢ ሥልጠና መውሰድ አለባቸው።

## 5) ጤና እና የመጀመሪያ እርዳታ

ሀ) በተቋሙ ውስጥ ክብካቤ የሚሰጡ ሠራተኞች የእያንዳንዱን ሕፃናት የጤና እና የማኅበራዊ ክብካቤ ፍላጎት እና መፍትሄ በሚሹ ጉዳዮች ላይ ተገቢውን ግንዛቤ እንዲያገኙ መደረግ አለበት፡፡

ለ) የጤና እንክብካቤ ባለሙያ፣ የመጀመሪያ እርዳታ ክፍል፣ የክሊኒክ ተደራሽነት በተቋሙ ውስጥ ወይም በተቋሙ አካባቢ መኖር አለበት።

ሐ) በተቋሙ የሚገኙ ሁሉም ሠራተኞች በመሠረታዊ የመጀመሪያ እርዳታ አሰጣጥና ወቅታዊ የሆነ የማጠናከሪያ ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

መ) ሥልጠናው ልዩ ፍላጎቶች ያላቸውን ሕፃናት ግምት ውስጥ ማስገባት እና የማነቅ እና የትንታ (መጫወቻዎች፣ ምግብ፣ ወዘተ) አደጋ፣ የሚጥል በሽታ እና የአደጋ ጊዜ የህይወት ማዳን (ሲ.ፒ.አር) ስልጠናዎች ማካተት አለበት። እንዲሁም የእያንዳንዱን ሕፃን ጤናና ደህንነት የሚያጎለብት መሠረታዊ ዕውቀት እንዲራቸው መደረግ

ሠ) ማንኛውም መደበኛ  የሕፃናት ክብካቤ ተቋማም የተሟላ በቀላሉ ሊገኙ የሚችሉ እንዲሁም በሚገባ የተደራጁ የመጀመሪያ እርዳታ ዕቃዎች እና የእሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች ሊኖሯቸው ይገባል።

ረ) በመደበኛ የህጻናት ክብካቤ ተቋም ውስጥ የሚገኙ ለመጀመሪያ እርዳታ የተዘጋጁ መድኀኒቶችና ሌሎች ዕቃዎች ተሟልተው መገኘታቸውንና  የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለማለፉን፣ እንዲሁም ማንኛውም ዓይነት ድንገተኛ ሁኔታ ቢፈጠር ለማስተናገድ በቂ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ሊታዩ በሚችሉባቸው ቦታዎች ላይ መቀመጥና በመደበኛነትም መፈተሽ አለባቸው።

## 6) የሥነ-ልቦና እና ማኅበራዊ ድጋፍ

ሀ) የሥነ-ልቦና እና ማኅበራዊ ድጋፍ የሕፃናትን አካላዊ፣ ማኅበራዊ፣ ስሜታዊ፣ አዕምሯዊ፣ መንፈሳዊ ፍላጎቶች  ለማሟላት በቀጣይነት  ሊሰጥ ይገባል።

ለ) ለሕፃናትን የሚሰጡ የስነ-ልቦናና ማህበራዊ ድጋፎች ትርጉም ያለውና አዎንታዊ ሕይወት መኖር የሚያስችሉ ሁሉንም የድጋፍ ዓይነቶች ማካተት አለባቸው።

ሐ) የሕፃኑ ጥቅም እና ደህንነት  ለማስጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተቋሙ ሕፃናቱ ከተገኙበት ቤተሰቦች፣ ጓደኞች እና የአካባቢው ማኅበረሰብ ጋር ያላቸውን ትስስር ለማስቀጠል እና ለማጎልበት የሥነ-ልቦናዊ-ማኅበራዊ ድጋፍ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ አለበት።

መ) ከቤተሰብ ጋር መልሶ መቀላቀል ስለሚቻልበት እና ለሕፃኑ ጥቅምን እና ደህንነትን ያማከለ በሚሆንበት ጊዜ በዚህ መመሪያ ከቤተሰብ ጋር መልሶ ስለማቀላቀል የተመለከቱት ድንጋጌዎች  ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

## 7) የባሕሪ አያያዝ

ሀ) ተንከባካቢዎች ማንኛውንም አካላዊ ቅጣት መጠቀምን ማስወገድ እና በምትኩም አዎንታዊ የጸባይ ማረምያ ዘዴዎችን መጠቀም አለባቸው።

ለ) ሕፃናት እንደ ስድብ፣ ማስፈራራት፣ ማንቋሸሽ፣ ማዋረድ፣ ማብሸቅ/ማሾፍ እና መገለል ካሉ ስሜታዊ ጥቃቶች መጠበቅ አለባቸው። እንዲሁም በግለሰብ ባህሪ የቡድን ቅጣት የተከለከለ ነው።

ሐ) ለሕክምና ወይም የሌሎችን ጤና ለመጠበቅ ሲባል እንዲሁም ሁሉም አማራጮች ታይተው በተቀመጡ ፖሊሲዎች መሠረት ለሌሎች ሕፃናት ፈጣን ደህንነት አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር ሕፃናትን ማግለል የተከለከለ ነው።

መ) እያንዳንዱ መደበኛ ተቋማዊ የሕፃናት ክብካቤ ተቋም ለሕፃናቱ እና ለሠራተኞቹ ተደራሽ የሚሆኑ የባሕሪ አያያዝ ፖሊሲ ማዘጋጀት አለበት።

## 8) ግምገማ እና ክትትል

ሀ) መደበኛ ተቋማዊ የሕፃናት ክብካቤ ተቋማት ግምገማ እና ክትትል በየዓመቱ ማካሄድ አለባቸው።

ለ) ሚኒስቴሩ የግምገማ እና የክትትል ጉብኝቶችን ለማካሄድ ከሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና ድርጅቶች፣ ከሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት እና ከማኅበረሰብ አባላት የተወጣጡ ከ5 ያላነሱ ተወካዮችን የያዘ የሥራ አመራር እና የክትትል ባለሙያዎች ቡድን ያቋቁማል።

ሐ) ግምገማ እና ክትትሉን የሚያካሂደው ቡድን በሕፃናት ክብካቤ ተቋም ውስጥ የሚኖሩ ሕፃናትን እንዲሁም አስፈላጊ ሲሆን ሠራተኞችን ቃለ መጠይቅ ማድረግ አለበት። እንዲሁም ሕፃናት በተናጠል እንጂ ተንከባካቢዎቻቸው ባሉበት ቃለ መጠይቅ ሊደረግላቸው አይገባም።

መ) በግምገማው ወቅት የተገኙ ማንኛውም ስጋቶችን እና መወሰድ ያለባቸው ማሻሻያዎችን የሚገልጽ ሪፖርት ጉብኝቱ በተደረገ በ2 ሳምንታት ውስጥ ተዘጋጅቶ ቅጂው ለተቋሙ ስራ አስኪያጅ እንዲደርሰው መደረግ አለበት።

## 9) የህጻናት ጥበቃ

ሀ) ማንኛውም መደበኛ ተቋማዊ የሕፃናት ክብካቤ ተቋም የሕፃናት ጥበቃ ፖሊሲ ሊኖረው ይገባል።

ለ) የሕፃናት ጥበቃ እርምጃዎች የሚከተሉትን ሁኔታዎች አካተው መፈጸም አለባቸው፡፡

1) የጥቃት ምልክቶችን እና የመከላከያ ዘዴዎችን መገንዘብ እንዲችሉ የሠራተኞችን እና የሕፃናትን አቅም መገንባት፤

2) ክንውኖች ወይም ኩነቶች ባልተለመዱ ቦታዎች እና ከህብረተሰቡ ክብካቤ መስጫ ቦታ ውጭ የሚከናወኑ ከሆነ፤ የሕፃናቱን ደህንነት ለመጠበቅ የሚውሉ ልዩ የመከላከያ እርምጃዎች መወሰዳቸውን ማረጋገጥ፣

3) የሕፃናቱን መረጃ፣ ታሪክ እና ምስሎች (ፎቶግራፎች፣ ቪዲዮ ወይም የማኅበራዊ ሚዲያዎችን) አላግባብ የመጠቀም ሥጋትን መቀነስ፤

4) ከሕፃናት ማቆያ ተቋሙ ውጭ የተጠረጠሩ ወይም የተረጋገጡ የሕፃናት ጥቃት ክስተቶችን ማሳወቅ፤

5) የጥቃት ወይም ብዝበዛ ይፈጸማል የሚሉ ስጋቶቸ ወይም አጋጣሚዎች ሲኖሩ ተንከባካቢዎችና ሠራተኞች የምክር ድጋፍ ተደራሽነት መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

6) ከሕፃናቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት እና ተፅእኖ ያለው ማንኛውም አጋር ድርጅት ወይም የተለየ አገልግሎት አቅራቢ ላይ ተገቢ እና ሙሉ የዳሰሳ ጥናት መደረጉን ማረጋገጥ፤

7) በማንኛውም ጊዜ ለሕፃኑ ክብካቤ ኃላፊነት ያለበት ሰው ማንነትማሳወቅ፤

8) ሕፃናት ደህንነት እንዲሰማቸው እና እንዳይሰማቸው ስለሚያደርጓቸው ነገር ከሕፃናቱ ጋር በመወያየት ስለ ራሳቸው ወይም ስለ ጓደኞቻቸው የሚያሳስባቸው ጉዳይ ሲኖር ቅሬታ ማቅረብ የሚችሉባቸውን መንገዶች ላይ መስማማት፤

9) ማንኛውም የተጠቆመ የሕፃናት ጥበቃ ክስተት ወይም ሥጋት በጥንቃቄ የመመርመር፤ በምርመራው ውጤቶች ላይ በመመሥረትም ተጨባጭ ውሳኔ መስጠትና ተግባራዊ ማድረግ፣

10) ለሠራተኞች እና ለሕፃናት ገለልተኛ የሆነ ጥቆማ የማድረጊያ ዘዴ ዝግጁ መሆኑን ማረጋገጥ፣

11) የፀረ-ጉልበተኝነት መርሆዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ፣

12) የወንዶች ልጆች እና የልጃገረዶች እንዲሁም የሕፃናት እና የታዳጊ ወጣቶች የተለያዩ ፍላጎቶች ከግምት ውስጥ መግባታቸውን ማረጋገጥ።

### 10) የድህረ ክብካቤ ድጋፍ

ሀ) መደበኛ ተቋማዊ የሕፃናት ክብካቤ ተቋሙን የለቀቁ እና የድጋፍ ፍላጎት ያላቸው ሕፃናት እና ታዳጊዎች ከክብካቤው ከወጡ እስከ ሦስት ዓመት ድረስ እርዳታ እና ድጋፍ የማግኘት ዕድል ሊኖራቸው ይገባል።

ለ) መደበኛ ተቋማዊ የሕፃናት ክብካቤ ተቋሙ ምክር ወይም ድጋፍ ማስፈለጉን ለማረጋገጥ ከክብካቤ የወጡ ሕፃናትን እና ታዳጊዎችን ቢያንስ በየሩብ ዓመቱ የሚከታተል አንድ ሠራተኛ መመደብ አለበት። ሆኖም የመገናኘት ድግግሞሹ በሕፃኑ የግል ፍላጎቶች ላይ በመመሥረት በጉዳይ ሠራተኛው የሚወሰን ይሆናል።

ሐ) መደበኛ ተቋማዊ የሕፃናት ክብካቤ ተቋሙ ግልፅ የሆነ አሰራር ሊኖረው ይገባል። ተቋሙ በስራ ላይ እስካለ ድረስ በክብካቤው ስር ለነበሩ ሕፃናት እና ታዳጊዎች ምክር እና ድጋፍ በፈለጉ ጊዜ ወደ ክብካቤ ተቋሙ ተመልሰው ሊመጡ ይችላሉ።

## ክፍል አሥር

## በአስቸኳይ ጊዜ የሚሰጥ ክብካቤ

### 69. መነሻ

1) በተፈጥሮ አደጋ፣ በጦርነት፣ በፖለቲካ ሁከት ወይም ብዙ ሕዝብ በሚፈናቀልበት ወቅት አልያም በስደተኞች መመለስ ምክንያት ሕፃናት ከቤተሰቦቻቸው ወይም ከተንከባካቢዎቻቸው እና ከማኅበረሰባቸው ጋር የመነጠል ስጋት ላይ ስለሚወድቁ በፈቃደኝነት፣ በግዴለሽነት ወይም በሁለተኛ ደረጃ ሊፈጠር የሚችል የመነጠል ስጋትን ለመቀነስም ተጨማሪ ቅድመ ጥንቃቄዎች መደረግ አለበት።

### 70. በአስቸኳይ ጊዜ የሚሰጥ ክብካቤ መርሆዎች

1) በአስቸኳይ ጊዜ ወቅት የሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማት እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በዚህ መመሪያ ውስጥ የሰፈሩት መርሆዎችን በተለይም ለሚከተሉት ልዩ ትኩረት በመስጠት መተግበራቸውን ያረጋግጣሉ፡-

ሀ) ሕፃናትን የመንከባከብ እና የመጠበቅ ቀዳሚ ኃላፊነት የቤተሰቦቻቸው እና የማኅበረሰቡ መሆኑን፣

ለ) ሁሉም ጥረቶች የቤተሰብን አንድነት መጠበቅ እና በአስቸኳይ ጊዜ አንድ ላይ መቆየታቸውን የማረጋገጥ፣

ሐ) በአስቸኳይ ጊዜ ለተነጠሉ እና ተጋላጭ ለሆኑ ሕፃናት ክብካቤ፣ ጥበቃ፣ ክትትል እና ምላሽ በመስጠት ረገድ ማኅበረሰቦች ቁልፍ ሚና እንዲጫወቱ መደገፍ።

## 71. የአስቸኳይ ጊዜ የባለድርሻ አካላት ሚና እና ኃላፊነት

1) ሚኒስቴሩ በአስቸኳይ ጊዜ ወቅት የሕፃናትን ክብካቤ እና ጥበቃ ለማረጋገጥ የአስቸኳይ ጊዜ ጉዳዮች ኃላፊነት ከተጣለበት የመንግሥት መስሪያ ቤት እና አግባብ ካላቸው ሌሎች ተቋማት ጋር በትብብር ይሠራል።

2) ሚኒስቴሩ በአስቸኳይ ጊዜ የተጎዱ፣ በተለይም ከቤተሰቦቻቸው የተነጠሉ እና የወላጅ ወይም ያሳዳጊ ክብካቤ የሌላቸዉ ሕፃናትን ክብካቤ እና ጥበቃ በሚመለከት የዓለም አቀፍ እና የሃገር ውስጥ ድርጅቶች ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች እና ጥረቶች የተቀናጁ መሆናቸውን እንዲሁም ተገቢ የውይይት እና የቅንጅት ሥርዓቶች መኖራቸውን ማረጋገጥ አለበት።

3) ሚኒስቴሩ የህጻናት ስደተኞች ጥበቃ እና ድጋፍን በተመለከተ ከሚመለከታቸው አለም አቀፍና የሀገር ውስጥ ድርጅቶች ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡

4) የስደተኛ ሕፃናት እና ወጣቶች ጥበቃ አገልግሎት የሚሰጡ በጎ ፈቃደኞች በአማራጭ ክብካቤ ውስጥ ለተመደቡ ስደተኛ ሕፃናት እና ቤተሰቦቻቸው የሚደረጉ ክትትሎችን እና የቤት ለቤት ጉብኝቶችን ይደግፋሉ።

## 72. የመለያየት ሥጋትን መቀነስ

1) በከፍተኛ ቁጥር የህዝብ መፈናቀል ሲያጋጥም ቤተሰቦች አብረው መጓዛቸውን እና ሕፃናት በማንኛውም ጊዜ በአዋቂዎች ጥበቃ ስር መሆናቸዉን በማረጋገጥ የመለያየትን ስጋት ለመቀነስ ጥረት መደረግ አለበት።

2) የሚመለከተው የመንግስት አካል የመልቀቂያ እና የአቀባበል ሂደቶች ወዳልታሰበ መነጣጠል እንዳያመሩ ማረጋገጥ አለበት።

3) መረጃ የመስጠት ጥረቶችን ጨምሮ የመለያየት አደጋን የመከላከል ይዘት ያላቸው መልእክቶችን በየመዳረሻ ቦታ መለጠፍ ወይም እንዲታዩ ማድረግ፣ ወላጆች እና ሕፃናት መነጠልን ጥቆማ ማድረግ እንዲችሉ በቀላሉ የሚታዩ ቦታዎችን መለየትን፣ በተፈናቃይ መጠለያዎች ውስጥ የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያ ማሰማራትን እና ሌሎች እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው፡፡

4) ሕፃናት ከቤሰባቸው የተለያዩ ከሆነ፣ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተቀመጡት የጉዳይ አያያዝ ሂደቶች በአስቸኳይ ሁኔታዎች ውስጥ ተግባራዊ ይሆናሉ። እንዲሁም ሕፃኑ ከቤተሰብ መለያየቱ እንደተረጋገጠ ቤተሰብን የማፈላለግ ጥረቶች ወዲያውኑ መጀመር አለበት።

## 73. በአስቸኳይ ጊዜ የሚሰጡ አማራጭ የሕፃናት ክብካቤ

1) በአስቸኳይ ጊዜ ሕፃናት በማኅበረሰባቸው ውስጥ ባሉ የቤተሰብ ተኮር ክብካቤ ከቤተሰቦቻቸው ጋር መልሰው እስኪቀላቀሉ ወይም ካልተቻለም ቋሚ የሆነ የአማራጭ ክብካቤ መፍትሔ እስከሚገኝ ድረስ በጊዜያዊ አማራጭ ክብካቤ ዉስጥ መመደብ አለባቸው።

2) ተቋማዊ ክብካቤን ለመቀነስ እና ከቤተሰብ ጋር መልሶ ማቀላቀል እና ማዋሃድን ለማመቻቸት እጩ የአስቸኳይ ጊዜ የአደራ ቤተሰቦችን አስቀድሞ በመለየት የአስቸኳይ ጊዜ የዝግጅት ዕቅዶች መዘጋጀት አለባቸው።

3) በአስቸኳይ ጊዜ የሕፃኑን የቅርብ ቤተሰብ ለማግኘት በሚደረግ ጥረት ጊዜ በሚከተሉት ጊዜያዊ የክብካቤ አማራጮች ውስጥ እንዲመደቡ መደረግ አለበት፡፡

ሀ) የተቋጥሮ ዝምድና ክብካቤ፤

ለ) የአደራ ቤተሰብ ክብካቤ፤

ሐ) ዕድሜያቸው ከፍ ላሉ የሕፃናት ከድጋፍ ጋር ራስን ችሎ የመኖር አገልግሎት።

4) ጉዲፈቻ በአስቸኳይ ጊዜ እንደ አማራጭ የህጻናት ክብካቤ መወሰድ የለበትም። ሆኖም ቤተሰብን የማፈላለግ እና መልሶ የማቀላቀል ሁሉም ጥረቶች ከተደረጉ እና ቢያንስ የሁለት ዓመት ጊዜ ካለፈ በኋላ ጉዲፈቻ እንደ አማራጭ ሊወሰድ ይችላል።

5) የአስቸኳይ ሁኔታዉ እንደተፈጠረ ሌሎች አማራጮች በሚገባ ታይተው ያለመገኘታቸው ሲረጋገጥና ተቋማዊ ክብካቤ የመጨረሻው አመራጭ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር ተቋማዊ ክብካቤን እንደ አማራጭ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡

6) የሁኔታው አስቸኳይነት ሲያበቃ፣ ሕፃናትን በተቋማዊ ክብካቤ ተቋም ውስጥ ድጋፍ እያገኙ እንዲቆዩ የሚደረገው ምደባ ከስድስት ወራት መብለጥ የለበትም፡፡

7) በአስቸኳይ ሁኔታዎች ውስጥ የሚገኙ ሕፃናት የክብካቤ ምደባ የተመዘገበ፣ ክትትል የሚደረግበት እንዲሁም በሚመለከታቸው ባለሥልጣናት የሚገመገም መሆኑ ማረጋገጥ መረጋገት አለበት፡፡

8) ማንኛውም ስደተኛ ሕፃን በብሔራዊ የሲቪል ምዝገባ እና የወሳኝ ኩነቶች የመረጃ ቋት መካተት አለባቸው።

## ክፍል አሥራ አንድ

## የጉዳይ አያያዝ የአሰራር ሥርዓት

### 74. የጉዳይ አያያዝ

1) ማንኛውም መደበኛ የሕፃናት አማራጭ ክብካቤ በብሔራዊ የሕፃናት የጉዳይ አያያዝ ማዕቀፍ የተቀመጡ የጉዳይ አያያዝ ሂደቶችን መከተል አለበት።

2) የጉዳይ አያያዝ ስራ አስኪያጁ፣ የጉዳይ ሠራተኛው እና ሌሎች በዚህ መመሪያ ሥር ለሕፃናት አማራጭ ክብካቤ በመስጠት ሂደት ውስጥ የሚሳተፉ ባለሙያዎች በብሔራዊ የሕፃናት የጉዳይ አያያዝ ማዕቀፍ የተጠቀሱትን ደረጃዎች እና የአሰራር ሂደቶችን መከተል አለባቸው፡፡

3) ማንኛውም ሕፃን ከወላጅ ክብካቤ የተነጠለ መሆኑ ከተረጋገጠ፣ የሕፃኑ ወላጆች እና የተቋጥሮ ዝምድና ያላቸው የቤተሰብ አባላትን ለማግኘት አፋጣኝ ጥረቶች መደረግ አለባቸው። የሚደረገው ጥረትም የተሟላ እና በሚገባ የተሰነደ መሆን አለበት።

4) ማንኛውም ሕፃን ከቤተሰብ የተለየ መሆኑ ከተረጋገጠ እና ቤተሰቡን ፈልጎ ማግኘት የማይቻል ከሆነ የጉዳይ ሠራተኛው በብሔራዊ የሕፃናት የጉዳይ አያያዝ ማዕቀፉ በሚደነግገው ቅፅን በመጠቀም ጉዳዩን ማረጋገጥ እና የመጀመርያ ደረጃ ማጣሪያ ማከናወን አለበት።

5) የጉዳይ ሠራተኞች ሕፃኑን ተቀብለው ወይም መዝግበው በብሔራዊ የሕፃናት ጉዳይ አያያዝ ማዕቀፍ የተገለጸውን ሂደት በመከተል እና የተዘጋጁ ቅፆችን በመጠቀም የተጋላጭነት ደረጃውን መለየት አለባቸው፡፡

6) የማጣራት ሂደቱ በሕፃኑ ላይ የወንጀል ባሕርይ ያለው የከፋ ስጋት በወቅቱ መኖሩን ካመለከተ ሕፃኑን ወደ ፖሊስ፤ በሕፃኑ ላይ የአካል ጉዳት ደርሶ ከሆነ ደግሞ ወደ ጤና ተቋም መወሰድ አለበት።

7) የሕፃናት ጥበቃ ባለሙያው ወይም አግባብነት ያለው ቢሮ ስለመረጃው እና ስለተወሰደው አፋጣኝ እርምጃ ወዲያውኑ እንዲያውቁት መደረግ አለበት፡፡

8) በመንግሥት የሚከናወን ሕፃንን ከቤተሰቡ አካባቢ የማውጣት ተግባር ከሕፃኑ ደህንነት አንጻር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እንደ መጨረሻ አማራጭ መወሰድ ያለበት እርምጃ ሲሆን በዚህ መመሪያ በክፍል ሁለት የተዘረዘሩትን ሂደቶች የጠበቀ፣ ጊዜያዊ እና በጥንቃቄ ክትትል የሚደረግበት ሊሆን ይገባል።

9) አንድ ሕፃን ከቤተሰቡ የተለየ ከሆነ፣ የዳሰሳ ጥናቱ የሕፃኑ የመለየት ምክንያቶችን፣ ቤተሰቡ እና ሕፃኑ በመልሶ መቀላቀል ላይ ያላቸውን አመለካከት ሊገልጽ ይገባል።

10) ጉዳይ አያያዙ በብሔራዊ የሕፃናት የጉዳይ አያያዝ ማዕቀፍ የተዘረዘሩ አካሄዶችን ማለትም ጥበቃ ሊያስፈልገው የሚችል ሕፃንን መለየት፣ የቅበላ ማጣርያ፣ የዳሰሳ ጥናት፣ የክብካቤ ዕቅድ ዝግጅት፣ የክብካቤ ዕቅዱ ትግበራ፣ የጉዳይ ግምገማ እና የጉዳይ ማጠናቀቂያን በቅደም ተከተል መከተል ይኖርበታል። እያንዳንዱ ቅደም ተከተል በአግባቡ ሊከናወን እና የሕፃኑን ጥቅምና ደህንነት ያማከለ ሊሆን ይገባል።

11) የሕፃኑን ጥቅም እና ደህንነት ያላማከለ ምንም ዓይነት ውሳኔ ወይም እርምጃ ሊወሰድ አይገባም፤ እንዲሁም ከሚመለከታቸው የስራ ዘርፎች የተውጣጡ ባለሙያዎች በተዋቀረ ቡድን መካሄድ እና ሕፃኑን ተሳታፊ ያደረገ መሆን አለበት፡፡

12) የዳሰሳ ጥናቱን ተከትሎ በጉዳይ አያያዝ ዙርያ ያሉ ባለድርሻ አካላት በአንድ ጉዳይ ዙርያ ያሉ አስፈላጊ ምክንያቶችን በመገምገም እና በመመዘን በተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መብቶች ስምምነት፣ በአፍሪካ የሕፃናት መብቶችና ደህንነት ድንጋጌ፣ የተባበሩት መንግስታት የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት እና ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸው ሌሎች አለም አቀፍ ህጎች ያስቀመጧቿውን ሃላፊነቶች ክብደት በመስጠት የአንድን ሕፃን መብት በሚገባ ያከበረ፣ ጥቅምና ደህንነቱን ያረጋገጠ ሁሉን ያማከለ ውሳኔ መስጠት ይኖርባቸዋል።

13) ባለድርሻ አካላት የዳሰሳ ጥናቶችን እና የሕፃኑን ጥቅምና ደህንነትን ያማከለ ውሳኔን ሲሰጡ ሚኒስቴሩ ባወጣው መመሪያዎች መሠረት መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡

14) የሕፃኑን ጥቅምና ደህንነትን ያማከለ ውሳኔ አሰጣጥ መደበኛው ሂደት መከተል አለበት።

15) አንድ ሕፃን የጥበቃ አገልግሎት እንደሚያስፈልገው መሆኑ ከተረጋገጠ፣ የጉዳይ ሠራተኛው ሕፃኑን በብሔራዊ የጉዳይ አያያዝ መመሪያዎች ማዕቀፍ በተቀመጡ መስፈርቶች መሠረት በብሔራዊ የሕፃናት የጉዳይ አያያዝ ስርዓት ወይም የሕፃናት ጥበቃ የመረጃ አስተዳደር ስርዓት መመዝገብ አለበት፡፡

16) በብሔራዊ የሕፃናት የጉዳይ አያያዝ ማዕቀፍ የተዘረዘሩት ሌሎች አካሄዶች እና ኃላፊነቶችም ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ተግባራዊ መደረግ አለባቸው፡፡

## ክፍል አሥራ ሁለት

## የመረጃ አያያዝ፣ ክትትል እና ግምገማ

### 75. የመረጃ አያያዝ

1) ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ዓላማ መረጃ አያያዝ የአማራጭ የሕፃናት ክብካቤ አገልግሎቶች መረጃዎችን የመሰብሰብ፣ የማከማቸት፣ የመጠበቅ፣ የማረጋገጥ፣ የመተንተን፣ የማቀናበር፣ እና የማሠራጨት ሂደት ነው።

2) ሚኒስቴሩ እና ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በአሰራር ሂደታቸው ውስጥ ለመረጃ ማሰባሰብ፣ ምዝገባ እና ትንተና በቂ ጊዜ እና ሃብት መመደብ አለባቸው።

3) ሚኒስቴሩ ለአማራጭ የሕፃናት ክብካቤ አገልግሎቶች የሚውል ብሔራዊ የመረጃ ቋት ዝግጁ መሆኑን እና ሂደቱን ለመደገፍ የሚያስችል በቂ የሰው እና የገንዘብ ሀብት መኖሩን ያረጋግጣል።

4) አስቀደሞ በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት የተሰበሰበ መረጃ በወረቀት ላይ በተመሠረተ የመረጃ አያያዝ ሥርዓትን በመጠቀም ቢመዘገብም በቀጣይነት በብሄራዊ ጉዳይ አያያዝ ስርዓት ውስጥ መግባት ይኖርበታል።

5) አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የመረጃውን ጥራት ለማሻሻል የተሳሳቱ እና የሚጣረሱ መረጃዎችን መለየት እና ማስወገድ አለባቸው። እንዲሁም መረጃዎች ትክክል፣ የተሟሉ እና ከፍተኛ ጥራት ያላቸው መሆኑንም ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

6) መረጃ ወደ ብሔራዊ የጉዳይ አያያዝ ሥርዓት በሚገባበት ወቅት መረጃውን የሚያስገባው ግለሰብ ማንኛውም የገባ መረጃን ወዲያውኑ መገምገሙን እና ትክክለኛነቱ መጣራቱን ማረጋገጥና ማንኛውም ስህተት ማረም አለበት፡፡

7) ሚኒስቴሩ እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የተሻለ የእቅድ እና የበጀት አፈጻጸም እንዲኖራቸው በየተወሰነ ጊዜ መረጃን መተንተን ይኖርባቸዋል።

8) ሚኒስቴሩ እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለሕፃናት የሚሰጧቸውን አገልግሎቶች ለማሻሻል ጠንካራ የግምገማ ሂደቶችን የሚያረጋግጡ ስኬቶችን፣ ተግዳሮቶችን እና የተገኙ ትምህርቶችን የሚይዙ ከፍተኛ ጥራት ያላቸው ግልጽ ሪፖርቶችን ማዘጋጀት አለባቸው።

9) አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አስተማማኝ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችን ለማጎልበት ለሠራተኞቻቸው ሥልጠና ማመቻቸት አለባቸው።

### 76. የሕፃን ማኅደር መክፈት

1) ለእያንዳንዱ ሕፃን በስሙ ማኅደር መከፈት አለበት፤ ሕፃኑ ወደ ሌላ አማራጭ የሕፃናት ክብካቤ በሚዛወርበት ወቅት ማኅደሩ ከሕፃናኑ ጋር አብሮ መሄድ አለበት።

2) ሕፃኑን በመጀመሪያ ያገኘው አካል የሚከተሉትን መረጃዎች መሰብሰብ ይኖርበታል፡-

ሀ) የልየታ ቀን፣

ለ) ስም (የቅፅል ስምን ጨምሮ) ፣

ሐ) ፆታ፣

መ) የሕፃኑ ሁኔታ (የተተወ/የተጣለ፣ ጠፍቶ የተገኘ፣ የቅርብ ተንከባካቢ የሌለው፣ ) ፣

ሠ) የሕፃኑ የልደት ቦታና እና ቀን ወይም የሚገመት ዕድሜ ፣

ረ) ሕፃኑ የአካል ጉዳት ካለበት፣

ሰ) የቤተሰብ አባላት የልደት ቦታ እና ቀን፣

ሸ) የቀድሞ እና የአሁን ተንከባካቢ፣

ቀ) የአማራጭ ክብካቤ የምደባ ታሪክ፣

በ) የወላጅ ወይም ወላጆች የተቋጥሮ ዝምድና ያላቸው ቤተሰቦች ስም እና መገኛ አድራሻ፣

ተ) የቀድሞ ተንከባካቢ ስም እና አድራሻ (ካለ)፣

ቸ) ሃይማኖት፣

ኀ) የሚናገሩት ቋንቋ፣

ነ) የትምህርት ደረጃ እና የት/ቤት ስም (አስፈላጊ ከሆነ)።

## 77. የመረጃ ክምችት፣ ዝውውር እና ደህንነት

1) እያንዳንዱ በወረቀት እና በዲጂታል የተመዘገበ መረጃ በግል ማኅደር ውስጥ የቁጥር ስያሜ ተሰጥቶት ሊቀመጥ ይገባል።

2) አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና ሚኒስቴሩ የተሰበሰበው መረጃ ካልተፈቀዱ ማስተካከያዎች፣ ቅጂ፣ ከመነካካት፣ ከሕገ-ወጥ ውድመት፣ በድንገት ከመጥፋት፣ ተገቢ ካልሆነ የጉዳይ ማጠቃለያ እና ካልተፈቀደ ዝውውር በአስተማማኝ ሁኔታ የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው።

3) ሁሉም የሕፃናቱ ዲጂታል መረጃዎች በይለፍ ቃል የተጠበቁ መሆን እና የይለፍ ቃሉም በየተወሰነ ጊዜ መቀያየር ይኖርበታል። እንዲሁም የይለፍ ቃል በግለሰቦች መካከል መጋራት የተከለከለ ነው።

4) የወረቀት ማኅደሮችን በተመለከተ፤ ሚኒስቴሩ እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የእያንዳንዱ ጉዳይ ማኅደር ሽፋን ላይ ምንም ዓይነት የመለያ መረጃ አለመኖሩን እና እያንዳንዱ ማኅደር በግለሰብ የጉዳይ ማኅደር ቁጥር ብቻ በግልጽ የተሰየመ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው።

5) የወረቀት ማኅደሮች የማወቅ አስፈላጊነት ላይ በመመስረት መረጃው ባስፈለገ ጊዜ ብቻ እንዲገኙና ደህንነታቸው በተረጋጠ እና በአስተማማኝ ቦታ መቀመጥ አለባቸው።

6) በባለድርሻ አካላት መካከል የመረጃ ልውውጥ የሚኖረው የማወቅ አስፈላጊነት ላይ መሰረት ያደረገ እንዲሁም የሕፃኑን ጥቅምና ደህንነትን ያማከለ ሲሆን ብቻ ነው።

7) የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት መረጃን የሚያጋሩባቸው መመርያዎችን ወይም ስምምነቶችን በማዘጋጀት ከጉዳይ ጋር የተያያዘ የመረጃ ፍሰትን በመደበኛነት፣ በአስተማማኝ እና ሥነ-ምግባርን በጠበቀ መንገድ መከናወናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

8) የወረቀት ማኅደሮች የሚዛወሩ ከሆነ፣ ማኅደሮቹ ማኅተም በተደረገበት የታሸገ ሳጥን ወይም ፖስታ ውስጥ መቀመጥ አለባቸው።

9) የወረቀት መረጃዎች የሚወገዱት ሥልጣን ባለው የመንግሥት አካል በተሰጡ የመረጃ አወጋገድ ሂደቶች መሠረት መሆን ይኖርበታል።

10) መረጃ በኢንተርኔት ወይም በሌላ ዲጂታል መንገድ በሚጋራበት ጊዜ በይለፍ ቃል በተጠበቁ ማኅደሮች መላክ ይኖርበታል።

11) ሚኒስቴሩ እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የማንኛውንም ዲጂታል ማኅደር በመደበኛ ሁኔታ መጠባበቂያ ቅጂ መያዝ አለባቸው። እንዲሁም ጥሩና አስተማማኝ የሆነ ሁለተኛ የኤሌክትሮኒክ ክምችት ዘዴ ማዕከላዊ በሆነ ቦታ መቀመጥ ይኖርበታል።

12) መረጃን ከመበላሸት እና ከመጥፋት ለመታደግ ኮምፒውተሮች ወቅቱን የጠበቀ ፀረ-ቫይረስ ሶፍትዌር ሊኖራቸው ይገባል።

13) አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ማኅደሮችን ለክልል ቢሮዎች ማጋራት እንዲሁም የአገልግሎት ዘመናቸውን የጨረሱ ማኅደሮችን አግባብ ላለው ቢሮ ማስተላለፍ አለባቸው።

## 78. *ሪፖርት*

1) አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የራሳቸው የክትትል፣ የግምገማ እና የሪፖርት ሥርዓት መዘርጋት አለባቸው። ይህም ሥርዐት ተቋሞች የአገልግሎታቸውን ጥራት እና ተደራሽነት ለመከታተል እንዲሁም ማሻሻያ ለማድረግ የሚያግዝ መሆን አለበት።

2) አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሪፖርት በሚያደርጉበት ወቅት ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃ ያቀርባሉ:-

ሀ) በጉዳይ አያያዝ ሥርዓቱ የተገለገሉ የሕፃናት እና የቤተሰብ ብዛት፣

ለ) የሕፃናቱ አጠቃላይ ሁኔታ (ዕድሜ፣ ጾታ፣ ጤና፣ ትምህርት፣ የቤተሰቡ የኢኮኖሚ ሁኔታ፣ እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎች)፣

ሐ) ትኩረት የሚፈልጉ የጉዳይ ምድብ፣

መ) ለእያንዳንዱ ሕፃን የተደረጉ የአገልግሎት ዝውውሮች ብዛት እና የአገልግሎቱ አይነት፣

ሠ) የጉዳይ ውይይት መድረክ የሚያስፈልጋቸው የሕፃናት ብዛት፣

ረ) ሕፃናት የጉዳይ አያያዝ አገልግሎቶችን እያገኙ ያሉበት የጊዜ ርዝመት፣

ሰ) የተጠናቀቁ ጉዳዮች የተጠናቀቁባቸው ምክንያቶች፡፡

3) መረጃው በክትትል እና በግምገማ ባለሙያ፣ በፕሮጀክት ቡድኑ ወይም በቀጥታ ከሕፃናት ወይም ቤተሰቦች ጋር በሚሠሩ የጉዳይ ሠራተኞች ሊሰበሰብ እና ሊደራጅ ይችላል።

4) አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በየሶስት ወሩ እና ዓመታዊ ሪፖርቶችን ሚኒስቴሩ ባዘጋጀው ቅጽ መሰረት ተዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ፣ አግባብ ላላው ቢሮ ማቅረብ አለባቸው። ተጨማሪ የሪፖርት መስፈርቶች በዚህ መመርያ እና ሌሎች በሚዘጋጁ የአፈጻጸም መመሪያዎች መሰረት ሊዘጋጁ ይችላሉ፡፡

## 79. ክትትል እና ግምገማ

1) የአገልግሎት ሰጪ ተቋማትን የአገልግሎት ጥራት መከታተልን እና መቆጣጠርን ዓላማ ያደረገ መደበኛ ክትትልና ግምገማ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ባለው ቢሮ ይካሄዳል።

2) አግባብነት ያለው ቢሮ የሚከተሉት ሃላፊነቶች አሉበት፣

ሀ) በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚቀርቡ የሩብ ዓመትና ዓመታዊ ሪፖርቶችን መገምገም፤

ለ) የፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ግምገማ በየተወሰነ ጊዜ ማካሄድ፤

ሐ) ከአማራጭ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር የግምገማ ስብሰባዎችን ማዘጋጀት፤

መ) ከግምገማ ስብሰባዎች በኋላ ለአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ግብረ መልስ መስጠት።

3) አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አገልግሎቶቻቸውን ለመገምገም የአሰራር ሂደት እና የተጽዕኖ ግምገማዎችን ማካሄድ አለባቸው።

4) ሚኒስቴሩ እና አግባብነት ያላው ቢሮ፣ የአማራጭ ሕፃናት ክብካቤ አገልግሎቶችን ትግበራ እና የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ በሚዘጋጅ ደረጃዉን የጠበቀ የአሰራር ሂደት (ኤስ.ኦ.ፒ) ወይም መመሪያ መሠረት ክትትል እና ግምገማ ያካሂዳሉ። የግምገማ ቡድኑም፡-

ሀ) በክትትል ቅጾች የተመዘገበ መረጃን ይገመግማል፤

ለ) የግምገማ ስብሰባዎችን ቃለ-ጉባኤ ይይዛል፤

ሐ) ከአገልግሎት ተጠቃሚዎች ግብረ መልስን ይሰበስባል፤

መ) የአገልግሎት ሰጪ ተቋማትን የሩብ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርቶችን ይገመግማል፤

ሠ) የመስክ ጉብኝቶችን አካሂዶ የሚያገኛቸውን መረጃዎች ያደራጃል።

5) ግምገማዎች የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዓመት ሁለት ጊዜ (በግማሽ ዓመትና በዓመቱ መጨረሻ) ይከናወናሉ፡-

ሀ) የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ፖሊሲዎች እና ተግባራት፣

ለ) የማኅበራዊ አገልግሎት የሰው ኃይል እና ብቃት፣

ሐ) በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚሰጡ አገልግሎቶች የሕፃናቱን ጥቅም እና ደህንነት ያማከሉ እና ከሕፃናቱ መብቶች አኳያ የተቃኙ መሆናቸውን እንዲሁም አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ ውጤታማ እና ተገቢ የሆኑ የጉዳይ አያያዝ መመርያዎችን የሚተገብር መሆኑን፣

መ) አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አጠቃላይ ወይም ዝርዝር ዓላማዎቻቸውን እያሳኩ ወይም ያሳኩ መሆናቸውን፣

ሠ) አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ የማኅበረሰብን እና የሕፃናትን ተሳትፎ ከግምት ውስጥ የሚያስገባ መሆኑን፣

ረ) አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ የሥርዓተ ፆታን እና የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ በአገልግሎቶቹ ውስጥ ማካተቱን፣

ሰ) በእንክብካቤ ሰጪው እንዲሁም በሌሎች የአማራጭ ክብካቤ ዓይነቶች ውስጥ የሕፃናቱ ደህንነት እና ጥበቃ አስተማማኝ መሆኑን፣

ሸ) የጉዳይ ማዘዋወር እና ማጠናቀቂያዎች በአግባቡ መተግበራቸውን፣

ቀ) የድህረ ምደባ አገልግሎቶች በአግባቡ የእየተተገበሩ መሆኑን፣

6) የግምገማ ቡድኑ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ የፕሮጀክቱ አፈጻጸም ከፕሮጀክት ዕቅድ አንጻር የሚለካበት የራሱ የማረጋገጫ ዝርዝር ይኖረዋል።

7) ማንኛውም አገልግሎት ሰጪ ተቋም የአገልግሎት ጥራትን ለማሻሻል አግባብነት ያለው የመንግሥት አካላት እንደ ግብዓት የተሰጠውን ግብረ መልስ ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።

8) በዚህ ክፍል የሚካሄዱት ሁሉም የክትትል እና የግምገማ ክንውኖች የብሔራዊ የሕፃናት ደረጃዉን የጠበቀ የአሰራር ሂደትን (ኤስ.ኦ.ፒ) መከተል አለባቸው።

9) ተሞክሮዎች ስለማስፋት

ሀ) ሚኒስቴሩ በብሔራዊ ደረጃ ከእያንዳንዱ አገልግሎት የተገኘውን ልምድ በአግባቡ በመሰነድ በዚህ መመርያ መሰረት በብሔራዊ ደረጃ ለሚመሰረቱ ስራ አስፈጻሚ ቡድን እና ብሔራዊ ግብረሀይል ማሰራጨት ይኖርበታል።

ለ) አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የተገኙ ተሞክሮዎች ለማሳየትና ለአማራጭ እና ተቋማዊ ክብካቤ ለማጋራት የውስጣዊ አካሄድ ትንታኔ ማካሄድ አለባቸው፡፡ እንዲሁም ቁልፍ ስኬቶችን፣ ተግዳሮቶችንና የተገኙ ትምህርቶችን መሰነድ እና ለሚኒስቴሩ መጋራት አለባቸው።

## ክፍል አሥራ ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 80. ተጠያቂነት

በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች በመጣስ በሕፃናት ላይ ጉዳት ያደረሰ ሕፃናቱን ለመንከባከብ ኃላፊነት የተሰጠው ሰው ወይም የመንግሥት ሠራተኛ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም እንደአግባቡ በአስተዳደር ወይም በወንጀል ወይም በፍትሐ ብሔር ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### 81. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

በዚህ መመሪያ የተደነገጉት የሕፃናት መብቶችና የአሰራር ስርዓቶች እያደጉና በሂደት እየተሟሉ የሚመጡ በመሆናቸው ተፈፃሚነታቸው የአንድ ዓመት የሽግግር ጊዜ ይኖረዋል። መመሪያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከሚቆጠር አንድ ዓመት በኋላ ማንኛውም አገልግሎት ሰጪ ተቋም በዚህ መመሪያ የተጣለበትን ግዴታ ካልተወጣ ተጠያቂ ይሆናል።

### 82. መስፈርቶችን ስለማውጣትና አሰራሮችን ስለመዘርጋት

ይህን መመሪያን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መስፈርቶችንና ቅጾችን ሚኒስቴሩ ሊያወጣ ይችላል፡፡

### 83.የተሻሩ ህጎች

የሚከተሉት መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡ -

1) የአደራ ቤተሰብና የአገር ውስጥ ጉዲፈቻ አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 48/2013

2) የማህበረሰብ አቀፍ የህጻናት ክብካቤ፣መልሶ ማቀላቀልና ማዋሃድ፣ የአደራ ቤተሰብ፣ ጉዲፈቻና የተቋማዊ ክብካቤ አገልግሎት መመሪያ ግንቦት 2001

### 84. ተፈፃሚነት የሌላቸዉ መመሪያዎችና አሰራሮች

ማንኛዉም መመሪያ ወይም አሠራር ከዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረኑ ከሆነ ተፈፃሚነት አይኖራቸዉም፡፡

### 85. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፌደራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፫/፪ሺ፲፪ መሰረት በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በፍትህ ሚኒስቴር እና በሚኒስቴሩ ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር)**

**የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር**

**ሚኒስትር**